# አማርኛ
## እንደአፍ መፍቻ ቋንቋ

# የመምህር መምሪያ
## 2ኛ ክፍል

አዘጋጆች

አንበሴ በቀለ

እሸቱ ኣጋ

አርታኢ

መላኩ ጽጌ

ትጃኒ ምትኩ

ጥራት ተቆጣጣሪዎች

በርናባስ ደበሎ

ይልፋሸዋ ጥላሁን

ታምሩ ገለታ(ዶ/ር)

ግራፊክስ

ጆናታን ግርማ

# ማውጫ

ርዕስ ገጽ

ማውጫ ........ ii

መግቢያ ........ v

ምዕራፍ አንድ ........ 1

ልብሶች ........ 1

ምዕራፍ ሁለት ........ 12

ወቅቶች ........ 12

ምዕራፍ ሶስት ........ 21

ተረቶች ........ 21

ምዕራፍ አራት ........ 31

የአትክልት ቦታ ........ 31

ምዕራፍ አምስት ........ 39

የአከባቢ ጽዳት ........ 39

ምዕራፍ ስድስት ........ 48

ባህላዊ ሙዚቃ ........ 48

ምዕራፍ ሰባት ........ 58

መልካም ባህሪ ........ 58

ምዕራፍ ስምንት ........ 66

የምግብ ዝግጅት ........ 66

**ምዕራፍ ዘጠኝ**......................................................................75

**ዲጂታል መሳሪያዎች**......................................................................75

**ምዕራፍ አስር**......................................................................84

**የዱር እንሰሳት**......................................................................84

**መልሶች**......................................................................92

**መርሃ ትምህርት**......................................................................99

© 2014 ዓ.ም. የኦሮሚያ ትምህርት ቢሮ።

ይህ መፅሐፍ በ2014 ዓ.ም በኦሮሚያ ትምህርት ቢሮ እና በነቀምቴ መምህራን ትምህርት ኮሌጅ በትብብር የተዘጋጀ ነው። የመጽሐፉ ህጋዊ የቅጂ ባለቤት የኦሮሚያ ክልል ትምህርት ቢሮ ነው። መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው። የዚህን መጽሐፍ ክፍል በተለያዩ መሳሪያዎች ያለባለቤቱ የቅድሚያ ፈቃድ እንደገና ማሳተም፣ ማሰራጨት፣ ማከማቸትና መልሶ መጠቀም አይቻልም።

የስዕሎችን የቅጂ መብቶች ለማክበር በተቻለን መጠን የሚፈለግብንን ጥረት ሁሉ አድርገናል። ሳናውቅ በስህተት ሳንጠቅሳቸው የተዘለሉ ካሉ በቅድሚያ ይቅርታ እየጠየቅን በሚቀጥሉት ህትመቶች አስፈላጊውን እውቅና እንደምንሰጥ ለመግለጽ እንወዳለን።

# መግቢያ

ይህ የመምህር መምሪያ የተዘጋጀው በአማርኛ ቋንቋ አፋቸውን ለፈቱ ተማሪዎች ማስተማሪያ የተዘጋጀውን የተማሪ መፅሐፍ መሠረት በማድረግ ነው። በመሆኑም በተማሪ መጽሐፍ ውስጥ የቀረቡትን ይዘቶች እንዴት ማስተማርና ተግባራቱን እና መልመጃዎቹን እንዴት ማሠራት እንደሚገባ ሁሉአቀፍ የሆነ ጥቆማ ለመምህር ያቀርባል። ከዚህም ሌላ የክፍል አደረጃጀትና አስተዳደሩ ምን መሆን እንደሚገባው አቅጣጫ ያስቀምጣል። በዚህም መምህራን የየክፍላቸውንና የየተማሪዎቻቸውን ተጨባጭ ሁኔታ ከግምት ውስጥ በማስገባት መምሪያውን ተግባራዊ ያደርጉታል ተብሎ ይጠበቃል።

## የመምሪያው አደረጃጀትና ይዘት

ይህ የመምህር መምሪያ ከላይ እንደተገለፀው የተማሪ መጽሐፍን በመንተራስ የተዘጋጀ በመሆኑ የይዘት አደረጃጀቱም ይህንኑ የተከተለ ነው። ስለሆነም በተማሪ መጽሐፍ ውስጥ የተቀመጡት ምዕራፎች በቅደም ተከተል ቀርበውበታል። በየምዕራፉ ለሚከናወኑ የማዳመጥ ተግባራት የተዘጋጁት ምንባቦችም በመምህር መምሪያው ተካተዋል። አስፈላጊ ይሆናሉ ተብለው በታሰቡ ይዘቶች ላይም ተጨማሪ ማስታወሻዎች የተሰጡ ሲሆን፣ በየደረጃው ለቀረቡ መልመጃዎችም ናሙና መልሶች እንዲካተቱ ሆኗል። እነዚህ ናሙና መልሶች የቀረቡትም በትምህርቱ አሰጣጥ ወቅት ወጥነት ያለው አካሄድ እንዲኖር ታስቦ ሲሆን፣ መምህራንና ተማሪዎቻቸው እንደየሁኔታው (አውዱ) የሚያቀርቧቸው ተጨማሪ ምላሾችም ከግምት የሚገቡ ናቸው።

## ልዩ ትኩረት ሊሰጥባቸው የሚገቡ ነጥቦች

- የየትኛውም ክፍለ ጊዜ ትምህርት ሲቀርብ አራቱን የቋንቋ መሠረታዊ ክሂሎች በተመጣጠነና በተቀናጀ መልኩ ያካተተ ሊሆን ይገባል፤
- የትምህርቱ አቀራረብ አሳታፊ፣ ትብብራዊ እና ተግባቦታዊ የማስተማር ዘዴ መርህን የተከተለ ሊሆን ይገባል (ለምሳሌ ተማሪን ማዕከል ያደረገ መሆን)፤
- የልሥራ፣ እንሥራ፣ ሥሩ አካሄድ ሁልጊዜም ይተግበር፤ በተለይ አዲስ ርዕሰ ጉዳይ እና መልመጃ ሲቀርብ ተግባራዊ ሊሆን ይገባል፤
- ሁሉም ተማሪዎች ከተመሳሳይ ዳራ ያልመጡ ወይም ተመሳሳይ ልምድ የሌላቸው ስለሚሆን በመማር ወቅት የሚቸገሩ ተማሪዎችን ቀስ በቀስ የማብቃት ስልትን (scaffolding) በመተግበር ማገዝ ያስፈልጋል፤

- ልዩ ተሰጥዖ ያላቸው ተማሪዎችና ላቅ ያለ አፈፃፀም የሚያሳዩ ተማሪዎች ሲያጋጥሙንም ችሎታዎቻቸውን ለማዝለቅ ማበረታትና ተጨማሪ ተግባራትን እያዘጋጀን በመምጣት ማትጋት ይገባል፤
- በክፍል ተሳትፎ ወቅት ጥንቃቄ የተሞላበት አካሄድን መከተል ይገባል (የባህል፣ የሀይማኖት፣ የፆታ ወዘተ አካታችነትን ከግምት ማስገባት)
- ተማሪዎቹ በሚማሩበት አካባቢ በሌላ መልኩ የሚተረጎም ቃል ወይም አገላለፅ ወይም ምስል ሲያጋጥም (ታቡ የሆነ) በሌላ መተካት/ማለዘብ
- ልዩ ድጋፍ ለሚያስፈልጋቸው የአካቶ ትምህርትን መርህ በመከተል ተገቢ እገዛ ሊያደርጉላቸው ይገባል፡፡

# ምዕራፍ አንድ
# ልብሶች

(18 ክፍለ ጊዜ)

## 1. የሚጠበቁ ውጤቶች

**ከዚህ ምዕራፍ ትምህርት በኋላ ተማሪዎች**

- የማዳመጥ ግብአቱን አዳምጠው አጠቃላይ መልእክት ይለያሉ።
- ምንባብን አንብቦ ዋና መልእክትን ይለያሉ።
- ለተዘውታሪ ቃላት ፍች ይሰጣሉ።
- ባለ ሶስት ቀለም ቃላትን ይነጣጥላሉ፤ያጣምራሉ።
- የፊደል ድምጽግንኙነትን ይጽፋሉ።

## 2. ዝርዝር ይዘቶች

- ማዳመጥና መናገር
- ድምጻዊ ግንዛቤ
- የትዕምርተ ድምጽ ግንዛቤ
- የቃላት ጥናት ተዘውታሪ ቃላት(የትምህርት ቃላት)
- ማንበብና መጻፍ
- ማንበብ፡ ትክክለኛነት፣ በፍጥነት፣ በመግለጽ፣ በመረዳት
- መጻፍ፡ ድምጸትን በትክክል መረዳት

### 3. የማስተማሪያ ብልሀቶችና መሳሪያዎች

መምህር ስለሚደመጠው ጉዳይ ቁንጽል መረጃዎችን መናገር። ጥቂት ጥያቄዎችን በሰሌዳ ላይ መጻፍ። ከዚያም ተማሪዎች እያዳመጡ መመለስ። መምህር ስለርእሰ ጉዳዩ መረጃዎችን መናገር። በተለመዱ ቃላት ላይ መወያየት፤ መምህር የሚደመጠውን ምንባብ ድምጽ ከፍ አድርጎ ማንበብ። በተማሪው መማሪያ መጽሀፍ ላይ ያሉትን አንብቦ የመረዳት ጥያቄዎች ማሰራት።

**መነጠልና ማጣመር፡** ተማሪዎች ቃላትን በፍጥነት መጥራት። (በዚህ ጊዜ መምህር ማጣመርን ለማሳየት ድምጾችን ያዋህዳል) እና መነጠልን ለማሳየት ቀለሞችን ወይም ድምጾችን በተከታታይ መነጠል። ተማሪዎች ቃላትን ወደ ሁለት ቀለሞችና ድምጾች

ነጥለው ማጣመር።

**ማተካካት፡**

ሀ. መግደፍ -- ተማሪዎች ቃላትን አዳምጠው በመነሻ ላይ ያለውን ቀለም/ድምጽ በመግደፍ ማንበብ።

ለ. መጨመር -- ተማሪዎች ቃላት ሲጠሩ አዳምጠው በቃላቱ ላይ ቀለሞችን ፣ድምጾችን መጨመር።

ሐ. ተማሪዎች ቃላት ሲነገሩ አዳምጠው በቃላት ውስጥ ያሉትን ቀለሞች ወይም ድምጾች በሌሎች መተካት። (/የድምጾችን/የፊደላትን ቅርጽ፣የባለቀለም ወረቀት ፣የካርቱን ስዕሎች ፣የቃላት ካርድ፣ ስሌዳ መጠቀም)

**ተዘውታሪ ቃላት፡** የተማሪዎች ልምድ በከፍተኛ ደረጃ የሚደጋገሙ ቃላትን በምንባብ ውስጥ እንዲለዩ ያደርጋቸዋል። በምንባብ ውስጥም ውጪም ወዲያውኑ መለየት።

**በቃል መጻፍ፡** በመምህራን የሚነበብላቸውን ቃላት ተማሪዎች በትክክል ይጽፋሉ። ተማሪ ቃሉን ያዳምጣል ከዚያም ለመጻፍ መሞከር።

**የግድግዳ ላይ ቃል፡** መምህር መነሻ እንዲሆነው ቃላትን ጽፎ በግድግዳ ላይ መለጠፍ። ተማሪ በግድግዳ ላይ የተለጣጠፉትን ቃላት የፍቻቸውን ውህደት ይመለከታል።

**ተደጋጋሚ ቃላዊ ንባብ፡** ይህ ተደጋጋሚ ቃላዊ ንባብ በማቅረብ ከጓደኛ፣ ከመምህራንና ከቤተሰብ ምላሽ ማግኘት።

**በጊዜ ተገደበ ተደጋጋሚ ንባብ፡** ተማሪዎች አጭር ምንባብን ብዙ ጊዜ ያነባሉ።እያንዳንዱን ንባብም በጊዜ ይገድባል።የንባብ ፍጥነትንም ለውጡን በቻርት ማስቀመጥ።

**አረፍተ ነገርን ደጋግሞ ማንበብ፡** አንድ አረፍተ ነገር ብዙ ጊዜ ማንበብ። በእያንዳንዱ ጊዜ ለተለየው ቃል ትኩረት መስጠት።

**የፊደል -ድምጽ ግንኙነት፣ቃላት፣አረፍተ ነገሮች**

**ለምልክቶች ትኩረት መስጠት፡** አገላለጽን ለማሻሻል መምህር በግልጽ ስርዐተ ነጥብ አላማ በመግለጽ እንዴት እነዚህ ምልክቶች በአገላለጽና በድምጸት ላይ ተጸእኖ እንደሚደርጉ ማብራራት።መምህር ተማሪዎችን በቡድን ማስቀመጥ። ስርዓተ ነጥቦችን(አራት ነጥብ፣ የጥያቄ ምልክት፣) ያልያዘ አጭር ምንባብ ለተማሪዎች መስጠት፤ ተማሪዎች ተራ በተራ ድምጻቸውን ከፍ አድርገው ማንበብ። ከዚያም መምህር ተማሪዎች ያለ ስርዓተ ነጥበ ማንበብ ቀላል ወይም ከባድ መሆኑን መጠየቅ። (ይሄ ለምን ሆነ? ምን ማለት እንችላለን? የስርዓተ ነጥብ አገልግሎት ነው ማለት እንችላለን? እንዴት ይረዳናል?) ከዚያም ተማሪዎች

አራት ነጥብ በሚገባበት ቦታ ከጓደኞቻቸው ጋር ይረዳዳሉ።

## ክፍለጊዜ አንድ

## ትምህርት አንድ፡ ማዳመጥ

### የልብስ ዓይነቶች

ወደ ማንበብ ወይም ወደማስደመጥ ተግባር ከመግባትዎ በፊት የተማሪዎችዎን የቀደመ እውቀት መቀስቀስ እንደሚያስፈልግ አይዘንጉ። ለዚህም ከዚህ በታች የቀረቡትንና ተመሳሳይ ቀስቃሽ ጥያቄዎችን አዘጋጅተው ይጠይቋቸው። ጥያቄዎቹን በቃል መመለስ እንዳለባቸው ግልጽ መመሪያ ይስጧቸው።

1. ምን ምን የልብስ አይነቶችን ታውቃላችሁ?
2. በስእሉ ላይ የምታይዋቸው ምን አይነት ልብሶች ናቸው?

የተማሪዎችዎን ግምት ከተቀበሉና ካደነቁላቸው በኋላ የምንባቡን መልእክት ለመረዳት በጥሞና ማዳመጥ እንዳለባቸው ያሳስቧቸው።

መምህር ምንባቡን ሶስት ጊዜ ያነብቡላቸው። የመጀመሪያው ንባብ ተማሪዎቹ የሚያዳምጡትን ሀሳብ ለመገንዘብ በፀጥታ የሚዳምጡበት ነው። ለሁለተኛ ጊዜ ሲነበብላቸው ለማዳመጥ ጊዜ ጥያቄዎች መልስ እንዲያስሱ ምቹ ሁኔታን ይፈጥርላቸዋል። ለሶስተኛ ጊዜ ሲነበብላቸው መልሶቻቸውን የሚያረጋግጡበት ይሆናል። በሚያነቡበት ጊዜ *** ምልክት ባለበት የቀረበውን ጥያቄ ይጠይቋቸው። ጥያቄው ከአዳመጡት በመነሳት ቀጣዩን እንዲገምቱ ይረዳቸዋል።

ልብሶች የተለያዩ ቀለማት አላቸው። ነጭ፤ ጥቁር፤ ቀይ፤ አረንጓዴ፣ ሰማያዊ ሊሆኑ ይችላሉ። እነዚህ ልብሶች በሁለት ሊከፈሉ ይችላሉ።

*** ክፍፍሎቹ ምን ምን የሚሆኑ ይመስላችኋል**

አንደኛው የባህል ልብስ ነው። ለምሳሌ ከባህል ልብሶች ቡሉኮ፣ ቀሚስ፣ ጋቢ፣ ነጠላ ሊጠቀሱ ይችላሉ። ሌላው፣ ዘመናዊ ልብስ ነው። ከዘመናዊ ለምሳሌ ኮት፣ ሱሪ፣ ሸሚዝና ሹራብ ይጠቀሳሉ።

መምህር ምንባቡን ካነበቡላቸው ወይም የማዳመጥ ግብአቱን ካቀረቡላቸው በኋላ

የተማሪዎቹን አዳምጦ መረዳት ለመፈተሽ የሚከተሉትን ጥያቄዎች ይጠይቋቸው።

**በአዳመጡት መሰረት በቃል መልስ እንዲሰጡ ያድርጓቸው።**

1. ከባህላዊ ልብሶች የትኞቹን ታውቃላችሁ?
2. ዘመናዊ ልብሶች የሚባሉት ምን ምን ናቸው?
3. ካዳመጣችሁት ምን ተረዳችሁ?

## ክፍለጊዜ ሁለት

መምህር በክፍለጊዜ አንድ ስለ ባህላዊና ዘመናዊ ልብሶች እንዳነበቡላቸው ያስታውሷቸው። በእለቱ ደግሞ ስለልብስ ቀለማት እንደሚያዳምጡ ይንገሯቸው። በመቀጠል በክፍለጊዜ ሁለት ስር የቀረቡትን ምስሎች እንዲመለከቱ ያድርጉ። ከተመለከቱት ምን እንደተረዱ ይጠይቋቸው።መልሳቸውን ከተቀበሉ በኋላ የሚከተለውን ያንብቡላቸው ወይም የማዳመጡን ግብአት ያቅርቡላቸው።

ልብሶች የተለያየ ቀለም ሊኖራቸው ይችላል። ለምሳሌ፡- ሰማያዊ፣ ነጭ፣ አረንጓዴ (ቅጠልያ)፣ ቀይ፣ ቢጫ ሊሆኑ ይችላሉ። እንደቀለማቱ መለያየት የሰዎች የቀለም ምርጫም ይለያያል። አንዳንድ ሰው የሚወደውን ሌላ ሰው ላይወደው ይችላል።

ልብስ ለተለያዩ አገልግሎቶችም ይውላል። ለምሳሌ የደንብ ልብስ፣ የዘወትር ልብስ ወይም ለበአል የሚለበስ ሆኖ ሊያገለግል ይችላል።

መምህር ተማሪዎች ከምንባቡ ባገኙት ሀሳብ መሰረት የሚከተሉትን ባዶቦታዎች እንዲሞሉ ያድርጉ።

1. ልብሶች የተለያየ ________ ሊኖራቸው ይችላል።
2. የተለያዩ ሰዎች የተለያየ የ________ ምርጫ አላቸው።

## ክፍለጊዜ ሶስት

## ትምህርት ሁለት፡ መናገር

መምህር ተማሪዎች በመማሪያ መጽሀፍ በክፍለጊዜ ሶስት ስር የቀረቡትን ምስሎች እንዲመለከቱ ያድርጉ። ከምስሎቹ በመነሳት፡

- ስለምስሎቹ መመሳሰልና መለያየት፣
- ስለሚያስተላልፉት መልእክት፣

- በደንብ ልብስና በዘወትር ልብስ መካከል ስላለ ልዩነት በየተራ ሀሳብ እንዲሰጡ በማድረግ መናገር እንዲለማመዱ ያድርጓቸው።

በተጨማሪም ቀጥሎ ላሉት ጥያቄዎች በቃል መልስ እንዲሰጡ ያድርጉ።

1. በአካባቢያችሁ ብዙ ጊዜ ምን አይነት ልብሶች ይለበሳሉ?
2. የራሳችሁን ልብስ ተመልከቱ። ዘመናዊ ወይስ ባህላዊ ነው?

## ክፍለጊዜ አራት

መምህር ተማሪዎችዎ በክፍለጊዜ አራት ስር የቀረበውን ምስል በደንብ እንዲመለከቱና የተገነዘቡትን በቃል ለክፍል ተማሪዎች ለማቅረብ እንዲዘጋጁ ያበረታቷቸው። የተዘጋጁበትንም በየተራ እንዲያቀርቡ ያመቻቹላቸው።

በተጨማሪ በሚቀጥሉት ጥያቄዎች መነሻነት የየግል የልብስ አይነትና ቀለም ምርጫቸውን እንዲናገሩ ያድርጉ። በዚህም ተግባር ንግግር መለማመዳቸውን ከአቀራረባቸው ይፈትሹ። አስፈለጊውን ድጋፍም ያድርጉላቸው።

1. ለበዓል መልበስ የሚያስደስታችሁ የልብስ አይነት የቱ ነው? ለምን?
2. የምትለብሱት ልብስ ቀለም ምን ቢሆን ያስደስታችኋል?

## ክፍለጊዜ አምስት

## ትምህርት ሶስት፡ መነጠልና ማጣመር

### ሀ. መነጠል

መምህር ተማሪዎችዎ በምስል ተወክለው የቀረቡትን ቃላት በምሰሌው መሰረት ነጣጥለው መጥራት እንዲችሉ ነጥለው በመጥራት ያሳይዋቸው። እያንዳንዳቸውን ሲጠሩ በጭብጨባ በማጀብ መነጠላቸውን እንዲረዱ ያድርጉ። በተመሳሳይ መንገድ የተሰጡ ባለሁለት ፊደል ቃላትን ለእያንዳንዱ ፊደል አንድ አንድ ጊዜ በማጨብጨብ ነጥለው ማሳየት መቻላቸውን ይከታተሉ።

መምህር ይኸን ተግባር ለማለማመድ የተጣመረውን ቃል ምሳሌ “ወሰደ” ከጠሩ በኋላ ወ-ሰ-ደ ወደሚለው እያንዳንዱን ከጭብጨባ ጋር እየጠሩ ነጥለው ያሳይዋቸው። በመቀጠል የሚሰጡትን ምሳሌ ከተማሪዎችዎ ጋር በጋራ ይስሩት። በጋራ ደጋግመው ከሰሩ እና ከአሰሩ

በኋላ ተማሪዎችዎ በመማሪያ መጽሃፉ ላይ የቀረቡትን ቃላት በምሳሌው መሰረት ነጥለው እንዲጠሩ ያድርጉ።

እያንዳንዳቸው ቃላቱን መነጠል መቻላቸውን በግል ሰርተው እንዲያሳዩ በማድረግ ያረጋግጡ።

## ክፍለጊዜ ስድስት

## ለ. ማጣመር

መምህር ተማሪዎችዎ ተነጣጥለው የሚነገራቸውን ፊደላት በፍጥነት አጣምረው ቃላት መናገር እንዲችሉ ያለማምዱቸው። በመጀመሪያ በቂ ምሳሌ ይስጧው። ምሳሌ ሲሰጧቸው በጥሞና እንዲከታተሉ ያድርጉ። በመቀጠል ምሳሌዎቹን ከእርስዎ ጋር በጋራ ደጋግመው እንዲሰሩ ያድርጉ። እርስዎ ነጥለው የጠሩላቸውን በህብረት ቃሉን እንዲጠሩ ያድርጉ። ቃሉን ሲጠሩ አንዴ ብቻ በማጨብጨብ መጣመሩን እንዲገነዘቡ ያድርጉ።

በመጨረሻም በጋራ የሰሩትን በተናጠል መስራት መቻላቸውን ተማሪዎችን በየተራ በማሳተፍ ትምህርቱን ይመዝኑ። አስፈላጊ ድጋፍ በመስጠት ትምህርቱን ያጠናክሩ።

## ክፍለጊዜ ሰባት

መምህር፣ ተማሪዎችዎ በክፍለ ጊዜ ሰባት ተነጣጥለው የቀረቡትን እንዲያጣምሩ ምሳሌ በመስጠት ያለማምዱቸው። ከዚያ ከተማሪዎችዎ ጋር በጋራ ይስሩ። በተመሳሳይ መንገድ መማሪያ መጽሐፍ ላይ የቀረቡትን ድምጽ በማሰማት እያጨበጨቡ እንዲያጣምሩ ያበረታቷቸው። ትክክለኝነቱን በመከታተል ያበረታቷቸው። በዚህም ተግባር በፍጥነት አጣምረው ቃላት መናገር እንዲችሉ ያለማምዱቸው። በመጨረሻም በጋራ የሰሩትን በተናጠል መስራት መቻላቸውን በየተራ በማሳተፍ ያረጋግጡ።

## ክፍለጊዜ ስምንት

## ትምህርት አራት፡ የቃላት ጥናት

### ሀ. ከመነሻ የጎደሉ ፊደላትን ማሟላት።

መምህር፣ ተማሪዎችዎ ከመነሻ የጎደሉትን ፊደላት በማሟላት ቃል መመስረት እንዲችሉ የቀረበውን ምሳሌና ሌሎች ተጨማሪ ምሳሌዎችን በመጠቀም ባዶ ቦታ መሙላት እንዲችሉ ያለማምዱቸው። ምሳሌ፡ "__ ለጠ" በሚለው ውስጥ ባለው በባዶ ቦታ ላይ "በ"፣ "ፈ"፣ "ገ"፣ "መ" ቢሞሉ = <u>በ</u>ለጠ <u>ፈ</u>ለጠ <u>ገ</u>ለጠ <u>መ</u>ለጠ የሚሉ ቃላት ሊገኙ

እንደሚችሉ ሰርተው ያሳይዋቸው። እርስዎ ሲሰሩ በደንብ እንዲከታተሉ ያድርጉ። በመቀጠል ሲከታተሉ የቆዩትን ከእርስዎ ጋር በህብረት እንዲሉ ያድርጉ። አያይዘውም መጽሐፋቸውን ክፍለጊዜ ስምንትን እንዲያወጡ ይንገሯቸው። ቃላቱን ወደ ደብተራቸው እንዲገለብጡና ማሚያዎቹን እንዲፈልጉ ጊዜ ይስጧቸው። ተማሪዎቹ የጎደሉትን የማሟላት ተግባር ሲከውኑ ይከታተሏቸው። አስፈላጊ ድጋፍም ይስጧቸው። በመጨረሻም እያንዳንዳቸው አንድ ባንድ ያገኙትን ማሚያ እንዲናገሩ ያድርጉ። ከተለያዩ ተማሪዎች የሚገኙ የተለያዩ ማሚያዎችን በመጨመር የቀረቡትን ቃላት ሰሌዳ ላይ ይፃፉላቸው።

*(ማስታወሻ፡ አንድ ቃል ካንድ በላይ ማሚያ ሊኖረው እንደሚችል ታሳቢ ይደረግ)*

## ክፍለጊዜ ዘጠኝ

### ለ. ከመድረሻ የጎደሉ ፊደላትን ማሟላት።

መምህር ተማሪዎችዎ ከመድረሻ የጎደሉትን ፊደላት በማሟላት ቃል መመስረት እንዲችሉ የቀረበውን ምሳሌና ሌሎች ተጨማሪ ምሳሌዎችን በመጠቀም ባዶ ቦታ መሙላት እንዲችሉ ያለማምዱቸው። ምሳሌ፡ አጠ__ = አጠበ አጠፈ አጠረ አጠና አጠራ፣ ከልምምድ በኋላ ክፍለጊዜ ዘጠኝ እንዲያወጡ ይንገሯቸው። ቃላቱን ወደ ደብተራቸው እንዲገለብጡና ማሚያዎቹን እንዲፈልጉ ጊዜ ይስጧቸው። ተማሪዎቹ የጎደሉትን የማሟላት ተግባር ሲከውኑ ይከታተሏቸው። አስፈላጊ ድጋፍም ይስጧቸው። በመጨረሻም እያንዳንዳቸው አንድ ባንድ ያገኙትን ማሚያ እንዲናገሩ ያድርጉ። አስፈላጊውን ማስተካከያ በመስጠት ያበረታቷቸው።

## ክፍለጊዜ አስር

### ሐ. ከመሃል የጎደሉ ፊደላትን ማሟላት።

መምህር ተማሪዎችዎ ከመሃል የጎደሉትን ፊደላት በመሟለት ቃል መመስረት እንዲችሉ የቀረበውን ምሳሌና ሌሎች ተጨማሪ ምሳሌዎችን በመጠቀም ባዶ ቦታ መሙላት እንዲችሉ ያለማምዱቸው። ምሳሌ፡ "ሰ__ ዳ" በሚለው ውስጥ ባለው ባዶ ቦታ ላይ "ሌ"፣ ቢሞላ = ሰሌዳ የሚል ቃል ሊገኝ እንደሚችል ሰርተው ያሳይዋቸው። እርስዎ ሲሰሩ በደንብ እንዲከታተሉ ያድርጉ። በመቀጠል ሲከታተሉ የቆዩትን ከእርስዎ ጋር በህብረት እንዲሉ ያድርጉ። በመቀጠልም መጽሐፋቸውን ክፍለጊዜ አስር እንዲያወጡ ይንገሯቸው። ቃላቱን ወደ ደብተራቸው እንዲገለብጡና ማሚያዎቹን

*እንዲፈልጉ ጊዜ ይስጧቸው።*

*ተማሪዎቹ የጎደሉትን የማሟላት ተግባር ሲከውኑ ይከታተሏቸው። አስፈላጊ ድጋፍም ይስጧቸው።*

*በመጨረሻም እያንዳንዳቸው አንድ ባንድ ያገኙትን ማሟያ እንዲናገሩ ያድርጉ። ከተለያዩ ተማሪዎች የሚገኙ የተለያዩ ማሟያዎችን በመጨመር የቀረቡትን ቃላት ሰሌዳ ላይ ይፃፉላቸው።*

### ክፍለጊዜ አስራ አንድ

# ትምህርት አምስት፡ ማንበብ

## የአሚና ልብስ

*መምህር የምንባቡን ርዕስ (**የአሚና ልብስ**) በጥቁር ሰሌዳ ላይ ይጻፉና ተማሪዎች ድምጽ እያሰሙ እንዲያነቡ ያድርጉ። በመቀጠልም በመማሪያ መጽሃፉ ላይ የቀረበውን ምስል እንዲመለከቱ ይምሯቸው። ቀጥሎ የቀረቡትን ቅድመንባብ ጥያቄዎችን ይጠይቁ። እንዳስፈላጊነቱ ሌሎች ለቅድመንባብ የሚሆኑና ከተማሪዎችዎ ልምድ ጋር የሚሄዱ ጥያቄዎችን አዘጋጅተው መጠየቅ ይችላሉ።*

1. *ከምስሉ ምን አያችሁ?*
2. *ስለአሚና ልብስ ምን የምታነቡ ይመስላችኋል?*

*ከልምድ በመነሳት የሚሰጡትን መልስ ይቀበሉ። በማያያዝ የሰጡትን ግምታዊ መልስ ለማረጋገጥ በጥሞና ማንበብ እንዳለባቸው ያሳስቧቸው።*

### ክፍለጊዜ አስራ ሁለት

### *የአንብቦ መረዳት*

*መምህር ተማሪዎቹ ባነበቡት መሰረት ለተቀመጠው ባዶ ቦታ ማሟያ የሚሆኑ ከተሰጡት ቃላት ውስጥ መምረጥ እንዲችሉ ጊዜ ይስጧቸው። ለሁሉም ባዶ ቦታዎች መልስ መፈለጋቸውን ከአረጋገጡ በኋላ ለእያንዳንዱ ባዶ ቦታ የተለያዩ ተማሪዎችን በማሳተፍ መልስ ይቀበሉ። ተማሪዎችን ሲያሳትፉ በመጀመሪያ ተሳታፊ ተማሪ ትክክለኛ መልስ ቢቀርብ እንኳን ሌላ ሊሉ የሚችሉ ተማሪዎች ሊኖሩ ስለሚችሉ ለሌላ መልስ እድል ይስጡ። የሚቀርቡትን መልሶች በሙሉ ሰሌዳ ላይ ይጻፉ። ከተማሪዎች የተለየ መልስ*

የሚሰጡ አለመኖራቸውን እጅ መውጣት በመቆሙ ካረጋገጡ በኋላ ትክክለኛውን መልስ ያረጋግጡላቸው። ከዚያ በኋላ በመልስነት ቀርበው መልስ ያልሆኑትን ከሰሌዳ ላይ በመጽዳት ወደ ቀጣይ ባዶ ቦታ ማስሞላት ይሸጋገሩ።

በተመሳሳይ መንገድ አምስቱንም ባዶ ቦታ ካስሞሉ በኋላ የተሟለውን ወደ ደብተራቸው እንዲገለብጡ ያድርጉ።

## ክፍለጊዜ አስራ ሶስት

**መምህር** ተደጋጋሚ ቃላዊ ንባብ (ድምጽን ከፍ አድርጎ ማንበብ) በማቅረብ ከጓደኛ፣ ከመምህራንና ከቤተሰብ ምላሽ ማግኘት የሚችሉበትና የማንበብ ችሎታቸውን የሚያሻሽሉበት ተግባር ነው። ለቃላዊ ንባብ የቀረቡትን ቃላትና አጭር ጽሁፍ ተማሪዎች ድምጻቸውን ከፍ አድርገው እንዲያነቡ ያድርጉ። ተረኛ ሲያነብ ሌሎቹ መጽሐፋቸውን ይዘው እንዲከታተሉ ያሳስቡ።

ተማሪዎች በሚያነቡበት ጊዜ የሚፈጥሩትን ስህተት በማረም ንባባቸውን ለማሻሻል በተደጋጋሚ ማንበብ እንዳለባቸውና ለሰሩት መልካም ስራ የማትጊያ ቃላትን በመጠቀም ያበረታቷቸው። በሚያነቡት ላይ ከጓደኛ፣ ከመምህራንና ከቤተሰብ ምላሽ ማግኘት እንደሚችሉ ያሳውቁ። በዚህም ንባባቸውን ማሻሻል እንደሚችሉ ያሳስቡ። በዚሁ መሰረት ቀጣዮቹን እንዲሰሩ ያድርጓቸው።

ሀ. በመማሪያ መጽሐፍ በክፍለጊዜ አስራ ሶስት ስር የቀረቡትን ቃላት ተማሪዎች ድምጻቸውን ከፍ አድርገው በተደጋጋሚ በየተራ ተነስተው በትክክል እንዲያነቡ ያድርጉ። በዚህ ሂደት ውስጥ ለድምጾችና ምልክቶች ተገቢውን ትኩረት ሰጥተው በትክክል ማንበባቸውን ይከታተሉ። ተገቢውን ድጋፍም ይስጧቸው።

## ክፍለጊዜ አስራ አራት

ለ. በመማሪያ መጽሐፍ በክፍለጊዜ አስራ አራት ስር የቀረቡትን ቃላዊ የአረፍተነገር ንባብ ተማሪዎች ድምጻቸውን ከፍ አድርገው በተደጋጋሚ በየተራ ተነስተው በትክክል እንዲያነቡ ያድርጉ። በዚህ ሂደት ውስጥ ለቃላት፣ ቅላጼና ምልክቶች ተገቢውን ትኩረት ሰጥተው በትክክል ማንበባቸውን ይከታተሉ። ተገቢውን ድጋፍም ይስጧቸው።

## ክፍለጊዜ አስራ አምስት

**በጊዜ የተገደበ ተደጋጋሚ ንባብ፡**ተማሪዎች አጭር ምንባብን ብዙ ጊዜ ያነባሉ።እያንዳንዱን

ንባብም በጊዜ ይገደባል። የንባብ ፍጥነትንም ለውጡን በቻርት ማስቀመጥና የታየውን መሻሻል ለማየት መረጃ በሩብሪክስ ወይም በቼክ ሊስት መያዝ ይገባል ።

መምህር ለቃላዊ ንባብ የቀረበውን አጭር ጽሁፍ ተማሪዎች ድምጻቸውን ከፍ አድርገው በየተራ እንዲያነቡ ያድርጉ። ተረኛ ሲያነብ ሌሎቹ መጽሐፋቸውን ይዘው እንዲከታተሉ ያሳስቡ። እንደ ጽሁፉ ስፋት ከአንድ ደቂቃ ባልበለጠ ጊዜ ውስጥ ተማሪዎችዎ በፍጥነትና በትክክል ማንበባቸውን ከላይ በተጠቀሰው መሰረት በመከታተል መረጃ ይያዙ። በተያዘ መረጃ መሰረት እንደየ ብቃታቸው አስፈላጊውን ድጋፍ በመስጠት የማንበብ ፍላጎት እንዲያድርባቸው ያድርጉ። በዚህ ሂደት ውስጥ ስንት ቃላትን እንዳነበቡና ከተነበበው ውስጥ ምን ያህሉን በትክክል እንዳነበቡ በመለየት መረጃዎችን ይያዙ። በያዙት መረጃ ላይ በመመስረት እንደ ልዩነታቸው አስፈላጊውን ድጋፍ ሊያደርጉላቸው ይገባል።

ተማሪዎች በሚያነቡበት ጊዜ የሚፈጥሩትን ስህተት በማረም ንባባቸውን ለማሻሻል በተደጋጋሚ ማንበብ እንዳለባቸውና ለሰሩት የተሻለ ስራ የማትጊያ ቃላትን በመጠቀም ያበረታቷቸው። በሚያነቡት ላይ ከጓደኛ፣ ከመምህራንና ከቤተሰብ ምላሽ ማግኘት እንደሚችሉ ያሳውቋቸው። በዚህም ንባባቸውን ማሻሻል እንደሚችሉ ያስረዷቸው።

## ክፍለጊዜ አስራ ስድስት

## ቃላትን ከስእሎቹ ጋር ማዛመድ

መምህር ተማሪዎችዎ የልብስ ስም አንብበው ቁጥሩን ከፊደላት ጋር እንዲያዛምዱ በምሳሌ ያሳዩዋቸው። አለበለዚያ ሰንጠረዡን ወደ ደብተራቸው እንዲገለብጡና በስእሎቹ ምትክ የምስሎቹን ስም ከነቅደም ተከተል ማስያዣ ፊደላት እንዲጽፉ ማድረግ። የጻፉትን በመስመር በማገናኘት እንዲያዛምዱ ያድርጉ። ወይም ምቹ ሁኔታ ካለ ቃላትና ስእሎቹን በተለያየ ፍላሽ ካርድ ላይ በማንሳት እንዲያዛምዱ ያድርጉ። ለዚህ ተግባር ሻሽ ቦርድ፣ የተለያየ ቀለም ያላቸውን ወረቀቶች መጠቀም ሂደቱን ምቹና ሳቢ ያደርገዋል።

## ክፍለጊዜ አስራ ሰባት

# ትምህርት ስድስት፡ መፃፍ

**ለምልክቶች ትኩረት መስጠት፡** አገላለጽን ለማሻሻል መምህር በግልጽ ስለስርዐተ ነጥብ አላማ በመግለጽ እንዴት (። እና ?) እነዚህ ምልክቶች በአገላለጽና በድምጸት ላይ ተጽእኖ እንደሚደርጉ ማብራራት።

መምህር ተማሪዎችን በቡድን ያስቀምጡ። ስርዓተ ነጥቦችን (አራት ነጥብ፣ ጥያቄ ምልክት፣) ያልያዘ በመማሪያ መጽሐፍ ክፍለጊዜ አስራ ሰባት "ሀ" ስር የቀረቡትን አረፍተነገሮች ተማሪዎች ተራ በተራ ድምጻቸውን ከፍ አድርገው እንዲያነቡ ያድርጉ። ከዚያም ያለ ስርዓተ ነጥብ ማንበብ ቀላል ወይም ከባድ መሆኑን ይጠይቁ። (ይሄ ለምን ሆነ? ምን ማለት እንችላለን? የስርዓተ ነጥብ አገልግሎት ነው ማለት እንችላለን?) የሚሉና የመሳሰሉትን ይጠይቁ። ከዚያም ተማሪዎች አራት ነጥብና ጥያቄ ምልክት በሚገባበት ቦታ ከጓደኞቻቸው ጋር በመነጋገር እንዲያስገቡ ያድርጉ።

## ክፍለጊዜ አስራ ስምንት

**ሀ.** በተነጋገሩበት መሰረት አራት ነጥብንና ጥያቄ ምልክትን በተስማሙበት ቦታ አስገብተው ይጻፉ። ምልክቶችን ያስገቡባቸውን እንዲያነቡ ያድርጉ። በመማሪያ መጽሐፍ ክፍለጊዜ አስራ ስምንት "**ለ**" ስር ስርአተነጥብ የገባበትን እንዲያነቡና ቀድመው ካነበቡት ተመሳሳይ አረፍተነገሮች ጋር በማገናዘብ በማንበብ ላይ የገጠማቸውን ችግር ያነጻጽሩ። ያስቸገራቸው የትኛውን ሲያነቡ እንደሆነ ይናገሩ።

**ለ** ተነጋግረው በጨመሩት ምልክቶችና በመማሪያ መጽሐፉ ላይ ተጨምረው በቀረቡት ምልክቶች መካካል ልዩነት ካለ እንዲናገሩ ያድርጉ። ልዩነቱ በአነባበብ ላይ ያመጣው ለውጥም ካለ ይጠይቃቸው። ለምሳሌ "ተማሪዎቹ ተባብረው ያጠናሉ?" እና "የቤት ስራችሁን ሰርታችኋል።" ተብሎ ሊጻፍ እንደሚችል በማሳየት በአነባበብና በሚተላለፍ መልእክት ላይ ተጽእኖ ሊኖረው እንደሚችል ያስረዷቸው።

**ሐ. በቃል መጻፍ፡**መምህር ቃላትን ሲያነብ ተማሪዎች በትክክል ይጽፋሉ።ተማሪ ቃሉን ያዳምጣል ከዚያም ለመጻፍ መሞከር።

1. ሀገር 2. ተማሪ 3. ቢፍቱ 4. ብሪቱ

***(ማስታወሻ ለመምህር፡** ለተማሪዎችዎ አዲስ የሚሆኑ ቃላት ሲያጋጥሙ ወረቀት ላይ በመጻፍ በክፍሉ ግድግዳ ላይ ይለጥፉ።)*

# ምዕራፍ ሁለት

# ወቅቶች

(18 ክፍለጊዜ)

## 1. ከትምህርቱ የሚጠበቁ ውጤቶች

ከዚህ ምዕራፍ ትምህርት በኋላ ተማሪዎች፡

- የማዳመጥ ግብአቱን አዳምጠው አጠቃላይ መልእክት ይለያሉ፤
- ምንባቡን በማዳመጥ ዝርዝር ሀሳቦችን ይለያሉ፤
- በቃል የምንባቡን መልእክት ይናገራሉ፤
- ወቅቶች ከሚለው ቃል ጋር የሚቀራረቡ የቃላት ትርጎሞችን ይሰጣሉ፤
- ድምጾችን ከቃላት የመነጠልና የማጣመር (ድምጾችን/ፊደላትን ለይተው መዘርዘር) ተግባር ይፈጽማሉ።
- የሚታወቁ ባለ አራት ቀለም ቃላትን ይጽፋሉ።
- አራት ነጥብንና ጥያቄ ምልክቶችን ይለያሉ።

## 2. ዝርዝር ይዘቶች

- መናገርና ማዳመጥ
- ስነድምጻዊ ግንዛቤና ትዕምርተ ድምጻዊ ግንዛቤ
- የቃላት ጥናት ተዘውታሪ ቃላት(የትምህርት ቃላት) -የቃላት ዕውቀት ማሳደግ
- ማንበብና መጻፍ
- ማንበብ ትክክለኛነት፣ በፍጥነት፣ በመግለጽ፣ በመረዳት
- መጻፍ ድምጸትን በትክክል መረዳት

## 3. የመማር ብልሃትና መሳሪያዎች

- መምህር ስለርዕሱ የቀደመ ዕውቀታቸውን ለማነሳሳት ለተማሪዎች የተወሰኑ ቅድመንባብ ጥያቄዎችን ማቅረብ። በክፊል የተሞሉ የቢጋር ሰንጠረዦችን በማቅረብ ቀሪውን ተማሪዎች እንዲሞሉ ማድረግ። መምህር ድምጹን ከፍ አድርጎ ሲያነብ የቀረውን ተማሪዎች በቃል ባዶ ቦታውን መሙላት።
- ተማሪዎች ከወቅቶች ጋር የሚቀራረቡ ቃላትን እንዲለዩ ማድረግ። (ለምሳሌ፡ በሳምንት ውስጥ ያሉ ቀናት፣ በአመት ውስጥ ያሉትን ወራት፣ የበጋ ወቅት፣

ክረምት፣ መከር) የአከባቢውን ወቅታዊ ሁኔታ ማሰብ

- **መነጠልና ማጣመር** ፡ ተማሪዎች በቃሉ ውስጥ ያሉትን ድምጾች በመነጠል መናገር። (በፍጥነት ማስባል) በመቀጠል (መምህር መነጠልን ለማሳየት ፊደላትን ማጣመር)። ተማሪዎች ቃሉን ጠርተው በቃሉ ውስጥ ያሉትን ቀለሞችና ድምጾች በመጥራት ማጣመር።
- **ማተካካት፡** መምህር ተማሪዎች የገደፉትን ቃላት መልሶ መተካት።
  ሀ. መግደፍ ፡ ተማሪዎች ቃላትን ካዳመጡ በኋላ ድምጾችን/ቀለማትን እንደመጀመሪያው ሳይጠሩ መቀየር
  ለ. መጨመር ፡ ተማሪዎች ባዳመጡት ቃል ላይ ድምጽን/ምዕላድን መጨመር
  ሐ. መተካት፡ ተማሪዎች ካዳመጡት ቃል ሌላ ድምጽ/ምእላድ መተካት (የድምጾችን/የፊደላትን ቅርጽ፣ የባለቀለም ወረቀት፣ የካርቱን ስዕሎች፣ የቃላት ካርድ፣ ሰሌዳ ወዘተ መጠቀም)
- **ከምንባቡ ጋር ማዛመድ** ተማሪዎች ምንባቡን በማንበብ መጻፍ መለማመድ፣ የሚጻፈውም ምንባቡ ነው።
- **ተዘውታሪ ቃል፡** ተማሪዎች ከምንባቡ ውስጥና ከምንባቡ ውጭ ከፍተኛ ድግግሞሽ ያላቸውን ቃላት ፈጥነው የመለየት ልምድ ማዳበር።
- **በቃል መጻፍ** ተማሪዎች ቃላትን አዳምጠው በትክክል ለመጻፍ መሞከር።
- **የግድግዳ ላይ ቃላት** መምህር ቃላትን ጽፈው ግድግዳ ላይ በመለጠፍ እንደማጣቀሻ መጠቀም። ተማሪዎች በተራ የተዘውታሪ ቃላትን ፍቺ መግለጥ።
- **ተደጋጋሚ ቃላዊ ንባብ፡** ይህ ተደጋጋሚ ቃላዊ ንባብ በማቅረብ ከጓደኛ፣ ከመምህራንና ከቤተሰብ ምላሽ ማግኘትን ይመለከታል።
- **በጊዜ የተገደበ ተደጋጋሚ ንባብ፡** ተማሪዎች አጭር ምንባብን ብዙ ጊዜ ያነባሉ። እያንዳንዱን ንባብም በጊዜ መገደብ። የንባብ ፍጥነትንም ለውጡን በቻርት ማስቀመጥ።
- **የፊደል -ድምጽ ግንኙነት፣ቃላት፣አረፍተ ነገሮች**
- **ለምልክቶች ትኩረት መስጠት፡** አገላለጽን ለማሻሻል መምህር በግልጽ የምልክቶችን አላማ በመግለጽ እንዴት እነዚህ ምልክቶች በአገላለጽና በድምጸት ላይ ተጽእኖ እንደሚያደርጉ ያብራራል።
- መምህር ተማሪዎችን በቡድን ማስቀመጥ። ስርዓተ ነጥቦችን (አራት ነጥብ፣የጥያቄ ምልክት፣) ያልያዘ አጭር ምንባብ ለተማሪዎች ይሰጣል፤ ተማሪዎች ተራ በተራ

ድምጻቸውን ከፍ አድርገው ማንበብ። ከዚያም መምህር ተማሪዎች ያለ ስርዓተ ነጥበ ማንበብ ቀላል ወይም ከባድ መሆኑን ይጠይቃል።ይሄ ለምን ሆነ፣ምን ማለት እንችላለን የስርዓተ ነጥብ አገልግሎት ነው ማለት እንችላለን? እንዴት ? ከዚያም ተማሪዎች አራት ነጥብ በሚገባበት ቦታ ከጓደኞቻቸው ጋር ያስገባሉ።

- በቡድን መጻፍ፡መምህር አርዐያ በመሆን ተማሪዎች አንድ የጋራ ንባብ እንዲጽፉ ማበረታታት።

**4.ምዘና**

- ቃላዊ/ጽሁፋዊ ጥያቄዎችን መጠየቅ
- አካላዊ ምላሽ፡ ተማሪዎች በግላቸው በአካል እንቅስቃሴ ለጥያቄዎች የሚሰጡት ምላሽ
- ኢመደበኛ ቁጥጥር፡ ምልከታ
- በሚታይ መወከል
- ተራ በተራ ማቅረብ
- የመውጫ ካርዶች
- ጽብረቃ
- ስልታዊ ልምምድ

**ክፍለጊዜ አንድ**

# ትምህርት አንድ፡ ማዳመጥ

***መምህር***፡ በመጀመሪያ ርእሱን (የወላጆች ቀን) ሰሌዳ ላይ ይጻፉላቸው። በመቀጠል ስለወላጆች ቀን የሚያውቁትን እንዲናገሩ ይጠቁቸው። ተማሪዎች ካላቸው ልምድ ሌላ ከሚያዳምጡት ምን አዲስ ነገር እንደሚያገኙ እያሰቡ በጥሞና እንዲያዳምጡ ያሳስቧቸው። በመጨረሻም ከዳመጡት ውስጥ የሚጠየቁት እንዳለ ያሳውቋቸው። ታሪኩንም ተማሪዎችዎ ሊከታተሉ በሚችሉት ፍጥነት ያንብቡላቸው። ማንበብ ከመጀመርዎ በፊት ግን ቀጥሎ ያሉትን የቅድመማዳመጥ ጥያቄዎችን ያንብቡላቸው።

1. ምስሉላይ ምን አይነት ሰዎችን አያችሁ?
2. በትምህርት ቤታችሁ አካል ጉዳተኞች ጉዳት ከሌለባቸው ጋር አብረው መማር ያስፈልጋል ትላላችሁ?

# የወላጆች ቀን

እለቱ ቅዳሜ ነው። የነሳፊዬ ትምህርት ቤት የአመቱ የወላጆች ቀን ነው። በዚህ ምክንያት የተማሪ ወላጆች በፕሮግራሙ ላይ እንዲገኙ ጥሪ ተደርጎላቸዋል። ወቅቱ **ክረምት** በመሆኑ ስነስርአቱን **ቀልጠፍ** ማድረግ ተፈልጓል። ስለዚህ የፕሮግራሙ **አስተዋዋቂ** የሽልማት ስነስርአት የሚፈጸምበት ሰአት መድረሱን አሳውቆ ሽልማት መስጠት ተጀመረ። ከፍተኛ **ውጤት** አምጥተው ከተሸለሙ ተማሪዎች ውስጥ ሳፈዬ ቢርመጂ አንዷ ነበረች። የሳፈዬ ስም ሲጠራ የሰሙት የበለጡ እናት "የኛዋ ሳፈዬ ናት" አሉ ወደ ልጃቸው ዞረው። "አዎ! እሷ ናት። ጎበዝ መሆኗን አታውቂም እንዴ?" አለች በለጡ። ሲባል ሰምቻለሁ፤ ያንቺስ ጓደኛ አይደለች? "ግን እኮ . . ." ሲሉ በለጡ ቀበል አድርጋ፣ "አይነስውር ናት ልትዪ ነው?" አለቻቸው። "**የአካል ጉዳት** ያለባቸው እንደማንም መስራት እንደሚችሉ ያስመሰከረች ጀግና ናት። እንዲያውም አስተማሪያችን፣ 'የኛ እንቁ' ይሏታል። እኔም የጎበዝኩትና ተሸላሚ መሆን የቻልኩት ከሷ ጋር መስራት ከጀመርኩ ወዲህ ነው" አለቻቸው። በመሃሉ የበለጡም ስም ሲጠራ ንግግራቸው ተቋረጠ።

| | | |
|---|---|---|
| **የማዳመጥ ጊዜ ጥያቄ መልሶች** | | |
| 1. በወላጆች | 2. ሽልማታቸውን | 3. ሳፋዬ |
| 4. ጎበዝ | 5. መስራት | |

## ክፍለጊዜ ሁለት

## አዳምጦ መረዳት

ሀ. መምህር ተማሪዎችዎ በክፍለጊዜ ሁለት ስር የቀረበውን ምስል እንዲመለከቱ ያድርጉ። ከምስሉ ምን እንደተረዱ ይጠይቋቸው። ካዳመጡት መልእክት ጋር በማዛመድ ምንን እንደሚያሳይ እንዲናገሩ ያድርጉ።

ለ. ያዳመጡትን መሰረት አድርገው በሚከተሉት ጥያቄዎች ላይ በጥንድ እንዲወያዩ ያድርጉ። መልሳቸውን ለክፍል በቃል እንዲያቀርቡ ያመቻቹላቸው።

1. ትምህርት ቤቱ ወላጆችን ለምን ጠራ?
2. በእለቱ የተሸለሙ ተማሪዎች እነማን ናቸው?
3. ካዳመጣችሁት ውስጥ ምን ደስ አላችሁ?

## ክፍለጊዜ ሶስት

**መምህር** ተማሪዎችዎ መማሪያ መጽሐፋቸው ክፍለጊዜ ሶስት ስር የቀረቡትን ባዶ ቦታ ያለባቸውን አረፍተነገሮችና ለማሟያ በአማራጭነት የቀረቡትን ቃላት ወደደብተራቸው እንዲገለብጡ ያድርጉ። በመቀጠል ባዶ ቦታዎችን በተገቢ ቃላት እንዲያሟሉ ግልጽ መመሪያ ይስጧቸው።

በግል የሰጡትን መልስ በጥንድ እንዲያስተያዩና በትክክለኝነቱ ላይ እንዲወያዩ ይደረግ። በመጨረሻም ከተወሰኑ ተማሪዎች መልስ በመቀበልና የተሰጡትን መልሶች ሰሌዳ ላይ በመጻፍ ትክክለኛውን ቃል እንዲገነዘቡ ያድርጉ።

## ክፍለጊዜ አራት

## ትምህርት ሁለት፡ መናገር

### መልመጃ አንድ

ሀ. መምህር ተማሪዎቹ በመማሪያ መጽሐፋቸው ላይ የቀረበውን ምስል እንዲመለከቱ ያድርጉ። ከምስሉ የተረዱትን ሃሳብ ተራ በተራ እንዲናገሩ በማድረግ የንግግር ልምምድ እንዲያደርጉ ያመቻቹላቸው። የሀሳባቸውን የተቀናጀ መሆን፣ ራሳቸውን ለመግለጽ ያላቸውን ብቃትና የመሳሰሉትን በመመዘን ተገቢውን ድጋፍ ያድርጉላቸው።

ለ. ካዳመጡት ጋር በማያያዝ ቀጥሎ ላሉት ጥያቄዎች በንግግር መልስ እንዲሰጡ በማድረግ የንግግር ችሎታ እንዲለማመዱ በማድረግ እንደተማሪዎቹ ጥንካሬና ድክመት ተገቢ የማበረታቻና ማሻሻያ ሀሳብ በመስጠት እንዲለማመዱ ይርዷቸው።

1. ባዳመጣችሁት ታሪክ ውስጥ ያለችውን፣ ሳፋዬን፣ ታደንቀላችሁ? ለምን?
2. ጎበዝ መሆን ትፈልጋላችሁ? ለምን?
3. ከአዳመጣችሁት ታሪክ ምን ሃሳብ አገኛችሁ (ምን ተረዳችሁ)?

## ክፍለጊዜ አምስት

### መልመጃ ሁለት

መምህር ያለፈውን እሁድ ቀን ምን በመስራት እንዳሳለፉ ለክፍል ተማሪዎች እንዲናገሩ በማድረግ ንግግር እንዲለማመዱ ተራ በተራ ያሳትፏቸው። ተማሪዎቹ በግል የሚናገሩትን እንዲያስታውሱና ለመናገር ዝግጁ እንዲሆኑ የማሰቢያ ጊዜ ይስጧቸው። ካሰቡበት በኋላ

ተራበተራ የራሳቸውን ሀሳብ እንዲገልጹ የተቀሩት እንዲያዳምጡ በማድረግ የመናገር

ሂደቱን ያመቻቹ። በክፍል ውስጥ የተናጋሪን ሀሳብ የሚሰርቁ ነገሮች እንዳይደረጉ ጥንቃቄ ይወሰድ።

## ክፍለጊዜ ስድስት

## ትምህርት ሶስት፡ መነጠልና ማጣመር

ሀ. መምህር በመማሪያ መጽሐፍ ላይ የቀረቡትን ቃላት በምሳሌው መሰረት ነጣጥለው መጥራት እንዲችሉ ነጥለው በመጥራት ያሳይዋቸው። እያንዳንዳቸውን ሲጠሩ በጭብጨባ በማጀብ መነጠላቸውን እንዲረዱ ያድርጉ። ለምሳሌ የቀረበውን “ወቅት” የሚለውን ቃል በ “ወ” “ቅ” እና “ት” በመነጠልና ለእያንዳንዳቸው አንዳንድ ጊዜ በማጨብጨብ በተናጠል ጠርተው ያሳይዋቸው። በተመሳሳይ መንገድ የቀረበውን መልመጃ ተማሪዎች ተራ በተራ ድምጻቸውን ከፍ አድርገው እየጠሩና እያጨበጨቡ መነጠላቸውን እንዲያሳዩ ያድርጉ። ይህ ሂደት እያንዳንዱን መጥራት ብቻ ሳይሆን በቃሉ ውስጥ ያሉትን ፊደላት ቁጥርም ለማወቅ ያስችላቸዋል።

## ክፍለጊዜ ሰባት

ለ. ተማሪዎቹ ፊደላትን አጣምረው ቃላትን መጥራት እንዲችሉ ተነጣጥለው የቀረቡትን በተናጠል ከጠሩ በኋላ በፍጥነት አጣምረው መጥራት እንዲለማመዱ በቂ ምሳሌ በመስጠት ያለማምዷቸው። ቃላቱን ጥቁር ሰሌዳ ላይ ነጣጥለው በመጻፍ ተማሪዎቹ ተራ በተራ እያንዳንዱን ፊደል እያጨበጨቡ በመጥራት ቃሉን ፈጥነው እንዲጠሩ በማድረግ ትምህርቱ ሊቀርብ ይችላል። ወይም ፊደላቱን በተለያየ ፍላሽ ካርድ ላይ በማዘጋጀት እያንዳንዱን ፊደል ተማሪዎች ከፊት ሆነው ይዘው እንዲቆሙ በማድረግ ሌሎች ተማሪዎች ተራ በተራ ፊደላቱን ጠርተው እንዲያጣምሩ ማድረግ ይቻላል።

## ክፍለጊዜ ስምንት እስከ አስር

## ትምህርት አራት፡ የቃላት ጥናት

በዚህ ትምህርት የቃላት አጠቃቀማቸውን እንዲያዳብሩ ታስቦ የተዘጋጀ ነው። በዚህ መሰረት ከቃላት ውስጥ የተተው ፊደላትን በማሟላት አዳዲስ ቃላትን ይመሰርታሉ። በዚህም የቃላት አጠቃቀማቸውን ያዳብራሉ። ተማሪዎቹ ይኸንን እንዲለማመዱ ከክፍለጊዜ ስምንት እስከ አስር ያሉት ለመልመጃነት ቀርበዋል። ክፍለጊዜ ስምንት ከመጀመሪያ በመጨመር የተለያዩ

*ቃላትን መመስረት የሚለማመዱበት ይሆናል። ክፍለጊዜ ዘጠኝ የመጨረሻ ድምጽ ወይም ፊደል በመጨመር አዲስ ቃል የሚመሰረትበት ነው። ክፍለጊዜ አስር በቃል መሃል በመጨመር አዲስ ቃል የሚመሰረትበት ነው። በዚሁ መሰረት በቂ ምሳሌ በመስጠት በቅደም ተከተል መልመጃውን ማሰራት ከመምህራን ይጠበቃል። እንዳስፈላጊነቱ መልመጃዎችን ጨምረው ማሰራት ይችላሉ።*

**ማሳሰቢያ፡** *የሚመሰረቱት ቃላት ከአንድ በላይ ሊሆኑ ይችላሉ።*

## ክፍለጊዜ አስራ አንድ

*መምህር ተማሪዎቹ በምሳሌው መሰረት እንዲሰሩ በቂ ምሳሌ ይስጧቸው። ሮጠ" ለሚለው ይሮጣል" ከሆነ በተመሳሳይ መንገድ የቀረቡትን ቃላት መጥራት እንዲችሉ በቃል እንዲመልሱ ያድርጉ። የተሳሳተ መልስ የሚሰጡ ተማሪዎች ካጋጠሙ ስህተታቸውን እራሳቸው እንዲደርሱበትና እንዲያርሙ ጥያቄው በተለያየ መንገድ ይቅረብላቸው። ተማሪዎቹ የሚናገሩት መልስ ጥቁር ሰሌዳ ላይ በመጻፍ ትክክለኝነቱን በማየትም እንዲያረጋግጡ እድል ይመቻችላቸው። በመጨረሻ ትክክለኛውን ወደ ደብተራቸው እንዲገለብጡ ይደረግ።*

## ክፍለጊዜ አስራ ሁለት

## ትምህርት አምስት ፡ ማንበብ

### ድልድይ

### ቅድመንባብ

*መምህር ተማሪዎች የቀደመ እውቀታቸውን መጠቀም እንዲችሉ የሚከተሉትን የቅድመንባብ ጥያቄዎች መጠየቅ ይችላሉ። የተሻለ የተማሪዎቹን ተነሳሽነት ይጨምራል ብለው የሚያስቡትንና ማንበብ ሳይኖርባቸው የሚመልሱት ሌሎች ጥያቄዎችንም አዘጋጅተው መጠየቅ ይችላሉ።*

1. ከቀረበው ስዕል ምን ተገነዘባችሁ?
2. ምንባቡ ስለምን ይመስላችኋል?
3. በምስል ሁለት ላይ ያሉ ሰዎች ምን እያደረጉ ይመስላችኋል?

*መምህር ተማሪዎች በጸጥታ በግላቸው እንዲያነቡ ግልጽ መመሪያ ይስጧቸው። በምንባቡ መሃል በሳጥን የተቀመጠው ጋ ሲደርሱ ምን እንዳነበቡና ቀጥሎ ምን ሊያነቡ እንደሆነ ለተወሰኑ ሰኮንዶች ማሰላሰል መልእክት ለመረዳት እንደሚጠቅም በማሳሰብ ይህንኑ እንዲፈጽሙ መመሪያ ይስጧቸው።*

## ክፍለጊዜ አስራ ሶስት

## የአንብቦ መረዳት ጥያቄዎች

መምህር በመማሪያ መጽሐፍ ላይ የቀረቡትን ቃላት ከአነበቡት ሃሳብ በመነሳት ተገቢ ቃል በባዶ ቦታ ላይ በመሙላት አረፍተነገሮቹን እንዲያስተካክሉ ይርዷቸው።

ተማሪዎቹ አረፍተነገሮቹን ወደደብተራቸው እንዲገለብጡ ይደረግ። የገለበጡትን በመጀመሪያ በግላቸው መልሱን ይስሩ። በመቀጠል በሰሩት መልስ ላይ በጥንድ በመወያየት ይተራረሙ። ይህ ሲከወን በመዘዋወር የተማሪዎቹን እንቅስቃሴ ይከታተሉ። አስፈላጊ ሆኖ በሚያገኙት ነጥብ ላይ ድጋፍ ያድርጉላቸው። በመጨረሻ በየጥያቄው የተወሰኑ ተማሪዎችን በማሳተፍ የተስተካከለ መልስ እንዲኖራቸው ይደረግ። መልሶቹ ጥቁር ሰሌዳ ላይ ይጻፍላቸው። የተስተካከለውን መልስ በማስታወሻቸው ላይ እንዲጽፉት ይደረግ።

## ክፍለጊዜ አስራ አራት

መምህር፣ እርስዎ በሚያመቻቹት መንገድ ተማሪዎች ለክፍለጊዜው የቀረቡትን ጥያቄዎች በምንባቡ መሰረት ተወያይተው መልሱን ይፈልጉ። ተወያይተው የደረሱበትን መልስ በተወካያቸው አማካኝነት ለክፍል ጓደኞቻቸው እንዲያቀርቡ ይደረግ።

## ክፍለጊዜ አስራ አምስት

## ደጋግሞ ከፍ ባለድምጽ ማንበብ

ሀ. መምህር ቃላቱን አቀላጥፈው ማንበባቸውን ይከታተሉ። የተለያዩ ተማሪዎችን እንዲያነቡ ያድርጉ።

ለ. ቃላትን ደጋግመው እንዳነበቡት አረፍተነገሮችንም ተራ በተራ ድምጻቸውን ከፍ አድርገው እንዲያነቡ ይደረግ። በዚህ ሂደት ውስጥ በተገቢፍጥነትና ቅላጼ ለማንበባቸው ትኩረት ይሰጥ።

## ክፍለጊዜ አስራ ስድስት

## ትምህርት ስድስት፡ መፃፍ

መምህር ተማሪዎቹ በትክክለኛ ፊደላት መጻፋቸውን ይከታተሉ። መጽሀፋቸውን ሸፍነው መማሪያ መጽሐፋቸው ላይ የቀረቡትን ቃላት አንድ ባንድ ሲያነቡላቸው እንዲጽፉ ያድርጉ። የጻፉትን ትክክል ስለመሆኑ በጥንድ ይነጋገሩበት። በመቀጠል መጽሃፋቸውን ከፍተው ትክክለኛውን አጻጻፍ እንዲያረጋግጡ ያድርጉ። በሞክሼ ፍደላት ምክንያት

የሚፈጠር መለያየት ችግር አለመሆኑን በማስረዳት ትምህርቱን ይቋጩላቸው።

## ክፍለጊዜ አስራ ሰባት

መምህር በ"ሀ" እና በ"ለ" ስር የቀረቡት ፅሁፎች ተመሳሳይ ናቸው። የቀረቡበት ዋና አላማ የስርአተነጥብ አስፈላጊነት እንዲረዱ ታስቦ ነው። ስለዚህ በመጀመሪያ በ"ሀ" ስር የቀረበውን ተማሪዎች በግላቸው እንዲያነቡ ያድርጉ። በመቀጠል የተወሰኑ ተማሪዎች ድምጻቸውን ከፍ አድርገው ለክፍሉ ተማሪዎች እንዲያነቡ መመሪያ ይስጧቸው።

በመቀጠል በማንበብ ላይ ችግር ገጥሟቸው እንደሆን ይጠይቋቸው። መልሰቸውን ከተቀበሉ በኋላ በ"ለ" ስር የቀረበውን በግላቸው እንዲያነቡ ያድርጉ። ከግል ንባብ በኋላ በ"ሀ" ስር የቀረበውን ድምጻቸውን ከፍ አድርገው ያነበቡ ተማሪዎች በ"ለ" ስር የቀረበውንም ድምጻቸውን ከፍ አድርገው እንዲያነቡ ያድርጉ። በመቀጠል በ"ሀ" ስር ወይስ በ"ለ" ስር የቀረበው ተመችቷቸው እንዳነበቡ ይጠይቋቸው።

በመጨረሻ በአራት ነጥብና በጥያቄ ምልክት አለመኖር ምክንያት እንደሆነ በቂ መረጃ በመስጠት የስርአተ ነጥብ አስፈላጊነት ያስረዷቸው።

## ክፍለጊዜ አስራ ስምንት

መምህር መልመጃው መጻፍን ለመለማመድ እንዲረዳ ተስቦ የቀረበ ነው። ተማሪዎቹ የተጀመረውን ሃሳብ ቃል ወይም ሀረግ በመጨመር አጭር ታሪክ በጋራ መጻፍን እንዲለማመዱ ይረዳቸዋል። ስለዚህ ባዶ ቦታዎች ያሉትን አጭር ታሪክ በመጀመሪያ በወረቀት ላይ እንዲገለብጡ ይደረግ። ከዚያ በእርስዎ በሚጠራ ቡድን አማካኝነት ክፍት ቦታዎቹን ሙሉ የሚያደርጉ ቃላት ወይም ሀረጋት እያዋጡ ታሪኩን ሙሉ እንዲያደርጉ ጊዜ ይስጧቸው። ተማሪዎቹ ሲሰሩ ድርጊታቸውን ይከታተሉ። አስፈላጊ በሆነበት ድጋፍ ያድርጉላቸው።

# ምዕራፍ ሶስት

# ተረቶች

(18 ክፍለ ጊዜ)

## 1. ከትምህርቱ የሚጠበቁ ውጤቶች

ከዚህ ምዕራፍ ትምህርት በኋላ ተማሪዎች

- ምንባቡን አዳምጠው ዋና ሀሳቡን በመለየት በቃል ይዘግባሉ።
- ያነበቡትን ምንባብ አጠቃላይ ሀሳብ ይጽፋሉ።
- በአረፍተ ነገር ውስጥ አራት ነጥብን ይጠቀማሉ።
- ባለአራት ቀለም ተዘውታሪ ቃላትን ይጽፋሉ።
- ቃለአጋኖንና የጥያቄ ምልክትን ይጠቀማሉ።

## 2. ዝርዝር ይዘቶች

- መናገርና ማዳመጥ
- ስነድምጻዊ ግንዛቤ
- ትዕምርተ ድምጻዊ ግንዛቤ
- የቃላት ጥናት፡ ተዘውታሪ ቃላት(የትምህርት ቃላት) የቃላት ዕውቀት ማሳደግ
- ማንበብና መጻፍ
  - ማንበብ፡ትክክለኛነት፣
  - በፍጥነት፣በመግለጽ፣በመረዳት
- መጻፍ፡ ድምጾትን በትክክል መረዳት

## 3. የማስተማሪያ ብልሀቶችና መሳሪያዎች

መምህር የተማሪዎቹን የቀደመ ዕውቀት ለማነሳሳት ስለርዕሱ የተወሰኑ ቅድመማዳመጥና ቅድመንባብ ጥያቄዎችን ያቀርባሉ። በክፊል የተሞሉ ሰንጠረዦችን በማቅረብ ቀሪውን ተማሪዎች እንዲሞሉ ያደርጋሉ። መምህር ድምጽ ከፍ አድርገው ሲያነቡ የቀረውን ተማሪዎች በቃል ባዶ ቦታውን ይሞላሉ።

ተማሪዎች ከወቅቶች ጋር የሚቀራረቡ ቃላትን [ለምሳሌ፡-በሳምንት ውስጥ ያሉ ቀናት፣ በአመት ውስጥ ያሉትን ወራት፣ ወቅት፣ (ክረምት፣ በጋ፣ በልግ ጸደይ)] እንዲለዩ ማድረግ።

**መነጠልና ማጣመር ፡**

**መምህር** መነጠልን ለማሳየት ቃላት ውስጥ ያሉ ፊደላትን ነጥሎ በመጥራት ያሳያሉ። ማጣመርንም ለማሳየት በቃል ውስጥ ያሉ ፊደላትን በተናጠል ጠርቶ በመጣመር ምሳሌ ይሰጣሉ።

ተማሪዎች በሚሰጣቸው ምሳሌ መሰረት የሚነበብላቸውን ቃል በፍጥነት ነጥለው ይጠራሉ። ተነጥሎ የሚነገራቸውን በፍጥነት አጣምረው ቃሉን ይናገራሉ።

**ማተካካት፡** መምህር ተማሪዎች የገደፉትን ቃላት መልሶ መተካት።

**ሀ.መግደፍ፡** ተማሪዎች ቃላትን ካዳመጡ በኋላ ድምጾችን/ቀለማትን እንደመጀመሪያው ሳይጠሩ መቀየር፤

**ለ.መጨመር** ፡ተማሪዎች ባዳመጡት ቃል ላይ ድምጽን/ምዕላድን መጨመር

**ሐ.መተካት** ተማሪዎች ካዳመጡት ቃል ሌላ ድምጽ/ምእላድ መተካት፤

(የድምጾችን/የፊደላትን ቅርጽ፣ የባለቀለም ወረቀት፣ የካርቱን ስዕሎች፣ የቃላት ካርድ፣ ሰሌዳ ወዘተ መጠቀም)

**ከምንባቡ ጋር ማዛመድ** ተማሪዎች ምንባቡን በማንበብ መጻፍ መለማመድ፣ የሚጻፈውም ምንባቡ ነው።

**ተዘውታሪ ቃላት፡** ተማሪዎች ከምንባቡ ውስጥና ከምንባቡ ውጭ ከፍተኛ ድግግሞሽ ያላቸውን ቃላት ፈጥነው የመለየት ልምድ ማዳበር።

**በቃል መጻፍ** ተማሪዎች ቃላትን አዳምጠው በትክክል ለመጻፍ መሞከር።

**ተደጋጋሚ ቃላዊ ንባብ፡** ይህ ተደጋጋሚ ቃላዊ ንባብ በማቅረብ ከጓደኛ፣ ከመምህራንና ከቤተሰብ ምላሽ ማግኘትን ይመለከታል።

**በጊዜ የተገደበ ተደጋጋሚ ንባብ፡** ተማሪዎች አጭር ምንባብን ብዙ ጊዜ ያነባሉ። እያንዳንዱን ንባብም በጊዜ መገደብ። የንባብ ፍጥነትንም ለውጡን በቻርት ማስቀመጥ።

**አረፍተ ነገሮችን ማድመቅ፡ አንድ** አረፍተ ነገር ብዙ ጊዜ ማንበብ። በእያንዳንዱ ጊዜ ለተለየው ቃል ትኩረት መስጠት።

**ለምልክቶች ትኩረት መስጠት፡** አገላለጽን ለማሻሻል መምህር በግልጽ የምልክቶችን አላማ በመግለጽ እንዴት እነዚህ ምልክቶች በአገላለጽና በድምጸት ላይ ተጽእኖ እንደሚደርጉ ያብራራሉ።

መምህር ተማሪዎችን በቡድን ማስቀመጥ። ስርዓተ ነጥቦችን (አራት ነጥብ፣የጥያቄ ምልክት፣)

ያልያዘ አጭር ምንባብ ለተማሪዎች ይሰጣል፤ ተማሪዎች ተራ በተራ ድምጻቸውን ከፍ አድርገው ማንበብ። ከዚያም መምህር ተማሪዎች ያለ ስርዓት ነጥበ ማንበብ ቀላል ወይም ከባድ መሆኑን ይጠይቃል።ይሄ ለምን ሆነ? ምን ማለት እንችላለን? የስርዓተ ነጥብ አገልግሎት ነው ማለት እንችላለን? እንዴት ይረዳናል? ከዚያም ተማሪዎች አራት ነጥብ በሚገባበት ቦታ ከጓደኞቻቸው ጋር ያስገባሉ።

በቡድን መጻፍ፡መምህር አርዐያ በመሆን ተማሪዎች አንድ የጋራ ንባብ እንዲጽፉ ማበረታታት።

## 4.ምዘና

- ቃላዊ/ጽሁፋዊ ጥያቄዎችን መጠየቅ
- አካላዊ ምላሽ (ተማሪዎች በግላቸው ለጥያቄዎች በአካል እንቅስቃሴ የሚሰጡት ምላሽ)
- ኢ-መደበኛ ቁጥጥር (ምልከታ) በሚታይ መወከል ተራ በተራ ማቅረብ የመውጫ ካርዶች ጽብረቃ ስልታዊ ልምምድ

## ክፍለጊዜ አንድ

## ትምህርት አንድ፡ ማዳመጥ

መምህር እባክዎ በመጀመሪያ በእለቱ የሚደመጠውን ርእስ “**ጠጣና አዞ**” በጥቁር ሰሌዳ ላይ ይጻፉ። ተማሪዎቹ ስለርእሱ የሚያውቁትን እንዲያስታውሱና ትኩረታቸው እንዲሰበሰብ የሚከተሉትን ጥያቄዎች በመጠየቅ ሊጀምሩ ይችላሉ። አለበለዚያም የተማሪዎቹን የማዳመጥ ስሜት ሊያነሳሱ የሚችሉና ከርእሱ ጋር ተያያዥነት ያለቸው እንዲሁም ተማሪዎቹ ከልምድ ተነስተው ሊመልሷቸው የሚችሉ ሌሎች ጥያቄዎች አዘጋጅተው መጠየቅ ይችላሉ።

መጽሀፋቸውን ክፍለጊዜ አንድን እንዲገልጡ ይንገሯቸው። በማዳመጥ ስር የቀረቡትን ስእሎች እንዲመለከቱ አድርጓቸው። ከስዕሉ ምን እንደተረዱ ይጠይቋቸው።

የተማሪዎቹን ግምት ከተቀበሉና ካደነቁላቸው በኋላ መልእክቱን እንዲረዱ ለክፍል ደረጃው በሚመጥን ፍጥነት ያንብቡላቸው። የነሱ ግምት እንዳለ ሆኖ የሚቀርበው ምን እንደሚል ለማወቅ በጥሞና ማዳመጥ እንደሚያስፈልግ ያሳስቧቸው።

መምህር ምንባቡንም ጮክ ብለው ያንብቡላቸው። በንባቡ መሃል *** ምልክት ባለበት

ንባቡን ገታ አድርገው ቀጣዩን ሀሳብ እንዲገምቱ ጥያቄውን ይጠይቋቸው። ተማሪዎቹ ካዳመጡት ተነስተው ቀጣዩን መገመት እንዲችሉ የራስዎትን ጥያቄም አዘጋጅተው መጠየቅ ይችላሉ። የሚቀርቡት ጥያቄዎች በተገቢው መንገድ ማዳመጥን የሚጋብዙ መሆን አለባቸው። መርዘምና መልሳቸውም ምርምር የሚጠይቁ መሆን የለባቸውም። በማዳመጥ ሂደት ውስጥ መልስ የሚያገኙላቸው መሆን አለባቸው።

## ጦጣና አዞ

በድሮ ጊዜ የጦጣ ልጅና እናቷ ሆነው አብረው ይኖሩ ነበር። የጦጣ ልጅ የግቤን ወንዝ ካላየሁ ብላ እናትዋን አስጨነቀች። ብዙ ተማካከሩ።

*** ቀጥሎ ምን የሚሆን ይመስላችኋል?***

ቢመካከሩም ሳይግባቡ ቀሩ። የጦጣ ልጅም ግቤን ለማየት ወደዛው አቀናች። እንደደረሰችም አዞ ያዛት። ማምለጫ መንገድ ስትፈልግ አንድ ነገር መጣላት። ብዙ ዘመድ እንዳላት፤ ቀድማ ቦታውን አይታ እንድትመጣ እንደላኳት ለአዞው ነገረችው። ስለዚህ እነሱን ይዛ ብትመጣ ብዙ ምግብ እንደሚያገኝ አበሰረችው። እሷን ብቻ ቢበላ ግን ተጎጂ መሆኑን ገለጸችለት።

*** አዞው ይለቃት ይሆን? ምን ይፈጠር ይሆን?***

አዞውም አምኖ ለቀቃት። እንደተለቀቀችም ዛፍ ላይ ወጥታ ከአንጀቷ ሳቀች። አዞውም “ምን ያስቅሻል?” ሲል ጠየቃት። “አንድም በራሴ፣ አንድም ባንተ ነው የምስቀው” አለችው። “በኔም ሆነ በራስሽ የምትስቂው ምንድነው?” አላት። “በራሴ የምስቀው ሰፈሬን ትቼ ግቤን ካለየሁ ብዬ አደጋ ላይ በመውደቄ ነው። ባንተ የምስቀው ደግሞ ብዙ ስትመኝ እጅህ የገባውን ሲሳይ በማጣትህ ነው” አለችው፤ ይባላል።

## ክፍለጊዜ ሁለት

## መልመጃ አንድ

## አዳምጦ መረዳታቸውን የሚፈትሹ ጥያቄዎች።

ሀ. በአዳመጡት መሰረት የሚመልሷቸው

ጥያቄዎቹ በማዳመጥ ላይ የሚመሰረቱ ከመሆናቸው አንጻር መልመጃዎቹ ከመሰራታቸው በፊት አንድ ጊዜ በድጋሚ ሊነበብላቸው ይገባል።በመቀጠል በመማሪያ መጽሐፍ ላይ የቀረቡትን ጥያቄዎች ላይ ለሁለት በመነጋገር መልስ እንዲፈልጉ ተማሪዎችን በቡድን

ማደራጀትና ሂደቱን እየተከታተሉ ድጋፍ መስጠት ተገቢ ይሆናል።

ለ. ባዳመጡት መሰረት ለቃላት ፍቺ መሥጠት

መምህር፣ እባክዎ ተማሪዎችዎ በቃላቱ ፍቺ ላይ በጥንድ እንዲወያዩ ያድርጉ። በውይይታቸው መሰረት በየተራ በቃላቸው የተስማሙበትን ፍቺ ለክፍሉ እንዲያቀርቡ ያበረታቱ። ከተሰጡት ቃላት ውጪ ካዳመጡት ጋር የተያያዙና ፍቺ የሚፈልጉ ቃላት ካሉ ተማሪዎችዎ እንዲጠይቁ ያበረታቱ። ለሚቀርቡ ጥያቄዎች ከተማሪዎች ውስጥ መልስ እንዲሠጥበት ያድርጉ። ተጨማሪ ማብራሪያ በመስጠት መልሱን ያጠናክሩ።

## ክፍለጊዜ ሶስት

## ትምህርት ሁለት፡ መናገር

መምህር እባክዎ ተማሪዎችዎ ሶሥት ሶሥት ሆነው እንዲቧደኑ ያድርጉ። ተማሪዎቹ ከአዳመጡት ውስጥ ዋና ዋና ነጥቦችን በየተራ ለቡድናቸው እንዲናገሩ ያመቻቹላቸው። በቡድናቸው በየግላቸው በሰጡት መልስ ላይ እንዲወያዩ ያድርጉ። የውይይቱን ሂደት ይከታተሉ። ለተማሪዎችዎ በቂ የመወያያ ጊዜ ይስጡ። የውይይታቸውን ውጤት በየተራ በቡድን ተወካይ በኩል በቃል ለክፍል እንዲያቀርቡ ያድርጉ።

1. በንግግር ወቅት የአቅራቢን የሀሳብ ፍሰት፣ በራስ መተማመንና የቃላት ምርጫ ትክለኛነት ላይ አስፈላጊ በሆነበት የእርምት ምጋቤ ምላሽ ይስጡ።
2. የአነጋገር ሁኔታቸውን በሩብሪክ መረጃ በመያዝ በየጊዜው የሚያሳዩትን መሻሻል ይከታተሉ። ያሳዩትን መሻሻል በማሳየት ይበልጥ ተግተው እንዲለማመዱ ያበረታቷቸው።

## ክፍለጊዜ አራት

መምህር እባክዎ ተማሪዎችዎ የሚያውቁትን ታሪክ/ተረት ለክፍል እንዲያቀርቡ በማድረግ የንግግር ችሎታቸውን እንዲያዳብሩ ሁኔታዎችን ያመቻቹላቸው። በዚህኛው አቀራረብ ላይ የመናገር እድል ለአላገኙ ተማሪዎች ትኩረት በመስጠት ያሳትፉ። በየተራ በሚያቀርቡበት ጊዜ የእያንዳንዳቸውን የንግግር ጥሩ ገጽታና ሊያሻሽሉ በሚገባቸው ላይ የወዲያው ምጋቤ ምላሽ በመስጠት ያበረታቷቸው።

## ክፍለጊዜ አምስት

መምህር እባክዎ ተማሪዎችዎን በጥንድ በጥንድ እንዲቧደኑ ያድርጉ። በቡድናቸው የትምህርት ሰአት ቢያልፍባቸው ምን ዘዴ እንደሚጠቀሙ እንዲወያዩ በቂ ጊዜ

ይስጧቸው። ሂደቱንም ይከታተሉ። የተወያዩበትን ከሁለት አንዳቸው ለክፍል እንደሚያቀርቡ ግልጽ መመሪያ ይስጧቸው። ማቅረቡን አነስተኛ ተሳትፎ ያላቸው ቅድሚያ እንዲሰጣቸው በማድረግ ያሳትፏቸው።

## ክፍለጊዜ ስድስት

## ትምህርት ሶስት፡ መነጠል እና ማጣመር

### መልመጃ ሁለት፡ መነጠል

*መምህር የእለቱን ትምህርት ከመጀመርዎ በፊት በምዕራፍ ሁለት ተመሳሳይ የመነጠል መልመጃዎችን መስራታቸውን ያስታውሷቸው። በተጨማሪ ከእለቱ መልመጃ ጋር ያስተዋውቁ። እያንዳንዱን ነጥለው ሲጠሩ እያጨበጨቡ መሆን እንዳለበት ያስታውሷቸው። እንደአስፈላጊነቱ ምሳሌዎችን በመስጠት ያሳትፏቸው።*

## ክፍለጊዜ ሰባት

*መምህር የእለቱን ትምህርት ከመጀመርዎ በፊት በክፍለጊዜ ስድስት የተሰራውን (መነጠልን) ያስታውሷቸው። በማያያዝም ከእለቱ ትምህርት (ማጣመር ጋር ያስተዋውቋቸው። በእለቱ ትምህርት በመጀመሪያ የተነጣጠሉትን በጭብጨባ እየታገዙ በተናጠል መጥራትና ወዲያውኑ አጣምሮ ቃሉን መጥራት እንደሚጠበቅባቸው ያሳውቋቸው። መልመጃውንም ተራ በተራ እየተነሱ እንዲሰሩ በማድረግ ያሳትፉ።*

## ክፍለጊዜ ስምንት

## ትምህርት አራት፡ የቃላት ጥናት

*መማሪያ መጽሐፍ መልመጃ ሶስት ስር የቀረቡትን ቃላት በማንበብ ከሚወክላቸው ምስል ጋር በመስመር በማገናኘት በትምህርት ቤት አከባቢ ተዘውትረው ስራ ላይ የሚውሉ ቃላት ጋር እንዲተዋወቁ ያድርጓቸው። ስዕሎቹንና ቃላቱን በተለያየ ካርድ ላይ ለማቅረብ ምቹ ሁኔታ ካለ በሌላ በኩል ቢሰራ ተማሪዎችን ይበልጥ የሚስብና አሳታፊ ይሆናል። ሌላ ምቹ መንገድ ፈልጎ ስራ ላይ ማዋል ይቻላል።*

## ክፍለጊዜ ዘጠኝ

### ሀ. ከቃል የመጀመሪያ ፊደል በመተው ቃል መመስረት።

*መምህር ተማሪዎች የመጀመሪያውን ድምጽ ወይም ፊደል በመተው ቃላት በፍጥነት እንዲመሰርቱ ያድርጉ። በቂ ምሳሌ በመስጠት ያበረታቷቸው። ቃሉን ካነበቡላቸው በኋላ የመጀመሪያውን ፊደል ትተው እንዲናገሩ ያድርጉ። ተማሪዎቹ ትተው የሚናገሩትን ቃል*

ጥቁር ሰሌዳ ላይ በመፃፍ ትክክለኝነቱን ተማሪዎች በማየት እንዲያረጋግጡ ያመቻቹላቸው። ምሳሌ “መተው” ከሚለው ውስጥ “መ” ሲተው “ተው” የሚል ቃል ይገኛል። በተመሳሳይ መንገድ እንዲሰሩ የሚከተሉትን ቃላት በዝግታ እያነበቡላቸው እንዲለማመዱ ያድርጉ።

1. አማረ
2. ተማረች
3. መተካት
4. በደብተር
5. ከክፍል
6. ተተነተነ

## ክፍለጊዜ አስር

## ለ. ከቃል መጨረሻ ፊደል በመተው ቃል መመስረት።

**መምህር** በክፍለጊዜ ዘጠኝ ከሚነበብላቸው ቃል ውስጥ የመጀመሪያውን ፊደል በመተው ቃላት መመስረት መለማመዳቸውን ምሳሌ በመስጠት ያስታውሷቸው። በመቀጠል የእለቱ ትምህርት የመጨረሻውን በመተው ቃላትን መመስረት እንደሆነ ምሳሌ በመስጠት ያሳውቋቸው። ቃላቱን በዝግታ እያነበቡ ተማሪዎቹ እጅ በማውጣት በፍጥነት ቃል እንዲመሰርቱ (እንዲጠሩ) ያድርጉ። ተማሪዎቹ የሚመሰርቱትን ቃል ጥቁር ሰሌዳ ላይ በመፃፍ ትክክለኝነቱን እንዲያረጋግጡ ይርዷቸው።

1. ሰጠመ
2. መላስ
3. መታው
4. ተማረች
5. ተካት
6. መጣች

## ክፍለጊዜ አስራ አንድ

## ሐ. ከቃል መሃል ፊደል በመተው ቃል መመስረት።

መምህር በተማሪ መጽሐፍ ላይ የቀረቡትን ምሳሌዎች በመጠቀም እንዴት መስራት እንዳለባቸው ያስረዱ። በቀደሙት ክፍለጊዜዎች ውስጥ ከቃል መጀመሪያና መጨረሻ ፊደል በመተው ቃላት መመስረትን መለማመዳቸውን ያስታውሷቸው። እነዚህን ደግሞ ሲነበብላቸው ከመሃል ፊደላትን በመተው ቃላት እንዴት እንደሚመሰርቱ እንዲለማመዱ ያግዟቸው። ምሳሌ “አደረሰ” ከሚለው ውስጥ በየተራ “ደ” እና “ረ” ቢተው “አረሰ” እና “አደሰ” የሚሉ ቃላትን ማግኘት ይቻላል። በሌላ በኩል ከአንድ በላይ ቃል መመስረት እንደሚቻልም ከግምት ይግባ።

1. አሰለፈ
2. አወለቀ
3. አፈሰሰ
4. አበጠረ
5. ምርቃት
6. አነበቡ

## ክፍለጊዜ አስራ ሁለት

## ትምህርት አምስት፡ ማንበብ

### የኤሊና የጥንቸል ውድድር

የምንባቡን ርዕስ (የኤሊና የጥንቸል ውድድር) በጥቁር ሰሌዳ ላይ ይጻፉና ከተማሪዎችዎ መካከል የተወሰኑት ርእሱን እንዲያነቡ ያድርጉ። በመቀጠል መማሪያ መጽሐፍ ላይ የቀረቡትን የቅድመንባብ ጥያቄዎች በመጠየቅ ከተወሰኑ ተማሪዎች ላይ መልስ ይቀበሉ። ሁሉም መልሶች ከግል ገጠመኝና ግንዛቤ የሚመጡ በመሆኑ ትክክል ናቸው። ስለዚህ በቅድመንባብ ጥያቄዎች ላይ አስተያየት ከመስጠት ይቆጠቡ።

*(የተማዎቹን ግምታዊ መልስ ከተለያዩ ተማሪዎች ይቀበሉ። ግምታቸውን ለማረጋገጥ ማንበብ እንዳለባቸው በማሳሰብ ወደ ንባብ እንዲገቡ ያድርጉ።*

**መምህር፣** ተማሪዎቹ ወደንባብ ከመግባታቸው በፊት በምንባቡ ውስጥ በሳጥን የተቀመጡ ጥያቄዎች እንዳሉ ይጠቁሟቸው። ጥያቄዎቹ ካነበቡት የተረዱትን እንዲያጤኑና ቀጥሎ የሚያነቡትን እንዲገምቱ የሚያደርጉ እንደሆነ እንዲገነዘቡ ይርዷቸው። ምንባቡን ድምጽ ሳያሰሙ በግላቸው ማንበብ እንዳለባቸውና ከምንባቡ የወጡ ጥያቄዎችን መመለስ እንደሚጠበቅባቸው በማሳሰብ ወደንባብ እንዲገቡ ያድርጉ።

## ክፍለጊዜ አስራ ሶስት

## አንብቦ የመረዳት ጥያቄዎች

### መልመጃ አምስት

ሀ. በመማሪያ መጽሐፍ ላይ የቀረቡትን ከምንባቡ ጋር የተያያዙ ሀሳቦችን ትክክል ከሆኑ "እውነት" ካልሆኑ "ሐሰት" በማለት መጀመሪያ በግል እንዲሰሩ ይደረግ። በመቀጠል በግል የሰሩትን መልስ በጥንድ እንዲወያዩበትና ሀሳብ እንዲለዋወጡ ይደረግ።

## ክፍለጊዜ አስራ አራት

ለ. በመማሪያ መጽሐፍ ላይ የቀረቡትን ከምንባብ የወጡ አረፍተነገሮች ውስጥ ያሉትን ባዶ ቦታዎች በትክክል የሚያሟሉ ከተሰጡት ቃላት ውስጥ በመምረጥ እንዲያሟሉ ግልጽ መመሪያ ይስጣቸው። መጀመሪያ በግል ሰርተው መልሳቸውን በጥንድ እንዲያስተያዩ ይደረግ።

## ክፍለጊዜ አስራ አምስት

**መምህር** ተማሪዎችዎ መማሪያ መጽሐፍ ላይ የቀረበውን አጭር ምንባብ ድምጽ እያሰሙ በየተራ እንዲያነቡ ያድርጉ። በዚህ የንባብ ጊዜ በተማሪዎችዎ የአነባበብ ሁኔታ ላይ ያትኩሩ። እየተከታተሉ አቀላጥፎ የማንበብ ችሎታቸውን እንዲያዳብሩ አስፈላጊውን ድጋፍ ያድርጉላቸው። ፍጥነታቸውን መረጃ በመያዝ ይከታተሉ።

ተማሪዎቹ ምንባቡን በየተራ ድምጻቸውን ከፍ አድርገው ለደረጃው በሚመጥን ፍጥነት እንዲያነቡ ያድርጉ። በዚህ ሂደት ውስጥ የተማሪዎቹን የንባብ ፍጥነት መሻሻል በሰንጠረዥ መረጃ ይያዙ። በያዙት መረጃ መሰረት እንደየተማሪዎቹ ሁኔታ የሚያስፈልጋቸውን ድጋፍ ያድርጉ።

## ክፍለጊዜ አስራ ስድስት

## ተግባር አራት

አጭር ምንባብ ለፍጥነትና ትክክለኛ ቅላጼ እንዳነበቡት አረፍተነገሮችንም ተራ በተራ ድምጻቸውን ከፍ አድርገው እንዲያነቡ ይደረግ። በዚህ ሂደት ውስጥም በተገቢ ፍጥነትና ቅላጼ ለማንበባቸው ትኩረት ይሰጥ።

## ክፍለጊዜ አስራ ሰባት

## ትምህርት ስድስት፡ መፃፍ

## መልመጃ ስድስት

**ለምልክቶች ትኩረት መስጠት፡** መምህር አገላለጽን ለማሻሻል በግልጽ የምልክቶችን አላማ በመግለጽ እንዴት እነዚህ ምልክቶች በአገላለጽና በድምጸት ላይ ተጸእኖ እንደሚደርጉ ያብራሩላቸው። በማብራሪያው መሰረት ተማሪዎች በመማሪያ መጽሐፍ ላይ የቀረቡትን አረፍተነገሮች ከቀረቡት ስርአተነጥቦች ውስጥ መርጠው በትክክለኛ ቦታ እንዲያስገቡ ተገቢ ድጋፍ ያድርጉላቸው።

## መልመጃ ሰባት

**መምህር** የሚከተሉትን ቃላት ያንብቡላቸውና በትክክል እንዲፅፉ ያድርጉ። በትክክለኛ ፊደላት መጻፋቸውን ይከታተሉ።

1. መንገድ
2. አቃተው
3. አድርጎ
4. መሻገሪያ

# ክፍለጊዜ አስራ ስምንት

## መልመጃ ስምንት

**መምህር** በመማሪያ መጽሐፍ ላይ የቀረቡትን የሚከተሉትን የመጻፍ ተግባራት በትክክል እንዲፈጽሙ ይርዷቸው። ተግባሩን በመጀመሪያ በግል ከሰሩ በኋላ የሰሩትን በጥንድ እንዲያስተያዩና እንዲተራረሙ ይደረግ።

ሀ. አራት ባለሁለት ፊደል ቃላት ጻፉ።

ለ. ሶስት ባለሶስት ፊደል ቃላት ጻፉ።

ሐ. ሁለት ባለአራት ፊደል ቃላት ጻፉ።

## ተግባር አምስት

መምህር አራት አራት በመሆን ስለአንድ አጭር ታሪክ የሚናገሩ አራት የተቀናጁ አረፍተነገሮች ተረዳድተው እንዲጽፉ ድጋፍ ያድርጉላቸው።

# ምዕራፍ አራት

# የአትክልት ቦታ

(18 ክፍለ ጊዜ)

## 1. ከትምህርቱ የሚጠበቁ ውጤቶች

ከዚህ ምዕራፍ ትምህርት በኋላ ተማሪዎች፡

- ከሚያዳምጡት ነገር ዝርዝር መረጃዎችን ይለያሉ፤
- ከሚያዳምጡት ነገር ዝርዝር መረጃዎችን ይጽፋሉ፤
- ቃለአጋኖንና የጥያቄ ምልክትን ለይተው ይጠቀማሉ፤
- ከቃላት ድምጾችን ይነጥላሉ፤
- ድምጾችን አጣምረው ቃል ይመሰርታሉ።

## 2. ዝርዝር ይዘቶች

- ማዳመጥና መናገር
- ድምጻዊ ግንዛቤ
- የትዕምርተ ድምጽ ግንዛቤ
- የቃላት ጥናት፡ ተዘውታሪ (የትምህርት) ቃላት
- -ጽንሰሃሳቦችን መሰየም
- ማንበብና መጻፍ፡ ማንበብ፡ትክክለኛነት፣ፍጥነት፣ጥሩ አገላለጽ፣አንብቦ መረዳት
- መጻፍ፡ትክክለኛነት፣ ድምጸታዊ ግንዛቤ

## 3. የማስተማሪያ ብልሀቶችና መሳሪያዎች

መምህር የተማሪዎችን የቀደመ እውቀት መቀስቀስ። በተማሪው የሚሞላ ቻርት ማዘጋጀት። መምህር ተማሪዎች ከሚያዳምጡት ነገር ቻርቱን እንዲሞሉ ማድረግ።

**መነጠልና ማጣመር**፡ መምህር ሞዴል ሆኖ ቃላትን ከድምጾች ጋር ድምጾችን ደግሞ ከቃላት ጋር በመነጠልና በማጣመር ማሳየት። ተማሪዎች በቃላት ውስጥ ድምጾችን ከዚያም ቃላትን በፍጥነት መጥራት (ፊደላትን አገናኝቶ ማጣመርን ያሳያል) ከዚያም እያንዳንዱን ቀለም ወይም ድምጽ መጥራት።

**ማተካካት**፡ መምህር ተማሪዎች በጨዋታ እንዲወዳደሩ በቡድን ማስቀመጥ። ተራ በተራ

ከቃላት ላይ ድምጾችን/ቀለማትን የመግደፍ፣ የመጨመርና የማተካካት ጨዋታ እንዲጫወቱ መንገር። ጨዋታው ለማጠናቀቅ የሚፈጀው ጊዜ በተማሪዎች አረዳድ ላይ ይመሰረታል። ጨዋታውን ቀድሞ ያጠናቀቀ ነጥብ ያገኛል። ይህም ትምህርቱን በተነሳሽነት እንዲከታተሉ ይረዳል። የጨዋታው ሂደት ሰዓት አስከባሪ፣ ውጤት መዝጋቢና መሪ ሊኖረው ይገባል።

ሀ. ተማሪዎች ቃላቱን ካነበቡ በኋላ በቃሉ መነሻ ላይ ያለውን ቀለም/ድምጽ በመተው መጥራት።

ለ. ተማሪዎች ቃላቱን ካዳመጡ በኋላ ቀለሞችን /ድምጾችን መጨመር።

ሐ. ማተካካት፡ተማሪዎች ካዳመጡ በኋላ በቃሉ ላይ ያሉትን ቀለማትን/ድምጾችን ይቀይራሉ

**መናገር፡** መምህር ቃሉን ካሳዩ በኋላ በቃሉ ውስጥ ያሉትን ድምጾች ይጥሩላቸውና ድምጾቹን ይነጣጥሉ(የታወቁ ትዕምርተ ድምጽ ግንዛቤን ይጠቀሙ) በሂደቱ ተማሪዎች ቃልን ወስደው ድምጾችን መነጠል ይለማመዳሉ (የድምጾችን/የፊደላትን ቅርጽ፣ የባለቀለም ወረቀት ፣ የካርቱን ስዕሎች፣ የቃላት ካርድ፣ ሰሌዳ መጠቀም ይቻላል) ከርእሰ ጉዳዩ ጋር በሚገናኙ ምንባቦች ተማሪዎችን ማንበብ ማለማመድ ይቻላል።

**ተደጋጋሚ ቃላዊ ንባብ፡**ይህ ተደጋጋሚ ቃላዊ ንባብ በማቅረብ ከጓደኛ፣ ከመምህራንና ከቤተሰብ ምላሽ ማግኘት።

**በጊዜ የተገደበ ተደጋጋሚ ንባብ፡** ተማሪዎች አጭር ምንባብን ብዙ ጊዜ ያነባሉ። እያንዳንዱን ንባብም በጊዜ መገደብ። የንባብ ፍጥነት ለውጥንም በቻርት ማስቀመጥ።

**የአረፍተ ነገር ቅኝት፡** አንድ አረፍተ ነገር ብዙ ጊዜ ማንበብ። በእያንዳንዱ ንባብ ጊዜ እያንዳንዱ ቃል ላይ ትኩረት መስጠት። የፊደል -ድምጽ ግንኙነት፣ ቃላት፣ አ/ነገሮች

**ለምልክቶች ትኩረት መስጠት፡**

አገላለጽን ለማሻሻል መምህር በግልጽ የምልክቶችን አላማ በመግለጽ እንዴት እነዚህ ምልክቶች በአገላለጽና በድምጸት ላይ ተጽእኖ እንደሚደርጉ ማብራራት።

**በቡድን መጻፍ፡**መምህር አርዐያ በመሆን ተማሪዎች አንድ የጋራ ንባብ እንዲጽፉ ማበረታታት።

## 4. ምዘና

- የቃል ወይም የጽሁፍ ጥያቄዎችን መጠየቅ
- አካላዊ ምላሽ፡ የተማሪዎች በግል ለጥያቄዎች አካላዊ ምላሽ መስጠት
- ኢ.መደበኛ ቁጥጥር፡ ምልከታ፣ በስዕል መወከል፣ ስልታዊ ልምምድ፣ ተራ በተራ ማቅረብ፣ የመውጫ ካርድ

## ክፍለጊዜ አንድ

# አትክልትና ፍራፍሬ

## ትምህርት አንድ፡ ማዳመጥ

መምህር ተማሪዎችዎ መጽሐፋቸውን ምዕራፍ አራት ክፍለጊዜ አንድ ገልጠው ርዕሱን እንዲያነቡ ያድርጉ። ከዚያም የተነበበሎትን ርእስ (አትክልትና ፍራፍሬ ) በጥቁር ሰሌዳ ላይ ይፃፉ። ተማሪዎቹ ስለርእሱ የሚያውቁትን እንዲያስታውሱና ትኩረታቸው እንዲሰበሰብ መማሪያ መጽሐፍ ላይ የቀረቡትን ቅድመንባብ ጥያቄዎች እንዲያነቡ ያድርጉ። ከተወሰኑ ተማሪዎች መልስ ይቀበሉ።

ተማሪዎቹ ግምታቸውን ከሚያዳምጡት መልእክት ጋር በማገናዘብ የሚነበብላቸውን ዋና ዋና ሃሳብ ለመረዳት በጥሞና ማዳመጥ እንዳለባቸው ያሳስቧቸው።

መምህር፣ ምንባቡን ሶስት ጊዜ ሊያነቡላቸው እንደሚገባ አይዘንጉ። በንባቡ መሃል *** ምልክት ባለበት ንባቡን ቆም አድርገው በትክክል ማዳመጣቸውን ለማረጋገጥና ቀጣዩን ሀሳብ እንዲገምቱ ጥያቄውን ይጠይቁ።

# አትክልትና ፍራፍሬ

የአትክልትና የፍራፍሬ ልዩ ልዩ ክፍሎች ለምግብነት ይውላሉ። አንዳንዶቹ ቅጠላቸው ይበላል። ሌሎቹ ሥራቸው ይበላል። የተቀሩት ደግሞ ፍሬያቸው ይበላል። ቅጠላቸው የሚበሉት ጥቅል ጎመን፣ አበባ ጎመን፣ ሰላጣና ቆስጣ ናቸው።

***ፍሬያቸው የሚበሉ አትክልት ምን ምን ይመስሏችኋል?***

ፍሬያቸው የሚበሉት አናናስ ብርቱካን፣ ሙዝ፣ ማንጎ፣ ፓፓያ፣ ግሽጣና የመሳሰሉት ናቸው። ሥራቸው የሚበሉት ደግሞ ካሮትና ቀይ ሥር ናቸው።

***የአትክልትና ፍራፍሬ ጥቅም ምን ይመስላችኋል?"***

**አትክልትና ፍራፍሬዎች ብዙ ጥቅሞች አላቸው። ከነዚህ ውስጥ በሽታ መከላከል አንዱ ነው። ሌላው ጥቅም ተሸጠው ገንዘብ ማስገኘታቸው ነው። በተጨማሪም ንፁህ አየር ለሰው ልጅ ይሰጣሉ። ሲያዩዋቸው ውበት ስላላቸው የመንፈስ እርካታን ያላብሳሉ። ስለዚህ አትክልትና ፍራፍሬዎችን ማምረት ብዙ ጥቅም አለው።**

*መምህር የተማሪዎችዎን አዳምጦ መረዳት ለመፈተሽ መማሪያ መጽሐፍ ላይ የቀረቡትን ሀሳቦች ባዳመጡት መሰረት ትክክል የሆነውን "እውነት"ትክክል ያልሆነውን "ሀሰት" በማለት እንዲመልሱ ያድርጉ።*

## ክፍለጊዜ ሁለት

*መምህር ተማሪዎች በክፍለጊዜ አንድ የተሰሩትን እና ከክፍለጊዜ ሁለት ትምህርት ጋር ማገናኘት እንዲችሉ ጥያቄዎች አዘጋጅተው ይጠይቁ። ቀጣዩን ስራ መከወን እንዲችሉ ተነቦላቸው የነበረውን በእለቱም በድጋሚ እንደሚያነቡላቸው ያሳውቋቸው። ንባብ ከመጀመርዎ በፊት እያዳመጡ እንዲሞሉ በመማሪያ መፅሐፋቸው ላይ ያለውን ሰንጠረዥ ወደ ደብተራቸው እንዲገለብጡ ያድርጉ። በሰንጠረዡ ምን እደሚሰሩም ይንገሯቸው። በእለቱ ንባብ ጊዜ *** ምልክት ባለበት የሚቀርበውን ጥያቄ አልፈው ታሪኩን ብቻ ሊያነቡላቸው ይችላሉ።*

## ክፍለጊዜ ሶስት

## ትምህርት ሁለት፡ መናገር

### ተግባር አንድ፡

*መምህር ተማሪዎቹ መማሪያ መጽሐፍ ላይ የቀረቡትን ጥያቄዎች ተራ በተራ በተጠየቀው መሰረት በቅደም ተከተል በቃል እንዲያቀርቡ ያድርጉ። አቀራረባቸው የጥሩ ተናጋሪ ባህሪያት የተላበሰ መሆኑን አከዋወናቸውን ይመዝኑና ተገቢውን ምጋቤ ምላሽ ይስጧቸው።*

## ክፍለጊዜ አራት

### ተግባር ሁለት፡

*መምህር፣ ተማሪዎቹ መማሪያ መጽሐፍ ላይ የቀረበውን የአትክልትና ፍራፍሬዎች ጠቀሜታ ላይ በጥንድ እንዲነጋገሩ ያመቻቹላቸው። በጥንድ ተነጋግረው ያገኟቸውን ሀሳቦች በተወካያቸው በኩል ለክፍል ተማሪዎች በቃል በሚሰጣቸው ጊዜ ውስጥ እንዲያቀርቡ ያድርጉ። ሂደቱን በመከታተል ተገቢ ድጋፍ ያድርጉላቸው።*

## ክፍለጊዜ አምስት

## ትምህርት ሶስት፡ መነጠልና ማጣመር

### መልመጃ ሶስት

### ሀ. መነጠል

መምህር ተማሪዎች በመማሪያ መጽሐፍ ላይ የቀረቡትን ቃላት በምሰሌው መሰረት ነጣጥለው መጥራት እንዲችሉ (ገ ን ዘ ብ) ነጥለው በመጥራት ያሳይዋቸው። እያንዳንዳቸውን ሲጠሩ በጭብጨባ በማጀብ መነጠላቸውን እንዲረዱ ያድርጉ። በተመሳሳይ መንገድ የተሰጡ ባለአራት ፊደል ቃላትን ለእያንዳንዱ ፊደል አንድ አንድ ጊዜ በማጨብጨብ ነጥለው ማሳየት መቻላቸውን ይከታተሉ። ለዚህ ተግባር ፍላሽ ካርድ መጠቀም ይችላሉ። እያንዳንዳቸው ቃላቱን መነጠል መቻላቸውን በግል ሰርተው እንዲያሳዩ በማድረግ ያረጋግጡ።

## ክፍለጊዜ ስድስት

### ለ. ማጣመር

መምህር ተማሪዎችዎ በመማሪያ መጽሐፍ ላይ ተነጣጥለው የቀረቡትን ፊደላት በፍጥነት አጣምረው ቃላት መናገር እንዲችሉ ያለማምዷቸው። በመጀመሪያ በቂ ምሳሌ ይስጧው። ምሳሌ ሲሰጧቸው በጥሞና እንዲከታተሉ ያድርጉ። በመቀጠል ምሳሌዎቹን ከእርስዎ ጋር በጋራ ደጋግመው እንዲሰሩ ያድርጉ። እርስዎ ነጥለው የጠሩላቸውን በህብረት ቃሉን እንዲጠሩ ያድርጉ። ቃሉን ሲጠሩ አንዴ ብቻ በማጨብጨብ መጣመሩን እንዲገነዘቡ ያድርጉ። በመጨረሻም በጋራ የሰሩትን በተናጠል መስራት መቻላቸውን ተማሪዎችን በየተራ በማሳተፍ ትምህርቱን ይመዝኑ። አስፈላጊ ድጋፍ በመስጠት ትምህርቱን ያጠናክሩ።

## ክፍለጊዜ ሰባት

## ትምህርት አራት፡ የቃላት ጥናት

### መልመጃ አራት

መምህር ተማሪዎችዎ በክፍለ ጊዜ ሰባት ስር የቀረቡትን ቃላት ከቀረበ ማብራሪያ ጋር በየግላቸው አንብበው ያዛምዱ። በግል ያዛመዱትን በጥንድ እያስተያዩ በመልሶቻቸው ላይ እንዲነጋገሩ ከዚያ እርስዎ ሀሳቡን እያነበቡላቸው ከሀሳቡ የሚዛመድ ቃል እጅ በማውጣት በተናጠል እንዲመልሱ በማድረግ ያሳትፏቸው። በዚህ ተሳትፏቸውም መረዳታቸውን ያረጋግጡ።

## ክፍለጊዜ ስምንት

## ድምጽ በመተው ማንበብ

## መልመጃ አምስት

### ሀ. መግደፍ

መምህር በመማሪያ መጽሐፍ ላይ በቀረበ ምሳሌ መሰረት የመጀመሪያውን ድምጽ/ፊደል በመተው አዲስ የሚፈጠሩ ቃላት እንዲያነቡ ምሳሌዎች በመስጠት ያዘጋጇቸው። በመቀጠል በየተራ መማሪያ መጽሐፍ ላይ ከቀረቡት ቃላት የመጀመሪያውን ድምጽ/ፊደል በመተው በቃል እንዲያቀርቡ ያድርጉ። የተማሪዎቹን መልስ ጥቁር ሰሌዳ ላይ በመጻፍ ትክክለኛውን መልስ የመለየት ስራ በቃላቱ ቅደም ተከተል መሰረት ያሰሯቸው።

## ክፍለጊዜ ዘጠኝ

### ለ. ከመጀመሪያ ድምፅ/ፊደል መጨመር

መምህር በመማሪያ መጽሐፍ ላይ በቀረበው ምሳሌ መሰረት አንድ ድምፅ/ፊደል በቀረቡት ቃላት መጀመሪያ ላይ በመጨመር ቃላቱን በቃል እንዲያቀርቡ ያድርጉ። የተማሪዎቹን መልስ ጥቁር ሰሌዳ ላይ በመጻፍ ትክክለኛውን መልስ  የመለየት ስራ በቃላቱ ቅደም ተከተል መሰረት ያሰሯቸው።

## ክፍለጊዜ አስር

### ሐ. በምሳሌው መሰረት ይስሩ።

መምህር በመማሪያ መጽሐፍ ላይ በቀረበው ምሳሌ መሰረት ቃላቱን እንዲያነቡ በቂ ምሳሌዎችን በመስጠት ያዘጋጇቸው። በመቀጠል በየተራ መማሪያ መጽሐፍ ላይ የቀረቡትን ቃላት በማርባት በቃል እንዲያቀርቡ ያድርጉ። የተማሪዎቹን መልስ ጥቁር ሰሌዳ ላይ በመጻፍ ትክክለኛውን መልስ  የመለየት ስራ በቃላቱ ቅደም ተከተል መሰረት ያሰሯቸው።

## ክፍለጊዜ አስራ አንድ

### መ. መነሻ ቅጥያ መነጠል

መምህር በመማሪያ መጽሐፍ ላይ በቀረበው ምሳሌ መሰረት የቃላቱን መነሻ ቅጥያ መነጠል እንዲችሉ በቂ ምሳሌዎችን በመስጠት ያዘጋጇቸው። በመቀጠል በየተራ መማሪያ መጽሐፍ ላይ ከቀረቡትን ቃላት መነሻ ቅጥያ ለመነጠል በጥንድ እንዲወያዩ ያድርጉ። የተወያዩበትን አንድ በአንድ በቃል እንዲያቀርቡ ያድርጉ። የተማሪዎቹን መልስ ጥቁር ሰሌዳ ላይ በመጻፍ ትክክለኛውን መልስ  የመለየት ስራ በቃላቱ ቅደም ተከተል መሰረት ያሰሯቸው።

## ክፍለጊዜ አስራ ሁለት

## ድምጽ መተካት

## መልመጃ ስድስት

### ሀ. የመጀመሪያ ድምጽ/ፊደል መተካት

መምህር በመማሪያ መጽሐፍ ላይ በቀረበው ምሳሌ መሰረት የመጀመሪያውን ድምጽ/ፊደል በመተካት አዲስ የሚፈጠሩ ቃላት እንዲያነቡ ምሳሌዎች በመስጠት ያዘጋጇቸው። በመቀጠል በየተራ መማሪያ መጽሐፍ ላይ የቀረቡትን መነሻ ድምጽ/ፊደል በመተካት በቃል እንዲያቀርቡ ያድርጉ። የተማሪዎቹን መልስ ጥቁር ሰሌዳ ላይ በመጻፍ ትክክለኛውን መልስ የመለየት ስራ በቃላቱ ቅደም ተከተል መሰረት ያሰሯቸው።

## ክፍለጊዜ አስራ ሶስት

### ለ. የመሃል ድምጽ/ፊደል መተካት

መምህር በመማሪያ መጽሐፍ ላይ በቀረበው ምሳሌ መሰረት የቃል መሃል ድምጽ/ፊደል በመተካት አዲስ የሚፈጠሩ ቃላት እንዲያነቡ ምሳሌዎች በመስጠት ያዘጋጇቸው። በመቀጠል በየተራ መማሪያ መጽሐፍ ላይ የቀረቡትን የቃል መሃል ድምጽ/ፊደል በመተካት በቃል እንዲያቀርቡ ያድርጉ። የተማሪዎቹን መልስ ጥቁር ሰሌዳ ላይ በመጻፍ ትክክለኛውን መልስ የመለየት ስራ በቃላቱ ቅደም ተከተል መሰረት ያሰሯቸው።

*ማሳሰቢያ፡ በመተካት የሚፈጠሩት ቃላት ከአንድ በላይ ሊሆኑ ይችላሉ።*

## ክፍለጊዜ አስራ አራት

## ትምህርት አምስት፡ ማንበብ

## የአትክልት ቦታ ዝግጅት

**መምህር** ተማሪዎች መፅሐፋቸውን ክፍለጊዜ አስራ አራትን እንዲያወጡ ያድርጉ። ርዕሱን እንዲያነቡ ያድርጉና ርዕሱን (የአትክልት ቦታ ዝግጅት) ጥቁር ሰሌዳ ላይ ይፃፉት። በመቀጠልም መማሪያ መጽሐፍ ላይ ያሉትን ቅድመንባብ ጥያቄዎች እጅ በማውጣት በየተራ እንዲመልሱ በመጠየቅ ከተወሰኑ ተማሪዎች መልስ ይቀበሉ።

**መምህር** እባኮ ተማሪዎቹ ድምጽ ሳያሰሙ በግላቸው፣ ምንባቡን እንዲያነቡ ያድርጉ። ንባባቸውን ይከታተሉ። በመማሪያ መጽሐፍ ላይ በአንብቦ መረዳት (መልመጃ ሰባት "ሀ") ስር የቀረቡትን ጥያቄዎች ሁለት ሁለት ሆነው እየተወያዩ እንዲሰሩ ያድርጉ። የውይይቱን

ሂደት ይመልከቱና አስፈላጊውን ድጋፍ ያድርጉላቸው።

## ክፍለጊዜ አስራ አምስት

**መምህር፣** ተማሪዎች መፅሐፋቸውን ክፍለጊዜ አስራ አምስትን እንዲያወጡ ያድርጉ። በክፍለጊዜው ስር ከቀረቡት አማራጭ ቃላት ውስጥ በመምረጥ ባዶ ቦታዎቹን በተስማሚ ቃላት በጥንድ እየተወያዩ እንዲሞሉ ያድርጉ። በጥንድ የሞሉትን ለክፍል በማቅረብ ትክክለኛ መልስ ማግኘት እንዲቻል ተራ በተራ እጅ በማውጣት እንዲሳተፉ ያድርጉ። ከተለያዩ ተማሪዎች የሚሰጠውን መልስ ጥቁር ሰሌዳ ላይ በመጻፍ ትክክለኛውን አማራጭ እንዲያውቁ ያድርጉ።

## ክፍለጊዜ አስራ ስድስት

### መልመጃ ስምንት

መምህር በ"ሀ" ስር ለቀረቡት ቃላትና ሀረጋት በምንባቡ መሰረት ፍቺ የሚሆኑ ከ "ለ" ስር በመፈልግ እንዲያዛምዱ ያድርጉ። ከምንባቡ ቃላትን ለመፈለግና ፍቺያቸውን ለመገንዘብ በቂ ጊዜ ይሰጣቸው። ተማሪዎቹ መልሶቹን ለማመልከት በ"ሀ" እና "ለ" ስር የቀረቡትን ቃላትና ሀረጋት ወደ ደብተራቸው እንዲገለብጡ ይደረግ። የገለበጡትን በመስመር በማገናኘት ትክክለኛውን አማራጭ ያመልክቱ።

## ክፍለጊዜ አስራ ሰባት

### መልመጃ ዘጠኝ

ተማሪዎቹ ለክፍለጊዜው የቀረቡትን አረፍተነገሮች በተገቢ ፍጥነት በተደጋጋሚ እንዲያነቡት በማድረግ ስለፍጥነታቸው፣ ቅላጼና ትክክለኝነት መረጃ ይያዝ።

## ክፍለጊዜ አስራ ስምንት

### ትምህርት ስድስት፡ መፃፍ

መምህር ተማሪዎችዎ በመማሪያ መጽሐፍ ላይ የቀረቡትን አረፍተነገሮች በተገቢ ስርአተነጥብ አሟልተው ደብተራቸው ላይ እንዲጽፉ ያድርጉ። ግንዛቤያቸው እንዲሰፋ በጥንድ እየተነጋገሩ እንዲሰሩ ይመቻችላቸው። በመቀጠል በጥንድ ተቀናጅተው ከሰሩት ተማሪዎች የተለያዩ የናሙና መልሶችን ይቀበሉ። ከተማሪዎቹ የሚቀበሉትን መልሶች ሰሌዳ ላይ ይጻፉ። ስለትክክለኝነቱ ሌሎች ተማሪዎች ሀሳብ እንዲሰጡበትም ያድርጉ።

# ምዕራፍ አምስት

# የአከባቢ ጽዳት

(18 ክፍለ ጊዜ)

## 1. ከትምህርቱ የሚጠበቁ ውጤቶች

- ከሚያዳምጡት ነገር አዳዲስ ቃላትን ይሰጣሉ፤
- ከሚያነቡት ጽሁፍ ዝርዝር ሀሳቦችን ይገልጻሉ፤
- ቃለአጋኖንና የጥያቄ ምልክትን ይለያሉ፤
- አራት ነጥብን በአረፍተነገር ውስጥ ይጠቀማሉ።

## 2. ዝርዝር ይዘቶች

- ማዳመጥና መናገር
- ድምጻዊ ግንዛቤ
- የትዕምርተ ድምጽ ግንዛቤ
- የቃላት ጥናት፡ተዘውታሪ(የትምህርት)ቃላት -ጽንሰሃሳቦችን መሰየም
- ማንበብና መጻፍ
    - ማንበብ፡ትክክለኛነት፣ፍጥነት፣ጥሩ አገላለጽ፣አንብቦ መረዳት
- መጻፍ፡ትክክለኛነት
    - ድምጸታዊ ግንዛቤ

## 3. የማስተማሪያ ብልሀቶችና መሳሪያዎች

መምህራን የተማሪዎችን የቀደመ እውቀት ያነሳሳሉ። በተማሪዎች የሚሞሉ ቻርቶች ያዘጋጃሉ። ተማሪዎች ከሚያዳምጡት ነገር ቻርቱን እንዲሞሉ ያደርጋሉ።

**መነጠልና ማጣመር**፡ ተማሪዎች በቃል ውስጥ ያለውን ድምጽ በፍጥነት ይጠራሉ።(መምህር ማጣመርን ለማሳየት የተነጣጠሉ ፊደላትን አጣምረው ያሳያሉ። ከዚያም መነጠልን ለማሳየት ቀለሞችን/ድምጾችን በተናጠል ይጠራሉ።

**ማተካካት**፡ መምህር ተማሪዎች በጨዋታ እንዲወዳደሩ በቡድን ያስቀምጧቸዋል። በየተራ ከቃላት ላይ ድምጾችን/ቀለማትን የመግደፍ፣ የመጨመርና የማተካካት ጨዋታ እንዲጫወቱ መንገር። ጨዋታውን ለማጠናቀቅ የሚፈጀው ጊዜ በተማሪዎቹ

አረዳደድ ላይ ይመሰረታል። ጨዋታውን ቀድሞ ያጠናቀቀ ነጥብ ያገኛል። ይህም ጨዋታውን በተነሳሽነት እንዲሳተፉ ያደርጋል። ጨዋታው ሰዓት አስከባሪ፣ ውጤት መዝጋቢና መሪ ይኖረዋል።

**ሀ.መግደፍ** -ተማሪዎች ቃላቱን ካነበቡ በኋላ በቃሉ መነሻ ላይ ያለውን ቀለም/ድምጽ በመተው መጥራት።

**ለ. መጨመር**-ተማሪዎች ቃላቱን ካዳመጡ በኋላ ቀለሞችን /ድምጾችን መጨመር።

**ሐ.መተካት**-ተማሪዎች ካዳመጡ በኋላ በቃሉ ላይ ያሉትን ቀለማትን/ድምጾችን መቀየር

**መናገር**፡ መምህር ቃሉን ካሳዩ በኋላ በቃሉ ውስጥ ያሉትን ድምጾች ይጠሩና ድምጾቹን ይነጥላሉ(የታወቁ ትዕምርተ ድምጽ ግንዛቤን ይጠቀሙ)ተማሪዎች ቃልን ወስደው ድምጾችን መነጠል ይለማመዳሉ(የታወቁ ትዕምርተ ድምጽ ግንዛቤን ተጠቅመው)

**በቃል መጻፍ**፡ መምህር በግድግዳ ላይ ያሉትን ቃላት ያነባሉ። ተማሪዎች አዳምጠው በትክክል ይጽፋሉ። (የድምጾችን/የፊደላትን ቅርጽ፣ የባለቀለም ወረቀት ፣የካርቱን ስዕሎች፣ የቃላት ካርድ፣ ሰሌዳ መጠቀም)

**ከምንባቡ ጋር ማገናኘት**፡ ተማሪዎች ማንበብን ይለማመዳሉ።

**ተደጋጋሚ ቃላዊ ንባብ**፡ ይህ ተደጋጋሚ ቃላዊ ንባብ በማቅረብ ከጓደኛ፣ ከመምህራንና ከቤተሰብ ምላሽ ማግኘት።

**በጊዜ የተገደበ ተደጋጋሚ ንባብ**፡ ተማሪዎች አጭር ምንባብን ብዙ ጊዜ ያነባሉ። እያንዳንዱ ንባብም በጊዜ ይገድባል። የንባብ ፍጥነት ለውጡንም በቻርት ማስቀመጥ።

**ለምልክቶች ትኩረት መስጠት**፡

አገላለጽን ለማሻሻል መምህር በግልጽ የምልክቶችን አላማ በመግለጽ እንዴት እነዚህ ምልክቶች በአገላለጽና በድምጸት ላይ ተጽእኖ እንደሚያደርጉ ማብራራት።

**በቡድን መጻፍ**፡ መምህር አርአያ በመሆን ተማሪዎች አንድ የጋራ ንባብ እንዲጽፉ ማብራራት፤ በጽሁፉ ውስጥ አራት ነጥብን መጠቀም።

## 4. ምዘና

- በጽሁፍ/በቃል ጥያቄዎችን መጠየቅ
- አካላዊ ምላሽ፡ ተማሪዎች በግል ለጥያቄዎች የሚመልሱት አካላዊ ምላሽ

- ኢ-መደበኛ ቁጥጥር፡ (ምልከታ፣ በስዕል መወከል፣ ተራ በተራ ማቅረብ፣ስልታዊ ልምምድ፣ የመውጫ ካርድ መጠቀም)

## ክፍለጊዜ አንድ

## ትምህርት አንድ፡ ማዳመጥ

መምህር፣ በመጀመሪያ በእለቱ የሚደመጠውን ርእስ (የነአየለ ግቢ) የሚለውን ተማሪዎችዎ ከመፅሐፋቸው ላይ እንዲያነቡ የድርጉ። የተነበበሎትን ርዕስ ጥቁር ሰሌዳ ላይ ይጻፉ። ተማሪዎቹ ስለርእሱ እንዲገምቱና የቀደመ እውቀታቸውን እንዲጠቀሙ እንዲሁም ትኩረታቸው እንዲሰበሰብ በመማሪያ መፅሐፍ ላይ ያሉትን ጥያቄዎች ያሰሯቸው።

መምህር ከቅድመማዳመጥ ጥያቄዎች ማሰራት በኋላ ማንበብ ከመጀመርዎ በፊት ተማሪዎቹ የማዳመጥ ጊዜ ጥያቄዎችን ወደ ደብተራቸው እንዲገለብጡ ያድርጉ። የገለበጡትን ጥያቄዎች እንዲያነቡ ጊዜ ይስጧቸው። ገልብጠው ለአነበቡት ጥያቄዎች መልስ የሚያገኙት እያዳመጡ እንደሆነ ያሳውቋቸው። የማዳመጥ ጊዜ ጥያቄ*** ምልክት ባለበት ቦታ ማንበቡን ቆም አድርገው ይጠይቁ። ከተወሰኑ ተማሪዎች መልስ ከተቀበሉ በኋላ ግምታቸውን ለማረጋገጥ በጥሞና ማዳመጡን መቀጠል እንዳለባቸው ያሳስቡ።

# የነአየለ ግቢ

አየለና ባለቤቱ ግቢያቸው መቆሸሹ አሳስቧቸዋል። አንድ ቀን አየለ ግቢውን **ሲቃኝ** አንድ አገልግሎት የማይሰጥ የፕላስቲክ ልብስ ማጠቢያ ተጥሎ አየ። የልብስ ማጠቢያው ውሃ **አቁሯል**። ተጠግቶ ሲመለከት ቢንቢዎች ተራብተውበታል። ማታ ማታ የሚያስቸግሯቸው ቢንቢዎች ከዚያ እየተነሱ እንደሆነ አወቀ። ማስወገድም እንዳለበትም አመነ።

*** እንዴት የሚያስወግደው ይመስላችኋል?***

ማጠቢያውን ማቃጠል ለአየር **ብክለት** ምክንያት እንደሚሆን አንድ ወቅት በሬዲዮ ሲነገር ሰምቷል። ስለዚህ ማቃጠል እንደሌለበት አሰበ። ከዚያም የሚወገድበትን ሲያስብ ባለቤቱ ማጠቢያውን በአፈር መሙላት እነደሚቻል ሃሳብ አቀረበች። ሃሳቡም የተሸለ እንደሆነ ተገነዘበ። ስለዚህ ማጠቢያውን በአፈር ሞሉ። ቢንቢዎቹም መራቢያ አጡ። በመጨረሻም እንዴት ጥቅም ላይ እንደሚያውሉ ሲያስቡ ለአትክልት መትከያ ማዋል እንደሚችል ተረዱ። የሰላጣ ችግኝ ገዝተው ተከሉበት። ሰላጣውን መንከባከብ የየእለት ተግባራቸው አደረጉ። በሚያዩት ለውጥ ደስተኛ ሆኑ። ከቢንቢዎቹ ከመገላገላቸውም በላይ ቦታው **ማራኪ** ሆነላቸው።

## ክፍለጊዜ ሁለት

## መልመጃ አንድ

መምህር መልመጃ አንድን ከማሰራትዎ በፊት ለመልመጃው አሰራር እንዲረዳቸው ታሪኩን ለማስታወስ አንድ ጊዜ እንደሚያነቡላቸውና በጥሞና ማዳመጥ እንደለባቸው ያሳውቋቸው።

ሀ. ታሪኩን በድጋሚ ካነበቡላቸው በኋላ መልመጃ አንድ "ሀ"ን እጅ እያወጡ በቃል እንዲ መልሱ ያድርጉ። መልሱ ትክክል ቢሆንም ከአንድ ተማሪ ብቻ አይቀበሉ፤ የተለያዩ ሀሳቦችም ሊኖሩ ስለሚችሉ።

ለ. **መምህር** መልመጃ አንድ "ለ"ን በተነበበላቸው ታሪክ መሰረት ትክክል የሆነውን "እውነት" ትክክል ያልሆነውን "ሐሰት" በማት ሶስት አባላት ባሉት ቡድን እንዲመልሱ በቡድን ያደራጇቸው። በቡድን ከሰሩ በኋላ የተለያየ ቡድን አባላት የተስማሙበትን መልስ እጅ እያወጡ እንዲመልሱ ያድርጉ። የቀረቡትን መልሶች ጥቁር ሰሌዳ ላይ በመጻፍ በትክክለኝነቱ ላይ ተማሪዎች ሀሳብ እንዲሰጡ ያድርጉ።

## ክፍለጊዜ ሶስት

ሐ. መምህር ተማሪዎቹ ባዳመጡት መሰረት ባዶ ቦታዎቹን የሚያሟሉትን በጥንድ ሆነው በመምረጥ እንዲመልሱ ይምሯቸው። ተማሪዎቹ ሲሰሩ በትክክለኛ ሂደት ላይ መሆናቸውን ይከታተሉ። በጥንድ ከሰሩ በኋላ ተሳትፏቸው ዝቅተኛ የሆነ ተማሪዎች እንዲመልሱ በመጠየቅ ያሳትፏቸው። የቀረቡትን መልሶች ጥቁር ሰሌዳ ላይ በመጻፍ በትክክለኝነቱ ላይ ተማሪዎች ሀሳብ እንዲሰጡ ያድርጉ።

## ክፍለጊዜ አራት

## ትምህርት ሁለት፡ መናገር

## ተግባር አንድ

መምህር በተማሪዎቹ ቤት አካባቢ በመጣላቸው ምክንያት ጉዳት ሊያስከትሉ የሚችሉ ነገሮች ምን ምን እንደሆኑ በየተራ እየተነሱ ለክፍል ተማሪዎች እንዲናገሩና የንግግር ልምምድ እንዲያደርጉ በየተራ ያሳትፏቸው። የጾታ ተሳትፎ፣ ገጠርና ከተማን የማካተት ጉዳይ ከግምት ይግባ።

## የቤት ስራ

መምህር ተማሪዎቹ በአካባቢያቸው አገልግሎታቸው በማብቃቱ ከሚጣሉ ነገሮች ውስጥ በሌላ መልክ አገልግሎት ሊሰጡ የሚችሉ ነገሮች ምን ምን እንደሆኑ ቤተሰባቸውን

*በመጠየቅ ለይተው እንዲመጡ የቤት ስራ ይስጧቸው።*

## ክፍለጊዜ አምስት

## ተግባር ሁለት

*ሀ. መምህር በተማሪዎቹ አካባቢ አገልግሎታቸው በማብቃቱ ከሚጣሉ ነገሮች ውስጥ በሌላ መልክ አገልግሎት ሊሰጡ የሚችሉ ነገሮች ምን ምን እንደሆኑ ቤተሰባቸውን በመጠየቅ ለይተው የመጡትን ጥንድ ጥንድ በመሆን እንዲወያዩበት ያድርጉ። የተወያዩባቸውንና ልምድ የተለዋወጡባቸውን ለክፍል ተማሪዎች እንዲነግሩ ያመቻቹላቸው። ተማሪዎቹ ተግባሩን ሲከውኑ በትክክለኛ ሂደት ላይ መሆናቸውን ይከታተሉ።*

## ክፍለጊዜ ስድስት

*ለ. ሀሳብ አሰባስቦ ለክፍል ተማሪዎች ማካፈል*

*መምህር ተማሪዎች በሚከተሉት ነጥቦች ላይ ሃሳብ አሰባስበው ያገኙትን ለክፍል ተማሪዎች በንግግር እንዲያቀርቡ ግልጽ መመሪያና የመስሪያ ጊዜ ይስጧቸው።*

የተጣሉና አከባቢን ሊበክሉ የሚችሉ ነገሮችን ይለዩ። የለዩትን እንዴት ማስወገድ እንደሚቻል ያስቡ። እንዴት እንደሚወገድና ስራ ላይ ማዋል እንደሚቻል ያላቸውን ሀሳብ አቀናጅተው ለክፍል ተማሪዎች ይንገሩ።

## ክፍለጊዜ ሰባት

ሐ. ግቢያቸው ቢቆሸሽ ምን ጉዳት ሊያመጣ እንደሚችል ያስቡ። ያሰቡትን ጉዳት እንዴት ማስቀረት እንደሚቻል ሀሳባቸውን ለክፍል ተማሪዎች ቆመው ይግለጹ።

## ክፍለጊዜ ስምንት

## ትምህርት ሶስት፡ መነጠልና ማጣመር

## መልመጃ ሁለት

### ሀ. መነጠል

*መምህር የመነጠልን ተግባር ደጋግመው እንደሰሩት በማስታወስ መማሪያ መጽሐፉ ላይ የቀረቡትን ቃላት ወደተገቢ ድምጾች በፍጥነት ነጥለው አንድ ባንድ እያጨበጨቡ በመጥራት ግንዛቤያቸውን እንዲያንጸባርቁ በማድረግ ትክክለኝነታቸውን ይከታተሉ። አስፈላጊውን እገዛም ያድርጉላቸው።*

## ክፍለጊዜ ዘጠኝ

### ለ. ማጣመር

መምህር የማጠመርን ተግባር ደጋግመው እንደሰሩት ተማሪዎችዎን ያስታውሷቸው። አያይዘውም በመማሪያ መጽሐፉ ላይ ተነጣጥለው የቀረቡትን ድምጾች አንድ ባንድ እያጨበጨቡና እየጠሩ ድምጾቹን በፍጥነት አጣምረው ቃሉን እንዲጠሩ ያድርጉ። ተግባሩን ተማሪዎችን በማስነሳት አንድ ባንድ እንዲተገብሩት ያድርጉ። ተግባሩን ለመከወን የራሳቸውን ፈጠራ ተጠቅመው በፍላሽ ካርድ ወይም በቅርበት በሚያገኙት ነገር እንዲተገብሩት ያነሳሷቸው።

## ክፍለጊዜ አስር

## ትምህርት አራት፡ የቃል ጥናት

## መልመጃ ሶስት

### ሀ.የጎደሉትን ፊደላት መሙላት

መምህር ተማሪዎች በምሳሌው መሰረት የተለያዩ ፊደላትን በጅምር ቃላት መጀመሪያ ላይ በመጨመር ቃላትን እንዲመሰርቱ ምሳሌ ይስጧቸው። በምሳሌው መሰረት በጥንድ ሆነው ከአስራ አምስት ደቂቃ ባልበለጠ ጊዜ ውስጥ የሚቻላቸውን የቃላት ብዛት እንዲመሰርቱ ይደረግ። በመቀጠል ከፍተኛውን ቁጥር ከመሰረተ ቡድን በመጀመር የተሰጡትን መልሶች ጥቁር ሰሌዳ ላይ እየጻፉ ትክክለኘነታቸውን እያረጋገጡ ማሰራት። በስተመጨረሻ ትክክለኘነታቸው የተረጋገጠ ቃለት ወደ ደብተራቸው እንዲገለብጡ በማድረግ የቃላት እውቀታቸው እንዲዳብር ማመቻቸት።

ምሳሌ፡ __ ለጠ = ገለጠ መለጠ በለጠ

## ክፍለጊዜ አስራ አንድ

ለ. መምህር ከዚህ በላይ በ “ሀ” ስር በሰሩት መሰረት በቃል መጨረሻ ፊደል በመጨመር ቃላትን እንዲመሰርቱ ይምሯቸው።

**ምሳሌ፡ መጽሐ__ =** መጽሐፍ

ሐ. መምህር ከዚህ በላይ በ “ሀ” እና በ “**ለ**” ስር በሰሩት መሰረት በቃል መሃል ፊደል በመጨመር ቃላትን እንዲመሰርቱ ይምሯቸው።

**ምሳሌ፡ ሰ__ ዳ** = ሰሌዳ

## ክፍለጊዜ አስራ ሁለት

# መልመጃ አራት

## ድምጽ ወይም ፊደል በመግደፍ ፈጥኖ መናገር

መምህር እርስዎ ከሚያነቡላቸው ቃላት ውስጥ ድምጽ ወይም ፊደል በመተው እጅ በማውጣት ቃል እንዲጠሩ በማድረግ ያሳትፏቸው።

**ሀ. የመጀመሪያ ድምጽ/ፊደል በመተው ፈጥነው እጅ በማውጣት እንዲሳተፉ መመሪያ ይስጧቸው።**

መምህር ተማሪዎች ከሚነበብላቸው ቃላት ውስጥ ቀለማት ወይም ድምጽ በመግደፍ አዳዲስ ቃላት እንዲመሰርቱ በቂ ምሳሌ በመስጠት ያለማምዷቸው። በዚህም የድምጽ ግንዛቤያቸውን እንዲያዳብሩ ከመነሻ በመግደፍ እንዲለማመዱ ቃላትን ያንብቡላቸው። እርስዎን ተከትለው ከተነበበላቸው ቃል ላይ ድምጽ ወይም ቀለም በመግደፍ ቃል እንዲፈጥሩ ግልጽ መመሪያ ይስጧቸው።

**ምሳሌ፡** 1. አሮጠ ⟶ ሮጠ

5. አጠና ⟶ "ጠና"

**ለተማሪዎች የሚነበቡ ቃላት**

| | | | |
|---|---|---|---|
| 1. አበራ | 2. አበላ | 3. አመጣች | 4. አኖረች |
| 5. ተራራ | 6. መጻፍ | 7. መውሰድ | 8. ውስጥ |

## ክፍለጊዜ አስራ ሶስት

**ለ. የመጨረሻ ድምጽ/ፊደል በመተው ፈጥነው እጅ በማውጣት እንዲሳተፉ መመሪያ ይስጧቸው።**

**ምሳሌ፡** መጣች መጣ

**ለተማሪዎች የሚነበቡ ቃላት**

| | | | |
|---|---|---|---|
| 1. ሰራን | 2. ፈራሁ | 3. ሄደች | 4. በራፍ |
| 5. ጋለበ | 6. መራት | 7. ጠራው | 8. ብስና |

## ክፍለጊዜ አስራ አራት

**ሐ. የመሃል ድምጽ/ፊደል በመተው ፈጥነው እጅ በማውጣት እንዲሳተፉ መመሪያ ይስጧቸው።**

ምሳሌ "አደረሰ" ከሚለው ቃል ውስጥ

"ደ" ቢተው "አረሰ"

"ረ" ቢተው" "አደሰ"

**ለተማሪዎች የሚነበቡ ቃላት**

| | | | |
|---|---|---|---|
| 1. ምርት | 2. ደብተር | 3. አበጠረ | 4. አበሰረ |
| 5. ገሰገሰ | 6. መራባት | 7. ጠራችው | 8. አጠገበ |

## ክፍለጊዜ አስራ አምስት

መ. ከሚነበቡላቸው ቃላት ውስጥ ካሉ ፊደላት አንዱን በመተካት በፍጥነት እንዲሳተፉ መመሪያ ይስጧቸው። ተማሪዎች እጅ ሲያወጡ የተናገሩትን ቃል ሰሌዳ ላይ በመጻፍ የትኛው እንደ ተተካ ተማሪዎች እንዲለዩ እድል ይፍጠሩላቸው።

በመጀመሪያ የቀረበውንና እንዳስፈላጊነቱ ተጨማሪ ምሳሌ በመስጠት ያዘጋጇቸው።

ምሳሌ 1. በራ ⟶ መራ/ሰራ

2. ወሰደ ⟶ ወረደ/ወለደ/ማለደ/ወሰነ

**ለተማሪዎች የሚነበቡ ቃላት**

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| 1. ውስጥ | 2. ሄደች | 3. ሰራን | 4. ፈራሁ | 5. ጠራው |
| 6. አበጠረ | 7. አመጣች | 8. አጠገበ | 9. መራባት | |

ሠ. ፊደላቱን ከሰንጠረዥ በመምረጥና በማጣመር አስር ቃላት እንዲመሰርቱ ምሳሌ በመስጠት ያዘጋጇቸው። ምሳሌ፡- ጠ + ራ ጠራ

## ክፍለጊዜ አስራ ስድስት

# ትምህርት አምስት፡ማንበብ

# መልመጃ አምስት

መምህር ተማሪዎች መፅሐፋቸውን ክፍለጊዜ አስራ ስድስትን እንዲያወጡ ያድርጉ። የቀረቡትን ምስሎች ተመልክተው በመማሪያ መጽሐፍ ላይ ያሉትን የቅድመንባብ

ጥያቄዎች እጅ በማውጣት በየተራ እንዲመልሱ በመጠየቅ ከተወሰኑ ተማሪዎች ላይ መልስ ይቀበሉ። ግምታቸውን ለማረጋገጥ ጽሁፉን ማንበብ እንዳለባቸው በማሳሰብ በጸጥታ በሚሰጣቸው ጊዜ ውስጥ እንዲያነቡ ያድርጉ።

መምህር እባኮ ተማሪዎቹ ድምጽ ሳያሰሙ በግላቸው፣ እንዲያነቡ ያድርጉ። አነባበባቸውን ይከታተሉ። በሚያስፈልግበት ድጋፍ በመስጠት ያበረታቷቸው። አንብበው ካጠናቀቁ በኋላ አንብቦ መረዳታቸውን ለመፈተሽ በመማሪያ መጽሐፉ ላይ የቀረበውን መልመጃ ትክክል የሆነውን "እውነት"፣ትክክል ያልሆነውን "ሀሰት" በማለት እንዲመልሱ ያደርጉ።

## ክፍለጊዜ አስራ ሰባት

### መልመጃ ሰባት

መምህር በመማሪያ መጽሐፍ ላይ ለክፍለጊዜው የቀረቡትን አረፍተነገሮች በየተራ እያስነበቡ በትክክለኛው ቅላጼና ለክፍል ደረጃው በሚመጥን ፍጥነት ማንበባቸውን ይከታተሉ። አስፈላጊውን እገዛም ያድርጉላቸው።

## ክፍለጊዜ አስራ ስምንት

### ትምህርት ስድስት፡ መጻፍ

### ተግባር ሶስት

**ሀ.** መምህር ተማሪዎች በትክክል መጻፋቸውን ለመከታተል የሚከተሉትን ቃላት በቃል የስጽፏቸው። የጻፉትን በጥንድ ተለዋውጠው እንዲያነቡ ያድርጉ። ትክክለኛውን ጥቁር ሰሌዳ ላይ በመጻፍ እንዲያስተካክሉም ያግዟቸው።

1. አካባቢ 2. ሰፈራችን 3. ንጽህናቸው 4. ተህዋሲያን

**ለ. በቡድን መጻፍ**

**መምህር**፣ ተማሪዎችን ከአምስት ተማሪ ባልበለጠ ቡድን ያደራጇቸው። በቡድናቸው ሆነው **"ንጹህ አካባቢ"ን** በተመለከተ ተወያይተው ከአምስት አረፍተነገር ባለበለጠ አጭር ጽሑፍ እንዲያዘጋጁ ያድርጉ። ያዘጋጁትን ጽሁፍ በየተራ ለሌሎች ቡድኖች ያንብቡ።

# ምዕራፍ ስድስት

# ባህላዊ ሙዚቃ

(18 ክፍለ ጊዜ)

## 1. ከትምህርቱ የሚጠበቁ ውጤቶች

ከዚህ ምዕራፍ ትምህርት በኋላ ተማሪዎች

- በማዳመጥ በተዘውታሪ ቃላት ቀላል አረፍተ ነገሮችን ይገነባሉ፤
- የተዘውታሪ ቃላትን ትርጉም በምንባቡ መሰረት ይለያሉ፤
- ቃለአጋኖና ጥያቄ ምልክትን ይጠቀማሉ፤
- ቅጥያዎችን ቃላት ላይ በመጨመር ይናገራሉ።

## 2. ዝርዝር ይዘቶች

- ማዳመጥና መናገር
- ድምጻዊ ግንዛቤ
- የትዕምርተ ድምጽ ግንዛቤ
- የቃላት ጥናት፡ ተዘውታሪ(የትምህርት)ቃላት -ጽንሰሃሳቦችን መሰየም
- ማንበብና መጻፍ ማንበብ፡ትክክለኛነት፣ፍጥነት፣ጥሩ አገላለጽ፣ አንብቦ መረዳት
- መጻፍ፡ አዳምጦ በትክክለኛ ፊደል መጻፍ

## 3. የማስተማሪያ ብልሀቶችና መሳሪያዎች

መምህር የተማሪዎችን የቀደመ እውቀት ተጠቅመው ያነሳሷቸዋል። የተወሰኑ ቅድመ ማዳመጥ ጥያቄዎችን መጠየቅ። ምንባቡን ድምጽ ከፍ አድርገው ያነቡላቸዋል። ተማሪዎችን በቡድን ያስቀምጣሉ። በደብተራቸውም ላይ ካዳመጡት ምንባብ አንድ ሀሳብ እንዲጽፉ ያደርጓቸዋል።

**ማጣመርና መነጠል፡** ተማሪዎች በአንድ ቃል ውስጥ ያሉ ድምጾችን ጠርተው ቃሉን በፍጥነት ይላሉ። (መምህር ማጣመርን ለማሳየት በተናጠል የቀረቡትን ፊደላት በማያያዝ ያሳይዋቸዋል። ከዚያም መነጠልን ለማሳየት ቀለሞችን/ ድምጾችን አንድ ባንድ መጥራት) (የድምጾችን/የፊደላትን ቅርጽ፣ የባለቀለም ወረቀት፣ የካርቱን ስዕሎች፣ የቃላት ካርድ፣ ሰሌዳ መጠቀም)

**መለየት፡**ተማሪዎች ቃላት በተመሳሳይ ድምጽ የሚጀምሩና የሚጨርሱ መሆናቸውን

ይወስናሉ።

**ተመሳሳይ ዜማ፡** ተማሪዎች ተመሳሳይ ዜማ ያላቸውን ቤተሰባዊ ቃላትን መጥራት።

**ቃላትን መመስረት፡** ተማሪዎች መጻፍን መለማመድ።

**ተዘውታሪ ቃላት፡** ተማሪዎች ከፍተኛ ድግግሞሽ ያላቸውን ቃላት ከምንባቡ ውስጥም ሆነ ውጭ ፈጥኖ የመለየት ልምድ ማዳበር።

**በቃል መጻፍ፡** መምህር ተማሪዎች በቃል የሚጽፏቸውን ሁለት አረፍተ ነገሮች ማዘጋጀት። ተማሪዎችም መምህር የሚያነቡላቸውን አረፍተነገሮች በማዳመጥ በትክክል መጻፍ።

**ግድግዳ ላይ የተለጠፉ ቃላት፡** ተማሪዎች አዳዲስ ቃላትን ባወቁ ጊዜ መምህር በወረቀት ላይ በመጻፍ በግድግዳ ላይ ለጥፈው እንደማጣቀሻ መጠቀም።

**ስዕላዊ መግለጫ፡**የቃላት ካርታ፣ ቻርትን መረዳት፣ቃላትን መፈለግ

**ጆርናሎችን መረዳት**፡ተማሪዎች ጆርናል አንብበው የቀደመ እውቀታቸውን ይገነባሉ፤ የቀደመ እውቀታቸውን አውጥተው ማንጸባረቅ።

**አውድን ማዛመድ፡**ተማሪዎች የሚዛመዱ አውዶችን አንብበው መልዕክቱን ማግኘት።

**ቀስበቀስ ማብቃት** ፡በገደል ማሚቶ፣በህብረት ማንበብ፣ከጓደኛ ጋር ማንበብ፣በሹክሹክታ ማንበብ

**በጊዜ የተገደበ ንባብ፡** ተማሪዎች አጭር ምንባብን ብዙ ጊዜ ማንበብ። የእያንዳንዱን የንባብም ይመዘግቡላቸዋል፤ ለውጡንም ለመመልከት በቻርት ማስቀመጥ።

**መከፋፈል፡** ተማሪዎች ሀረጋትን ከፋፍለው ማንበብ።

**መገመት፡** መምህር ለተማሪዎች በሚሰጣቸውን ፍንጭ መሰረት አድርገው ስለምን ሊያነቡ እንደሚችሉ እንዲገምቱ መጠየቅ።

**መጠየቅ፡** ተማሪዎች ጥያቄ መጠየቅ እንዲችሉ እድል መስጠት።

**ተቀናጅቶ ድምጽን ከፍ በማድረግ ማንበብ፡** መምህር አንድ አጭር ታሪክ ያዘጋጃሉ። ተማሪዎች አጭር ታሪክ በማንበብ ይሳተፋሉ። ታሪኩን በቡድን ይከፋፈላሉ። አንዱ ቡድን ጮክ ብሎ ሲያነብ ሌላኛው የተነበበውን የታሪክ ክፍል ዋና ሀሳብ መናገር።

**ተደጋጋሚ ቃላዊ ንባብ** ተማሪዎች ቃላዊ ንባብ በማካሄድ ከመምህራን፣ ከጓደኛ ምላሽ ያገኛሉ።

**በጊዜ የተገደበ ንባብ** ተማሪዎች አጭር ምንባብን ብዙ ጊዜ ያነባሉ። እያንዳንዱን ንባብም ሰዓት ይመዘግቡለታል፤ ለውጡንም ለመመልከት በቻርት ማስቀመጥ።

**የአረፍተ ነገር ቅኝት፡**

አንድ አረፍተ ነገር ብዙ ጊዜ ማንበብ። በእያንዳንዱ ንባብ ጊዜ እያንዳንዱ ቃል ላይ ትኩረት ይሰጣል። የፊደል-ድምጽ ግንኙነት፣ቃላት፣ በአ/ነገሮች

**ማጠቃለያ** መረጃዎችን በተደራጀና በተጠቃለለ መልክ ማቅረብን ማለማመድ።

የፊደል ድምጽ ግንኙነት፣ቃላት፣አረፍተ ነገር

**ለምልክቶች ትኩረት መስጠት፡**

አገላለጽን ለማሻሻል መምህር በግልጽ የምልክቶችን አላማ በመግለጽ እንዴት እነዚህ ምልክቶች በአገላለጽና በድምጸት ላይ ተጽእኖ እንደሚያደርጉ ማብራራት፡

**በቡድን መጻፍ፡** መምህር አርዐያ በመሆን ተማሪዎች አንድ የጋራ ንባብ እንዲጽፉ ማበረታታት።

## 4. ምዘና

- በጽሁፍ/በቃል ጥያቄዎችን መጠየቅ
- አካላዊ ምላሽ (ተማሪዎች በግል ለጥያቄዎች አካላዊ ምላሽ ይሰጣሉ)
- ኢ-መደበኛ ቁጥጥር (ምልከታ፣ በስዕል መወከል፣ ተራ በተራ ማቅረብ፣ ስልታዊ ልምምድ፣ የመውጫ ካርድ

## ክፍለጊዜ አንድ

## ትምህርት አንድ፡ ማዳመጥ

**መምህር**፣ ወደ ማንበብ ተግባር ከመግባትዎ በፊት የተማሪዎቹን የቀደመ እውቀት ለመቀስቀስ በመማሪያ መጽሐፍ ላይ የቀረቡትን የቅድመማዳመጥ ቀስቃሽ ጥያቄዎች ይጠይቁ። የተማሪዎችዎን ግምት ከተቀበሉ በኋላ የንባቡን መልእክት ለመረዳት በጥሞና ማዳመጥ እንዳለባቸው ያሳስቧቸው። በተጨማሪም ለማዳመጥ ጊዜ የተዘጋጁትን የባዶ ቦታ ማሟያ ቃላትና ባዶቦታ ያለባቸውን አረፍተነገሮች እንዲያነቡ ያድርጉ። ማንበባቸውን ካረጋገጡ በኋላ ምንባቡንም ያንብቡላቸው። በንባቡ መሃል *** ምልክት ባለበት ማንባቡን ቆም አድርገው ቀጣዩን ሀሳብ መገመት እንዲችሉ የቀረበውን ጥያቄ ይጠይቋቸው።

### ባህላዊ የሙዚቃ መሣሪያዎች

በሀገራችን የተለያዩ ባህላዊ የሙዚቃ መሣሪያዎች ይገኛሉ። እነዚህን የሙዚቃ መሳሪያዎች ከሚሰሩበት ቁስ አንፃር በሶስት ከፍሎ ማየት ይቻላል። እነዚህም የክር፣ የትንፋሽና የምት

በመባል ይታወቃሉ።

*** የክር የሚባሉት የትኞቹ ሊሆኑ ይችላሉ***

የክር የሚባሉት ባህላዊ የሙዚቃ መሳሪያዎች ክራር፣ በገናና ማሲንቆ ናቸው። የትነፋሽ የሚባሉት ደግሞ ዋሽንትና ጥሩምባ ናቸው። ሌሎቹ ደግሞ ነጋሪት፣ ከበሮ፣ አታሞ፣ ደወል፣ ቃጭልና ፅናፅል የምት ባህላዊ የሙዚቃ መሣሪያዎች በመባል ይታወቃሉ።
የክር ባህላዊ የሙዚቃ መሣሪያዎች የሚሠሩባቸው ቁሶች፣ እንጨት፣ የከብት ቆዳ፣ የበግና የፍየል ጅማቶች፣ የፈረስ ጭራ፣ ጣውላ፣ ጉድጓዳ ሳህን ዋና ዋናዎቹ ናቸው።

የትንፋሽ ባህላዊ የሙዚቃ መሣሪያዎችን ለማዘጋጀት፣ እንደየመሣሪያዎቹ ዓይነት የተለያዩ ቁሶችን እንጠቀማለን። ለመለከት መሥሪያ ቀርከሃና የድምፅ ማውጫ ቅል ያስፈልጋሉ። ለዋሽንት መስሪያ ደግሞ ሸንበቆና የተለያዩ ድምፆችን ለመፍጠር የሚያስችሉ ቀዳዳዎችን ለመብሳት ሹል ብረት ያስፈልጋል።

የምት ባህላዊ የሙዚቃ መሣሪያዎች ከተለያዩ ቁሶች ይዘጋጃሉ። ነጋሪት፣ ከበሮና አታሞ ለመስራት የዋንዛ እንጨት፣ የከብት ቆዳና ጠፍር ያስፈልጋሉ። ደወልና ቃጭል ለመስራት ደግሞ ነሃስ፣ መዳብና ብረት ያስፈልጋሉ። ፅናፅል ግን ከብረትና ከድቡልቡል እንጨት ይዘጋጃል።

## ክፍለጊዜ ሁለት

**መምህር** ማዳመጣቸውን የሚፈትሹ የመልመጃ አንድ ሀሳቦችን እውነት ወይም ሀሰት ብለው ባዳመጡት መሰረት እንዲመልሱ ያድርጉ። መልመጃውን ለመስራት እንዲያስችላቸው ምንባቡን እንደሚደግምላቸው ያሳውቋቸው። ከመድገምዎ በፊት የቀረቡትን ሀሳቦች እንዲያነቡ ያድርጉ። ሀሳቦቹን አንብበው ለማዳመጥ ዝግጁ ሲሆኑ በጥሞና እንዲያዳምጡ አድርገው ለክፍል ደረጃው በሚመጥን ፍጥነት ያንብቡላቸው።

መልሶቹን መጀመሪያ በግል ቀጥሎ በጥንድ መልሳቸውን በማስተያየት ሃሳብ ይለዋወጡበት። ከዚያም በተናጠልና በየተራ በቃል መልሳቸውን እንዲናገሩ እድል ይፍጠሩላቸው። መልሶቹን ጥቁር ሰሌዳ ላይ በመጻፍ ስለ ትክክለኝነቱ ተማሪዎቹ ሃሳብ እንዲሰጡበት ያድርጉ።

**ክፍለጊዜ ሶስት**

## መልመጃ ሁለት

የተጀመረውን የቃላት ካርታ ከባህላዊ የሙዚቃ መሳሪያ ጋር በተያያዙ ቃላት በማስፋፋት እንዲሞሉ ያድርጉ። ካርታውን ለመሙላት ከማዳመጥ ያገኙትን ሀሳብ መጠቀም እንደሚገባ ያስታውሷቸው። ባህላዊ የሙዚቃ መሳሪያዎች በሶስት ሊከፈሉ እንደሚችሉና ሶስቱ ክፍሎች የየራሳቸው ቅርንጫፎች እንዳላቸው ማስታወስ እንደሚገባ ግንዛቤ ይስጧቸው። በቀረቡት ክቦች ብቻ እንደማይወሰንና መጨመር እንዳለባቸው ግንዛቤ ይፈጠር።

**ክፍለጊዜ አራት**

## ትምህርት ሁለት፡ መናገር

## ተግባር አንድ

ተማሪዎች በአካባቢያቸው ስለሚዘወተር ባህላዊ የሙዚቃ መሳሪያ በቡድን ተወያይተው የተስማሙበትን ሃሳብ በተወካያቸው አማካኝነት ለክፍል ተማሪዎች ይናገሩ። ሃሳባቸውን ለመደገፍ በሚታይ ነገር ለመወከል ጥረት እንዲያደርጉ ይበረታቱ።

**ክፍለጊዜ አምስት**

## ተግባር ሁለት

ከባህላዊ የሙዚቃ መሳሪያዎች ውስጥ ቃጭል፣ ጽናፅል እና ድቤ በባህላዊ ሙዚቃ ውስጥ እንዴት እንደሚያገለግሉ ቤተሰቦቻቸውን ጠይቀው የተረዱትን ለክፍል ጓደኞቻቸው ተዘጋጅተውበት እንዲናገሩ ያመቻቹላቸው።

**ክፍለጊዜ ስድስት**

## ተግባር ሶስት

**መምህር** ተማሪዎቹ በአካባቢያቸው ስለሚያውቁት አንድ የሙዚቃ መሳሪያ ምንነትና ከምን ከምን እንደሚሰራ መረጃ በማሰባሰብ በቃላቸው ለክፍል ጓደኞቻቸው እንዲናገሩ በማድረግ የንግግር ችሎታቸውን እንዲያሻሽሉ ምቹ ሁኔታ ይፍጠሩላቸው። በንግግራቸው ላይ ተገቢና ወቅታዊ ምጋቤ ምላሽ ይስጧቸው።

**ክፍለጊዜ ሰባት**

## ትምህርት ሶስት፡ ማጣመርና መነጠል

## መልመጃ ሶስት

**መምህር** በመማሪያ መጽሐፍ ላይ የቀረቡት ቃላት ውስጥ ያሉ ድምጾችን ነጥለው እንዲጠሩ ያድርጉ። ነጥለው የጠሩትን ወዲያው አጣምረው ቃሉን ይናገሩ። ስለአጠራራቸው ትክክለኝነት የክፍሉ ተማሪዎች ሃሳብ እንዲሰጡበት በማድረግ በሚገባ እንዲለዩት ይደረግ። አዳዲስ የሚሆኑባቸው ቃላት በወረቀት ላይ ተጽፎ በክፍሉ ግድግዳ ላይ ይለጠፍ። ነጥሎ ለማሳየት ፍላሽ ካርድ፣ የተለያየ ቀለም ያላቸውን ወረቀት መጠቀም ይመከራል።

**ክፍለጊዜ ስምንት**

## መልመጃ አራት

መምህር በመማሪያ መጽሐፍ ላይ በቀረቡት ቃላት ላይ በምሰሌው መሰረት ቅጥያዎችን በመጨመር እንዲናገሩ ምሳሌዎችን በመስጠት ያበረታቷቸው። ጥረታቸውንም ያድንቁላቸው። ከአንድ በላይ ቅጥያ መጨመር እንደሚቻል ይጠቁሟቸው።

**ምሳሌ** 1 ከበሮ በከበሮ/ስለከበሮ/እንደከበሮ

2. ደረደረ መደርደር/ደርዳሪ

**ክፍለጊዜ ዘጠኝ**

## ትምህርት አራት፡ የቃላት ጥናት

## መልመጃ አምስት

### ቀጥሎ ካሉት ቃላት ጋር ተመሳሳይ ዜማ የሚፈጥሩ ቃላትን ተናገሩ።

**ምሳሌ** 1. ክህሎት አድናቆት/አገልግሎት

2. ህዳሴ ግስጋሴ/ልስላሴ

| | |
|---|---|
| 1. ብቃት | 2. ስንፍና |
| - ውልቃት | - ብልግና |
| - ግርፋት | - እርጅና |

**ክፍለጊዜ አስር**

## በተመሳሳይ ድምጽ የሚጀምሩና የሚጨርሱ ቃላትን መለየት

## መልመጃ ስድስት

መምህር በመማሪያ መጽሐፍ ላይ የቀረቡትን ቃላት በተመሳሳይ ድምጽ በሚጀምሩና በሚጨርሱ ለሁለት በመሆን በምሳሌው ላይ በመመስረት እንዲከፍሏቸው በቂ ምሳሌ ይስጧቸው።

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| መዘመር | ውልቃት | መቀመር | እርማት | ግርፋት | መደመር |
| ምርቃት | ማንበብ | ሽልማት | መጻፍ | ውቅራት | መመለስ |
| መሳተፍ | እልባት | መማር | እርዛት | መራቆት | ብቃት |
| ጥራት | መንከር | | | | |

| በተመሳሳይ ድምጽ የሚጀምሩ | በተመሳሳይ ድምጽ የሚጨርሱ |
|---|---|
| መዘመር | ውልቃት |
| መደመር | ሽልማት |
| መሳተፍ | እርማት |

## ክፍለጊዜ አስራ አንድ

## ቅጥያ በመተው ጽፎ ማንበብ

## መልመጃ ሰባት

**ሀ. መምህር** ተማሪዎቹ የመጀመሪያውን ቅጥያ አስቀርተው ቃሉን በመጻፍ እንዲያነቡ ያድርጉ። ተማሪዎችዎን አንድ ባንድ በማሳተፍ መረዳታቸውን ይፈትሹ።

ምሳሌ 1 በማሲንቆ ማሲንቆ

2. ስለመታ መታ

**ለ.መምህር** ተማሪዎቹ የመጨረሻውን ቅጥያ አስቀርተው ቃሉን በመጻፍ እንዲያነቡ ያድርጉ። ተማሪዎችዎን አንድ ባንድ በማሳተፍ መረዳታቸውን ይፈትሹ።

ምሳሌ1. ከርካሪዎች ከርካሪ

## ክፍለጊዜ አስራ ሁለት

## ትምህርት አምስት፡ ማንበብ

## ሰመረና ዋሽንት

መምህር ተማሪዎች መፅሐፋቸውን ክፍለጊዜ አስራ ሁለትን እንዲያወጡ ያድርጉ። ርዕሱን እንዲያነቡ ያድርጉና ርዕሱን (ሰመረና ዋሽንት) ጥቁር ሰሌዳ ላይ ይፃፉት። በመቀጠልም መማሪያ መጽሐፍ ላይ ያሉትን ቅድመንባብ ጥያቄዎች እጅ በማውጣት በየተራ

እንዲመልሱ በመጠየቅ ከተወሰኑ ተማሪዎች መልስ ይቀበሉ። ቀጥለውም ተማሪዎቹ ድምጽ ሳያሰሙ በግላቸው ምንባቡን እንዲያነቡ ያድርጉ። ባግባቡ እያነበቡ መሆናቸውን ይከታተሉ። አንብበው መረዳታቸውን ለመፈተሽ በመማሪያ መጽሐፍ ላይ የቀረቡትን ጥያቄዎች ሁለት ሁለት ሆነው እየተወያዩ እንዲሰሩ ያድርጉ። የውይይቱን ሂደት ይከታተሉና አስፈላጊውን ድጋፍ ያድርጉላቸው።

## ክፍለጊዜ አስራ ሶስት

## አንብቦ መረዳት

### መልመጃ ዘጠኝ

መምህር በመማሪያ መጽሐፉ ላይ ከምንባቡ የወጡ ሀሳባቸው መብራራት ያለባቸው አረፍተነገሮች ቀርበዋል። አረፍተነገሮቹ የያዙትን ሀሳብ እንዲያብራሩ ያድርጉ። ለማብራራት እንዲመች መጀመሪያ ለሁለት ሀሳብ ይለዋወጡበት። በመቀጠል ስለይዘቱ የተረዱትን ለክፍልጓደኞቻቸው ያቅርቡ።

## ክፍለጊዜ አስራ አራት

## በጊዜ የተገደበ ንባብ

### መልመጃ አስር

መምህር በመማሪያ መጽሐፍ ላይ የቀረበውን አጭር ጽሁፍ ተማሪዎቹ ድምጻቸውን ከፍ አድርገው በየተራ እንዲያነቡ ያድርጉ። ተማሪዎቹ በሚያነቡበት ጊዜ በተገቢ ፍጥነትና ቅላጼ መሆኑን ይከታተሉ። መረጃዎችን ይያዙ። ከአሁን በፊት ከያዙት መረጃ ጋር በማገናዘብ የተማሪዎችዎን ለውጥ ይመዝኑ።

## ክፍለጊዜ አስራ አምስት

## ትምህርት ስድስት መጻፍ

### መልመጃ አስራ አንድ

መምህር ከሙዚቃ መሳሪያዎች ውስጥ አንዱን በቡድን ያስመርጡ። የመረጡትን የሙዚቃ መሳሪያ ከምን እንደሚሳራና የየትኛው የሙዚቃ መሳሪያ ክፍል እንደሆነ ይወያዩ። ተጨማሪ ከመሳሪያው ጋር የተያያዘ በማዳመጥ ጊዜ የያዙትን ማስታወሻ እንዲመለከቱ ያድርጉ። የቡድን አባላት ስለመሳሪያው በሚያውቁትና በማዳመጥ ጊዜ በያዙት ማስታወሻ ላይ ሀሳብ እንዲለዋወጡ ያድርጉ። ከተወያዩበት ውስጥ ዋናዋና ነጥቦችን የቻሉትን ያህል እንዲያደራጁ ይንገሯቸው። በአደራጁት ሀሳብ መነሻነት አጭር ታሪክ ይጻፉ።

## ክፍለጊዜ አስራ ስድስት

### ተግባር አራት

መምህር በቡድን የጻፉትን በአንድ የቡድኑ አባል ለቡድን አባላት ተነቦ የሚያሻሽሉት ነገር ካለ እንዲነጋገሩበት መመሪያና ጊዜ ይሰጣቸው። ቀጥሎ የተስማሙበትን የመጨረሻ ጽሁፍ እንዲያዘጋጁ ይምሯቸው።


## ክፍለጊዜ አስራ ሰባት

### ተግባር አምስት

መምህር በቡድን ያዘጋጁትን ጽሑፍ እርሰዎ በሚሰጧቸው መመሪያና ቅደም ተከተል መሰረት ከቡድን አባላት ውስጥ በአንዳቸው ለሌሎች ቡድኖች ተነቦ ሀሳብ እንዲለዋወጡበት ይደረግ።

## ክፍለጊዜ አስራ ስምንት

**ሀ. መምህር በመማሪያ መጽሐፍ ላይ በጅምር የቀረውን የቃላት ካርታ ለሁለት እየተነጋገሩ እንዲሞሉ ያድርጉ።**



## ለ. አጫጭር አረፍተነገሮችን በትክክል መፃፉ።

**መምህር** ተማሪዎችዎ ትክክለኛ ፊደላትና ስርአተነጥብ ተጠቅመው መፃፍ እንዲለማመዱ የሚከተሉትን አጫጭር አረፍተነገሮች በዝግታ እያነበቡላቸው እንዲፅፉ ያድርጉ። ተማሪዎቹን በቃል እያስፃፉ ድርጊታቸውን ይከታተሉ። አስፈለጊ ሆኖ ያገኙትን ድጋፍ ለሚያስፈልጋቸው ይስጡ።

1. በለጠ ኳስ ተጫወተ።
2. ወይኔ! ስኳሬ ተደፋ።
3. የጨው አንኳር ያነሳው ማንነው?
4. በድንኳን ውስጥ ያለፈው ማንነው?

**ሐ.** **መምህር** ተማሪዎችዎ ከየሙዚቃ መሳሪያ አይነቶች ውስጥ የሁለት ሁለቱን ስም በትክክለኛ ፊደል ይጻፉ።

# ምዕራፍ ሰባት

# መልካም ባህሪ

(18 ክፍለ ጊዜ)

1. **ከዚህ ምዕራፍ ትምህርት በኋላ ተማሪዎቹ**

- ካዳመጡት ምንባብ የወጡ አዳዲስ ቃላትን ተጠቅመው ቀላል አረፍተ ነገሮችን ይመሰርታሉ፤
- ካዳመጡት ምንባብ ለወጡ ቃላት አገባባዊ ፍቺ ይሰጣሉ፤
- ተመሳሳይ ቅጥያ ያላቸውን ቃላት ይዘረዝራሉ፤
- ተቀባይነት ባለው የፍጥነት ደረጃ አጭር ታሪክ ያነባሉ፤
- ቃላትን በትክክል ይጽፋሉ።

2. **ዝርዝር ይዘቶች**

- ማዳመጥና መናገር
- ድምጻዊ ግንዛቤ (የትዕምርተ ድምጽ ግንዛቤ)
- የቃላት ጥናት፡ ተዘውታሪ(የትምህርት)ቃላት፣ጽንሰሃሳቦችን መሰየም
- ማንበብና መጻፍ
- ማንበብ፡ትክክለኛነት፣ፍጥነት፣ጥሩ አገላለጽ፣አንብቦ መረዳት
- መጻፍ፡ትክክለኛነት ድምጸታዊ ግንዛቤ

3. **የማስተማሪያ ብልሀቶችና መሳሪያዎች**

መምህር የተማሪዎችን የቀደመ እውቀት በመጠቀም የተወሰኑ ቅድመ ማዳመጥ ጥያቄዎችን ለማነቃቃት ያሰሯቸዋል። ምንባቡን ከፍ ባለ ድምጽ ይነበባል። ተማሪዎች አጭር ታሪክ ለመጻፍ የሚረዳቸውን ካዳመጡት ምንባብ አንድ ሀሳብ በደብተራቸው ላይ ይጽፋሉ።

**በጊዜ የተገደበ ንባበብ፡** ተማሪዎች አጭር ምንባብን ብዙ ጊዜ ማንበብ። እያንዳንዱን ንባብም ሰዓት መመዝገብ፤ለውጡንም ለመመልከት በቻርት ማስቀመጥ።

**መከፋፈል :** ተማሪዎች ሀረጋትን ከፋፍለው ማንበብ።

**በርካታ እድሎችን መፍጠር፡**ዳራዊ እውቀት መገንባት፡የቀደመ እውቀት ማንጸባረቅ

**መጠየቅ፡** ተማሪዎች ጥያቄ መጠየቅ እንዲችሉ እድል መስጠት።

**በቃል መጻፍ፡**መምህር ሶስት ተራ አረፍተ ነገሮችን በቃል ለማጻፍ ማዘጋጅት። መምህር ተማሪዎች በቃል የሚጽፏቸውን ሶስት ተራ አረፍተ ነገሮች ያዘጋጃል። ተማሪዎችም መምህር የሚያነባቸውን አረፍተነገሮች በማዳመጥ በትክክል መጻፍ።

**በጊዜ የተገደበ ንባብ** ተማሪዎች አጭር ምንባብን ብዙ ጊዜ ማንበብ። እያንዳንዱን ንባብም ሰዓት ይመዘግቡለታል፤ለውጡንም ለመመልከት በቻርት ማስቀመጥ።

**የአረፍተ ነገር ቅኝት፡**

አንድ አረፍተ ነገር ብዙ ጊዜ ይነበባል። በእያንዳንዱ ንባብ ጊዜ እንዳንዱ ቃል ላይ ትኩረት መስጠት።የፊደል-ድምጽ ግንኙነት፣ቃላት፣ በአ/ነገሮች

**ለምልክቶች ትኩረት መስጠት፡**

አገላለጽን ለማሻሻል መምህር በግልጽ የምልክቶችን አላማ በመግለጽ እንዴት እነዚህ ምልክቶች በአገላለጽና በድምጸት ላይ ተጽእኖ እንደሚያደርጉ ማብራራት።

**በቡድን መጻፍ፡** መምህር አርዐያ በመሆን ተማሪዎች አንድ የጋራ ንባብ እንዲጽፉ ማበረታታት።

**4.ምዘና**

- በጽሁፍ/በቃል ጥያቄዎችን መጠየቅ
- አካላዊ ምላሽ ተማሪዎች በግል ለጥያቄዎች የሚመልሱት አካላዊ ምላሽ
- ኢመደበኛ ቁጥጥር  ምልከታ በስዕል መወከል ተራ በተራ ማቅረብ  ስልታዊ ልምምድ የመውጫ ካርድ

## ክፍለጊዜ አንድ

## ትምህር አንድ፡ ማዳመጥ

መምህር ወደ ንባብ ተግባር ከመግባትዎ በፊት የተማሪዎቹን የቀደመ እውቀት መቀስቀስ እንደሚያስፈልግ አይዘንጉ። ለዚህም መማሪያ መፅሐፍ ላይ ያሉትን ቅድመንባብ ጥያቄዎች ያሰሯቸው። ሲነበብላቸው አዲስ የሚሆኑባቸው ቃላት ካጋጠማቸው በማስታወሻ መያዝ እንዳለባቸውም ያሳስቡ።

መምህር የተማሪዎችን የቅድመንባብ ጥያቄዎች መልስ ከተቀበሉ በኋላ የንባቡን መልዕክት ለመረዳት በጥሞና ማዳመጥ እንዳለባቸው ያስስቧቸው። በንባቡ መሀል*** ምልክት ባለበት ንባቡን ቆም አድርገው ቀጣዩን ሀሳብ መገመት እንዲችሉ ጥያቄ በመጠየቅ የማገናዘቢያ ጊዜ ይስጧቸው።

## አቶ ቶለሳ

አቶ ቶለሳ ችግረኞችን ይረዳሉ። የታመሙ ሰዎችን ይጠይቃሉ። ሀዘንተኞችን ያጽናናሉ። አንድ ቀን መንገድ ሲሄዱ በጣም የተጎሳቆለ ሰው አዩ። ሰውየው ልብሱ አልቋል። ባዶ እግሩ በእንቅፋት ቆስሏል። ሲያዩት በጣም አዘኑ። አቶ ቶለሳ ወዲያው የቤታቸው ሳጥን ታያቸው። የተወሰኑ የማይጠቀሙበት ልብስ ይዟል። ለምን እሱን ለተቸገሩ ሰዎች አልሰጥም ብለው አሰቡ። ወደቤታቸው እንደተመለሱም ያዩትን አሳዛኝ ነገር ለባለቤታቸው ነገሩ። ባለቤታቸው ወይዘሮ አያንቱም በሁኔታው አዝነው "ካሉን ልብሶች የተወሰነውን ለችግረኞች እንስጥ። አንድ ቅያሬ ካለን ይበቃል" አሉ። አቶ ቶለሳም ፈገግ አሉ። "እኔም ይኸን ነበር ያሰብኩት። መልካም አስበሻል። የኔ በመሆንሽ **ኮራሁብሽ**" አሉ።

በተግባቡት መሰረት የተወሰኑ ልብሶችና ጫማዎቻቸውን ለስጦታ ወላጆችዋ ሲያዘጋጁ ያየች የመጀመሪያ ልጃቸው አብደኔ ምን እያደረጉ እንደሆነ ጠየቀቻቸው። ያሰቡትን ነገሯት። ደስተኛ ሆና በእሷ እድሜ ላሉ የተቸገሩ ልጆች **ማካፈል** እንደምት ፈልግ ተናገረች። ቤተሰቡ በመስማማት ልብሶቻቸውን **ለታረዙ**፣ ትርፍ ጫማቸውን ጫማ ለሌላቸው ሰዎች ለመስጠት አቅራቢያቸው ወዳለ **የነዳያን** መሰብሰቢያ ቦታ አመሩ። ይኸን ተግባራቸውን ያዩ ሰዎች የአቶ ቶለሳን ቤተሰብ ያከብሯቸዋል። "ሁሉ ሰው እንደ አቶ ቶለሳ ቤተሰብ ደግ ቢሆን ችግረኛ አይኖርም ነበር፤ **ተደጋግፎ** መኖርም ይቻል ነበር" ይላሉ።

## መልመጃ አንድ

**ሀ.** እባክዎ መምህር ተማሪዎችዎ ማዳመጣቸውን የሚፈትሹ በመማሪያ መጽሐፍ ላይ የቀረቡትን ጥያቄዎችን እንዲሰሩ ያድርጉ። ጥያቄዎቹን በግላቸው እንዲያስቡባቸው ያድርጉ። በግላቸው ባሰቡባቸው መልሶች ላይ ሁለት ሁለት ሆነው እንዲወያዩ ጊዜ በመስጠት ሂደቱን ይከታተሉ። ጥያቄዎቹን በተናጥልና በተራ በቃል እንዲመልሱ ያድርጉ።

## ክፍለጊዜ ሁለት

**ለ.** መምህር መማሪያ መጽሐፍ ላይ ለቀረቡት የአዳምጦ መረዳት ጥያቄዎች ትክክለኛውን መልስ በግል እንዲመርጡ ያድርጉ። የግል መልሳቸውን ከሌሎች ጋር እንዲያስተያዩና በትክክለኛ መልስ ላይ እንዲወያዩ ካደረጉ በኋላ በተናጠል እጅ በማውጣት እንዲሳተፉ ያድርጉ።

## ክፍለጊዜ ሶስት

### መልመጃ ሁለት

መምህር ተማሪዎቹ በ"ሀ" ረድፍ ላሉት ቃላት በምንባቡ መሰረት ከ"ለ" ረድፍ ስር በመምረጥ እንዲያዛምዱ ያድርጉ። በግል ያዛመዱትን ለአራት ያስተያዩና የጋራ መልስ ለመያዝ ይሞክሩ። በመቀጠል ከተለያዩ ቡድኖች ለቃላቱ መልስ ይሆናል ብለው የተስማሙበትን ይቀበሉ። ሰሌዳ ላይ ይጻፉና ሌሎች ሀሳብ እንዲሰጡበት ያድርጉ። አስፈላጊ በሆነበት ተጨማሪ ማብራሪያ በመስጠት የቃላቱ ግንዛቤ እንዲኖራቸው ያድርጉ።

## ክፍለጊዜ አራት

### ትምህርት ሁለት፡ መናገር

### ተግባር አንድ

መምህር ተማሪዎችን በጥንድ ያቀናጁ። እያንዳንዱ ጥንድ በመልካም ባህሪ መገለጫዎች ላይ እንዲወያዩ በመድረግ የውይይታቸውን ሂደት ይከታተሉ። ሀሳቡን ለማብላላት የተወሰነ ደቂቃ ይስጧቸው። የሰጡት ጊዜ ሲያበቃ በየተራ ሀሳባቸውን ለክፍል ተማሪዎች እንዲያከፍሉ ያበረታቷቸው።

*የሚከተለውን ለቀጣይ ክፍለጊዜ ተዘጋጅተው እንዲመጡ የቤት ስራ ይስጧቸው። "በአካባቢያችሁ በጥሩነታቸው የሚታወቁ ሰዎች ምን ምን ተግባራትን እንደሚፈጽሙ ሰዎችን ጠይቃችሁ ለክፍል ጓደኞቻችሁ ንገሩ" በማለት ግልጽ መመሪያ ይስጧቸው።*

## ክፍለጊዜ አምስት

### ተግባር ሁለት

መምህር በሰጡት የቤት ስራ መሰረት በአካባቢያቸው በጥሩነታቸው የሚታወቁ ሰዎች ምን ምን ተግባራትን እንደሚፈጽሙ ሰዎችን ጠይቀው ለክፍል ጓደኞቻቸው በንግግር እንዲያቀርቡ ያመቻቹላቸው። የተዘጋጁበትን በሚያቀርቡበት ጊዜ አቀራረባቸውን ተከታትለው አስፈላጊውን የእርምት ድጋፍ ያድርጉላቸው። ጥረታቸውንም ያድንቁላቸው።

## ክፍለጊዜ ስድስት

### ተግባር ሶስት

መምህር ተማሪዎቹ መልካም በህሪ ነው ከሚሉት ውስጥ አንዱን ይምረጡ። የመረጡትን

መልካም ባህሪ ምንነትና በሚያስገኘው ጥቅም ላይ ተዘጋጅተው ለክፍል ጓደኞቻቸው ንግግር እንዲያደርጉ ይምሯቸው። ሲያቀርቡም ተከታትለው አስፈላጊውን ድጋፍ ያድርጉላቸው።

## ክፍለጊዜ ሰባት

## ትምህርት ሶስት፡ የቃላት ጥናት

### መልመጃ ሶስት

#### ሀ ለቃላት ፍቺ መስጠት

መምህር ተማሪዎቹ ከአዳመጡት ውስጥ ለወጡ ቃላት በግል ፊቺ እንዲሰጡና የየግል ፍቺያቸውን በማስተያየት ስለቃላቱ ያላቸውን እውቀት እንዲያደብሩ ያመቻቹላቸው። በፍቺዎች ላይ ሲነጋገሩም ክፍል ውስጥ በመዘዋወር ሂደቱን እየተከታተሉ ድጋፍ ያድርጉላቸው።

#### ለ ቅጥያ ጨምሮ መናገር

መምህር ቅጥያ ከፊትና ከኋላ እንዴት እንደሚጨመር ከቀረበው ምሳሌ ሌላ በመጨመር ግንዘቤ ያስጨብጧቸው። በማያያዝ በመማሪያ መጽሐፍ ላይ የቀረቡትን ቃላት ጥቁር ሰሌዳ ላይ ይጻፉ። ቃላቱ ላይ ቅጥያ በመጨመር እንዲናገሩ ተማሪዎችን ተራ በተራ አንድ ባንድ ያሳትፉና መልመጃውን ያሰሯቸው።

## ክፍለጊዜ ስምንት

#### ሐ ተመሳሳይ ዜማ ያላቸው ቃላት መናገር

መምህር በመማሪያ መጽሐፍ ላይ የከቀረቡት ቃላት ጋር ተመሳሳይ ዜማ የሚፈጥሩ ሶስት ሶስት ቃላት አፍልቀው እንዲናገሩ በቂ ምሳሌ ይስጧቸው። በተማሪዎቹ የሚቀርቡትን ቃላት ሰሌዳ ላይ በመጻፍ በዜማ ስለመመሳሰለቸው ሀሳብ እንዲሰጡ በማድረግ ትምህርቱን ያጠናክሩ።

## ክፍለጊዜ ዘጠኝ

#### መ ቃላት ላይ ቅጥያ ጨምሮ መናገር

መምህር ተማሪዎቹ ቃላት ላይ የተለያዩ ቅጥያዎችን መጨመር እንደሚቻልና ለአጠቃቀም ምቹ እንደሚደረግ ቀጥታ ባልሆነ መንገድ እንዲረዱ በቂ ምሳሌዎችን በመስጠት ያለማምዱ። ቅጥያዎች ከፊት፣ ከኋላ ወይም ከሁለቱም ሊጨመሩ እንደሚችሉ በርካታ ምሳሌዎችን በመስጠት ከአስረዱ በኋላ በቡድን ከእርሶ ጋር እንዲሰሩ ያድርጉ። ቀስ በቀስ እራሳቸውን ችለው እንዲሞክሩ እድሉን ይስጧቸው።

## ክፍለጊዜ አስር

## መልመጃ አራት

### ቃላትን በተመሳሳይ ድምጽ በሚጀምሩና በሚጨርሱ ስር መመደብ

**መምህር** ተመሳሳይ መልመጃ ሰርተው እንደነበር ያስታውሷቸው፡፡ ይኸንንም በተመሳሳይ መንገድ እንዲሰሩት በመምራት ለቅለቱ የተወሰኑ ምሳሌዎችን ከእርስዎ ጋር እንዲሰሩ ያድርጉ፡፡ ቀጥለው በራሳቸው እንዲሰሩ ያድርጉ፡፡

## ክፍለጊዜ አስራ አንድ

## ትምህርት አራት፡ ማንበብ

### የመልካም ስነምግባር መገለጫዎች

**መምህር** ተማሪዎች መፅሐፋቸውን ክፍለጊዜ አስራ አንድን እንዲያወጡ ያድርጉ፡፡ ርዕሱን እንዲያነቡ ያድርጉና ርዕሱን (የመልካም ስነምግባር መገለጫዎች) ጥቁር ሰሌዳ ላይ ይፃፉት፡፡ በመቀጠልም መማሪያ መጽሐፍ ላይ ያለውን ቅድመንባብ ጥያቄ እጅ በማውጣት በየተራ እንዲመልሱ በመጠየቅ ከተወሰኑ ተማሪዎች መልስ ይቀበሉ፡፡

ተማሪዎችዎ ማንበብ ከመጀመራቸው በፊት የንባብ ጊዜ ጥያቄውን እንዲያነቡ ያድርጉ፡፡ የባዶ ቦታ ማሚያዎቹን እያነበቡ እንደሚያገኙም ያሳውቋቸው፡፡ ምንባቡንም በግላቸው ድምጽ ሳያሰሙ እንዲያነቡ ያድርጉ፡፡ አነባበባቸውን ይከታተሉ፤ ተገቢ ድጋፍም ያድርጉላቸው፡፡

የተማሪዎችዎን አንብቦ የመረዳት ችሎታ ለመፈተሽ በመማሪያ መጽሐፉ ላይ በመልመጃ አምስት "ሀ" ስር የቀረቡትን ጥያቄዎች ሁለት ሁለት ሆነው እየተወያዩ እንዲሰሩ ያድርጉ፡፡ የውይይቱን ሂደትም ይከታተሉ፤ በተወያዮች መሃልም የተመጣጠነ ተሳትፎ እንዲኖር ለማድረግ የሚቻሎትን ሁሉ ያመቻቹ፡፡

## አንብቦ መረዳት

## መልመጃ አምስት

ሀ. **መምህር** ለቀረቡት ጥያቄዎች በምንባቡ መሰረት በጥንድ ተወያይተው መልስ እንዲሰጡ ያድርጉ፡፡ መልሶቻቸውንም ያርሙላቸው፡፡ ጥረታቸውን በማድነቅ ያበረታቷቸው፡፡

## ክፍለጊዜ አስራ ሁለት

ለ. መምህር በመልመጃ አምስት “ለ” ስር የቀረቡትን ቃላትና ሀረጋት በጥንድ ሆነው በሚወክሉት ባህሪ ስር እንዲደለድሉ ተማሪዎችን በጥንድ በጥንድ ያቀናጇቸው። እየተረዳዱ በመጥፎና በጥሩ ባህሪ ስር እንዲመድቡ ይርዷቸው።

## መልመጃ ስድስት

## መነሻና መድረሻ ቅጥያ ያላቸውን ቃላት ከምንባብ ማውጣት

ምንባቡን እያነበቡ መነሻና መድረሻ ቅጥያ ያላቸውን ቃላት እንዲፈልጉ ከምንባቡ ምሳሌ ይስጧቸው። ወደስራ ከመግባታቸው በፊት ያልተረዱት ነገር ካለ እንዲጠይቁ ይፍቀዱላቸው። በጥያቄያቸው ላይ በመመስረት አስፈላጊውን ለመስራት ምቹ ሁኔታ የሚፈጥርላቸውን መንገድ ያመቻቹላቸው። አሰራራቸውን በመመልከት ተነሳሳሽነት በሚፈጥሩ ቃላት ለስራው ያትጓቸው።

## ክፍለጊዜ አስራ ሶስት

## ተግባር አራት

መምህር የአቶ ቶለሳ ባልንጀራ በሚል ርእስ የቀረበውን ምንባብ የተማሪዎችዎን የንባብ ፍጥነት እንዲለኩበት የቀረበ ነው። ስለዚህ ተማሪዎችዎን አንድ ባንድ እያስነበቡ ካነበቡት ውስጥ ምን ያህል ቃላት በምን ያህል ጊዜውስጥ ያለ ስህተት እንዳነበቡ በመመዝገብ መሻሻላቸውን ይከታተሉ።

## ክፍለጊዜ አስራ አራት

## ተግባር አምስት

መምህር፣ በተግባር አራት ስር በፍጥነት ለማንበብ ትኩረት ተሰጥቶ የነበረው ክፍለጊዜ አስራ አራት ደግሞ ለፍጥነትና ትክክለኝነት ትኩረት በመስጠት እያስነበቡ የተማሪዎችዎን መሻሻል በየጊዜው ከሚይዙት መረጃ ጋር በማገናዘብ ለተሻለ ውጤት እንዲተጉ ይርዷቸው።

## ክፍለጊዜ አስራ አምስት

## በጊዜ የተገደበ ንባብ

## ተግባር ስድስት

መምህር በመማሪያ መጽሐፍ ላይ በጊዜ ለተገደበ ንባብ የቀረቡት አረፍተነገሮች ከአንድ ደቂቃ ባነሰና ያለምንም ስህተት እንዲያነቡ ይጠበቃል። ተማሪዎችዎ ስንት ቃላት ያለስህተት በ30 ሰከንድ ውስጥ ማንበብ እንደሚችሉ በጊዜ ገድበው ይከታተሉና መረጃ ይያዙ። በያዙት መረጃ በመጠቀም የተማሪዎችዎን መሻሻል ያበረታቱ።

## ክፍለጊዜ አስራ ስድስት

## ትምህርት አምስት፡ መጻፍ

### ተግባር ሰባት

*መምህር ተማሪዎችዎ ስለመልካም ስነምግባር ምንነትና ጠቀሜታ በቡድን ተወያይተው ሀሳብ እንዲያንሸራሽሩና በውይይቱ ውስጥ በዋና ዋና ጉዳዮች ላይ ማስታወሻ እንዲይዙ ይምሯቸው። በጋራ ያፈለቁትንና በማስታወሻ በያዙት ዋና ዋና ነጥቦች በመጠቀም እየተረዳዱ አጭር ታሪክ እንዲጽፉ ያበረታቷቸው።*

## ክፍለጊዜ አስራ ሰባት

### ተግባር ስምንት

*መምህር ተማሪዎችዎ ስለመልካም ስነምግባር ምንነትና ጠቀሜታ በቡድን ተወያይተው የጻፉትን በአንድ የቡድን አባል ለአባለቱ እንዲነበብና መሻሻል፣ መጨመርና መቀነስ ባለበት ላይ እንዲነጋገሩ ያድርጉ። በሚነጋገሩበት ጊዜ ክትትልና ድጋፍ ያድርጉላቸው። በእለቱ የመጨረሻ የሚሉትን ጽሁፍ ማዘጋጀት እንዳለባቸው ያስገንዝቡ።*

## ክፍለጊዜ አስራ ስምንት

### ተግባር ዘጠኝ

*መምህር ተማሪዎችዎ የደከሙበትን በየተራ ከየቡድኑ በሚወከሉ ተማሪዎች አማካኝነት ለሌሎች ቡድን አባላት እንዲያቀርቡ (እንዲነቡ) ይደረግ። የቀረበው ጥሩ ጅማሮ መሆኑን በመግለጽ ያበረታቷቸው። ማሻሻል ያለባቸውን አንኳር ነጥብ እየተቆሙ በየተራ ያስነብቧቸው።*

# ምዕራፍ ስምንት

# የምግብ ዝግጅት

(18 ክፍለ ጊዜ)

1. **ከዚህ ምዕራፍ ትምህርት በኋላ ተማሪዎች፡**
   - ከሚደመጠው ምንባብ ዋና ዋና መረጃዎች በተለየ መልክ ያደራጃሉ፤
   - ከሚደመጠው ምንባብ ተመሳሳይ ቃላትን ያዛምዳሉ፤
   - ተመሳሳይ ቅጥያ ያላቸውን ቃላት ይዘረዝራሉ፤
   - ተራ አረፍተነገሮችን ከምንባቡ ይለያሉ፤
   - አጭር ታሪክ በተገቢ ሁኔታ ያነባበሉ።

2. **ዝርዝር ይዘቶች**
   - ማዳመጥና መናገር
   - ድምጻዊ ግንዛቤ
   - የትዕምርተ ድምጽ ግንዛቤ
   - የቃላት ጥናት፡ ተዘውታሪ(የትምህርት)ቃላት -ጽንሰሃሳቦችን መሰየም
   - ማንበብና መጻፍ
     - ማንበብ፡ትክክለኛነት፣ ፍጥነት፣ ጥሩ አገላለጽ፣ አንብቦ መረዳት
   - መጻፍ፡ትክክለኛነት
     - ድምጸታዊ ግንዛቤ

3. **የማስተማሪያ ብልሀቶችና መሳሪያዎች**

መምህር ያልተሟላ ስዕላዊ መግለጫዎችን በማቅረብ ተማሪዎች እየተነበበላቸው የተጓደለውን ስዕላዊ መግለጫውን በመረጃ ይሞላሉ።

**ማጣመርና መነጠል፡** መምህር ከሚደመጠው ምንባብ የተወሰኑ ድህረግንድ ቅጥያ ያላቸውን ቃላት በመለየት፣ ጥቂት ቃላትን ድህረ ግንድ ቅጥያዎቻቸውን በማጣመርና በመነጠል ያሳያሉ። ተማሪዎቹ የተቀሩትን በምሳሌው መሰረት ድህረ ግንድ ቅጥያዎችን ከቃላቱ መለየት።

**መለየት** ተማሪዎች ቃላቱ በተመሳሳይ ቅድመግንድ ቅጥያዎች የሚጀምሩ ወይም ድህረግንድ ቅጥያ የሚጨርሱ መሆናቸውን መለየት።

**ተመሳሳይ ዜማ** ተማሪዎች ተመሳሳይ ዜማ ያላቸውን ቤተሰባዊ ቃላት መፍጠር።

**ቃላትን መመስረት** ተማሪዎች ማንበብን መለማመድ።

**ግድግዳላይ የተለጠፉ ቃላት፡**ተማሪዎች አዳዲስ ቃላትን ባወቁ ጊዜ መምህር በወረቀት ላይ በመጻፍ በግድግዳ ላይ ለጥፎ እንደማጣቀሻ መጠቀም።

**አውድን ማዛመድ** ተማሪዎች የሚዛመዱ አውዶችን ማንበብ። (የድምጾችን/የፊደላትን ቅርጽ፣ የባለቀለም ወረቀት፣ የካርቱን ስዕሎች ፣የቃላት ካርድ፣ ሰሌዳ መጠቀም)

**ቀስበቀስ ማብቃት፡** በገደል ማሚቶ፣ በህብረት ማንበብ፣ ከጓደኛ ጋር ማንበብ፣ በቀስታ ማንበብ

**በጊዜ የተገደበ ንባብ፡** ተማሪዎች አጭር ምንባብን ብዙ ጊዜ ማንበብ። እያንዳንዱን ንባብም ሰዓት መመዝገብ፤ ለውጡንም ለመመልከት በቻርት ማስቀመጥ።

**መከፋፈል፡** ተማሪዎች ሀረጋትን ከፋፍለው ማንበብ።

**በርካታ እድሎችን መፍጠር፡**ዳራዊ እውቀት መገንባት፡ የቀደመ እውቀት ማንጸባረቅ

**መገመት፡** መምህራን ለተማሪዎች በሚሰጧቸው ፍንጭ ላይ በመመስረት ስለምን ሊያነቡ እንደሚችሉ እንዲገምቱ መጠቀም።

**መጠየቅ፡** ተማሪዎች ጥያቄ መጠየቅ እንዲችሉ እድል መሥጠት።

**ተቀናጅቶ ድምጽን ከፍ በማድረግ ማንበብ፡** ተማሪዎች በታሪኩ ውስጥ ይሳተፋሉ (የድምጾችን/የፊደላትን ቅርጽ፣የባለቀለም ወረቀት ፣የካርቱን ስዕሎች ፣የቃላት ካርድ፣ ሰሌዳ መጠቀም)

**ተዘውታሪ ቃላት፡** መምህር ከምንባቡ ውስጥ ከፍተኛ ድግግሞሽ ያላቸውን ቃላት ይለያሉ። ተማሪዎች ከፍተኛ ድግግሞሽ ያላቸውን ቃላት ከምንባቡ ውስጥም ሆነ ውጭ ፈጥኖ የመለየት ልምድ ያዳብራሉ።

**ስዕላዊ መግለጫ/graphic organization/፡** የቃላት ካርታ፣ ቻርትን መረዳት፣ ቃላትን መፈለግ

**በቃል መጻፍ፡** መምህራን ሶስት ተራ አረፍተ ነገሮችን በቃል ለማስጻፍ ያዘጋጃሉ። ተማሪዎችም መምህራን የሚያነቡላቸውን አረፍተነገሮች በማዳመጥ በትክክል ይጽፋሉ።

**ማጠቃለያ** መረጃዎችን በተደራጀና በተጠቃለለ መልክ ማቅረብን ያለማምዳሉ።

የፊደል ድምጽ ግንኙነት፣ ቃላት፣ አረፍተ ነገር

**ለምልክቶች ትኩረት መስጠት፡**

አገላለጽን ለማሻሻል መምህር በግልጽ የምልክቶችን አላማ በመግለጽ እንዴት እነዚህ ምልክቶች በአገላለጽና በድምጸት ላይ ተጽእኖ እንደሚያደርጉ

ማብራራት።

**ተዘውታሪ ቃላት፡** መምህር ከምንባቡ ውስጥ ከፍተኛ ድግግሞሽ ያላቸውን ቃላት ይለያሉ። ተማሪዎች ከፍተኛ ድግግሞሽ ያላቸውን ቃላት ከምንባቡ ውስጥም ሆነ ውጭ ፈጥኖ የመለየት ልምድ ማዳበር።

**ተደጋጋሚ ቃላዊ ንባብ፡** ተማሪዎች ቃላዊ ንባብ በማካሄድ ከመምህራን፣ ከጓደኛ ምላሽ ማግኘት።

**በቡድን መጻፍ፡** መምህር አርዐያ በመሆን ተማሪዎች አንድ የጋራ ንባብ እንዲጽፉ ማበረታታት።

## 4.ምዘና

- በጽሁፍ/በቃል ጥያቄዎችን መጠየቅ
- አካላዊ ምላሽ (ተማሪዎች በግል ለጥያቄዎች የሚሰጡት አካላዊ ምላሽ)
- ኢመደበኛ ቁጥጥር (ምልከታ፣ በስዕል መወከል፣ ተራ በተራ ማቅረብ፣ ስልታዊ ልምምድ፣ የመውጫ ካርድ

## ክፍለ ጊዜአንድ

## ትምህርት አንድ፡ ማዳመጥ

እባክዎ መምህር ወደ ማስደመጥ ከመግባትዎ በፊት የተማሪዎችን የቀደመ እውቀት ለመቀስቀስ በመማሪያ መጻፉ ላይ የቀረቡትን የቅድመማዳመጥ ጥያቄዎች ለማሰራት የማዳመጥ ርእሱን (የተደራጀ ማዕድ ቤት) ያስነብቧቸውና ጥቁር ሰሌዳ ላይ ይጻፉት፤ የቅድመማዳመጥ ጥያቄዎቹንም ያሰሯቸው። የተማሪዎችዎን የቅድመማዳመጥ ጥያቄዎች መልስ ከተቀበሉ በኋላ ያዳመጡትን መልዕክት ለመረዳት በጥሞና ማዳመጥ እንዳለባቸው ያስስቧቸው። ከሚያዳምጡት ውስጥ ዋና ዋና የሚሏቸውን ነጥቦች በማስታወሻ መያዝ እንደሚጠበቅባቸውም ያሳውቋቸው። መልእክቱንም መረዳት እንዲችሉ ለደረጃው በሚመጥን ፍጥነት ሶስት ጊዜ ደጋግመው ያስደመጧቸው (ያንብቡላቸው)። በማዳመጥ ሂደቱ መሀል *** ምልክት ባለበት ማስደማጡን ቆም አድርገው የማዳመጥ ጊዜ ጥያቄዎችን ያሰሯቸው። በመጨረሻም በማዳመጥ ሂደት ውስጥ እንግዳ የሆኑባቸው ቃላት ካሉ እንዲጠይቁ ያድርጉ። ቃላቱን ወረቀት ላይ በመጻፍ በክፍሉ ግድግዳ ላይ ይለጥፉ። ቀጥለውም ማዳመጣቸውን የሚፈትሹ ጥያቄዎችን በየተራ እንዲመልሱ ያድርጉ።

# የተደራጀ ማዕድ ቤት

ምግብ ለማዘጋጅት የተደራጀ ማዕድ ቤት ቢኖር ይመረጣል። የተደራጀ ማዕድ ቤት ማለት ደግሞ የግድ ሰፊ መሆን አይጠበቅበትም። ማዕድቤቱ ትልቅም ሆነ ትንሽ ግድግዳውና ወለሉ ንፁህ የሆነና በቂ ብርሃን ያለው ቢሆን ይመረጣል። በአስፈላጊ ቁሳቁስም የተደራጀ መሆን ይጠበቅበታል።

*** በማዕድ ቤት ውስጥ ምን ምን ሊገኝ ይችላል?***

በማዕድ ቤት ውስጥ ምግብ ለማዘጋጀት የሚያገለግሉ የተለያዩ ቁሳቁሶች ያስፈልጋሉ። እነዚህም መክተፊያ፣ ቢላዋ፣ ብረት ድስት፣ ማንቆረቆሪያ፣ ማማሰያ፣ ማንኪያ ሹካና የመሳሰሉት ሊሆኑ ይችላሉ። በተጨማሪም የምግብ ጥሬ እቃዎችንና መገልገያ እቃዎችን ለማጠብና በጽዳት ለመስራት የሚያስችል የእቃ ማጠቢያ ሊኖር ይገባል። በተደራጀ ማዕድ ቤት የተዘጋጀ ምግብ ንጽህናው የተጠበቀና ለጤናም ተስማሚ ነው።

## ክፍለጊዜ ሁለት

## መልመጃ አንድ

## የአዳምጦ መረዳት ጥያቄዎች

*መምህር ለጥያቄዎቹ በቂ መልስ ለመስጠት እንዲያመች ተማሪዎችዎ ለሶስት ተቧድነው እንዲሰሩ ያድርጉ። የቡድናቸውን መልስ ከሌላ ቡድን መልስ ጋር እንዲያስተያዩና እንዲነጋገሩበት ያድርጉ። በቡድን ከተነጋገሩበት በኋላ የተስማሙበትን በየተራ ለክፍል እንዲገልጹ ያድርጉ።*

## ክፍለጊዜ ሶስት

## መልመጃ ሁለት

### ዋና ዋና ነጥቦችን ማደራጀት

*መምህር የእለቱ ተግባር ምን እንደሆነ (ዋና ዋና ነጥቦችን ማደራጀት) ያሳውቋቸው። ዋና ዋና ነጥቦችን ቀድመው ከያዙት ማስታወሻ ጋር ለማደራጀት እንዲረዳቸው በድጋሚ እንደሚያነቡላቸውና በጥሞና ማዳመጥ እንዳለባቸው አሳውቀው ያንብቡላቸው።*

*በተደጋገመ ንባብ ውስጥ በግል ያሰባሰቡትን መረጃ ለሁለት እንዲያደራጁት ያቀናጇቸው። ሂደቱን እየተከታተሉ ድጋፍ ያድርጉላቸው። ያደራጁትን ዋና ዋና ሃሳብ በየተራ ለክፍል ጓደኞቻቸው እንዲያቀርቡ ምቹ ሁኔታን ይፍጠሩላቸው። ወቅታዊና የወዲያው ምጋቤ ምላሽም ይስጧቸው።*

## ክፍለጊዜ አራት

## መልመጃ ሶስት

*መምህር ተማሪዎቹ ካዳመጡት ውስጥ ለወጡ ቃላት ፍቺ እንዲሰጡ ምሳሌ ይስጧቸው። በምሳሌው መሰረት በመማሪያ መጽሐፋቸው ላይ ለቀረቡት ቃላት መጀመሪያ በግል ፍቺ እንዲሰጡ ያድርጉ። በመቀጠል የየግል ፍቺያቸውን በጥንድ ያስተያዩ። ጥንዱን ከሌላ ጥንድ ጋር እንዲያስተያዩ በማድረግ ሂደቱን እየተከታተሉ ድጋፍ ይስጧቸው። የጋራ ግንዛቤ እንዲኖር ከተለያየ ቡድን በየተራ ፍቺዎቹን በመቀበል ጥቁር ሰሌዳ ላይ ይጻፉ፤ ሌሎች ቡድኖች በተሰጠው መልስ ላይ ሃሳብ እንዲሰጡ ያድርጉ።*

## ክፍለጊዜ አምስት

## ትምህርት ሁለት፡ መናገር

## ተግባር አንድ

*መምህር ተማሪዎቹ የቤተሰቦቻቸውን ማዕድ ቤት እና ያዳመጡትን ታሪክ በማነጻጸር የሚለያዩበትን እና የሚመሳሰሉበትን በየተራ እየተነሱ እንዲናገሩ በመድረግ ንግግር እንዲለማመዱ ያድርጓቸው።*

## ክፍለጊዜ ስድስት

## ተግባር ሁለት

*በማዕድ ቤት ውስጥ ሊኖሩ የሚችሉ ቁሳቁሶችን በቡድን ተወያይተው እንዲለዩ አምስት አባላት ባሉት ቡድን ያደረጇቸው። ቡድኑ ሰብሳቢና ጸሀፊ ይኑረው። የተሰጣቸውን ጊዜ ባግባቡ እንዲጠቀሙ ለማድረግ አንድ ሰአት ተቆጣጣሪና የተቀሩት በአባልነት ይሳተፉ። ለእያንዳንዳቸው የስራ ድርሻቸውን በሚገባ ያሳውቃቸው።*

*ቡድኑ ከተደራጀ በኋላ እያንዳንዱ አባል በውይይቱ ውስጥ ንቁ ተሳታፊ በመሆን በማዕድ ቤት ውስጥ ሊኖሩ ስለሚችሉ ቁሳቁሶች የመለየት ሂደት ውስጥ ሀሳብ ማቅረብ እንደሚጠበቅባቸው ያሳውቋቸው።*

*በውይይት የለዩዋቸውን የማዕድ ቤት ቁሳቁሶች አገልግሎታቸውንና ከምን እንደተሰሩ በውይይታቸው ማንሳት እንዳለባቸው ያስገንዝቧቸው። ተወያይተው ያደራጁትን ሀሳብ በተወካያቸው በኩል ለክፍል ጓደኞቻቸው በንግግር ያቅርቡ።*

## ክፍለጊዜ ሰባት

## ትምህርት ሶስት፡ መነጠልና ማጣመር

### መልመጃ አራት

### ሀ.መነሻ ቅጥያ መነጠል

መምህር ተማሪዎቹ መነሻ ቅጥያዎችን ከቃላት ለይተው ማሳየትን እንዲለማመዱ በቂ ምሳሌ በመስጠት ያለማምዷቸው። በመማሪያ መጽሐፍ ላይ ከቀረቡት ቃላት መነሻ ቅጥያዎችን በመጀመሪያ በግል እንዲነጥሉ ያድርጉ። በግል የሰሩትን በጥንድ ያስተያዩ። የጋራ ግንዘቤ ለመፍጠር ከተወሰኑ ተማሪዎች መልስ ተቀብለው ሰሌዳ ላይ በመጻፍ ተማሪዎች ሀሳብ እንዲሰጡበት ያድርጉ።

ምሳሌ፡የተደራጀ የ - ተደራጀ

### ለ.መነሻ ቅጥያ ማጣመር

መምህር ተማሪዎቹ መነሻ ቅጥያዎችን ከቃላት ጋር አጣምረው ማሳየትን እንዲለማመዱ በቂ ምሳሌ በመስጠት ያለማምዷቸው። በመማሪያ መጽሐፍ ላይ ተነጣጥለው የቀረቡትን መነሻ ቅጥያና ቃል በመጀመሪያ በግል እንዲያጣምሩ ያድርጉ። በግል የሰሩትን በጥንድ ያስተያዩ። የጋራ ግንዘቤ ለመፍጠር ከተወሰኑ ተማሪዎች መልስ ተቀብለው ሰሌዳ ላይ በመጻፍ ተማሪዎች ሀሳብ እንዲሰጡበት ያድርጉ።

ምሳሌ፡ የ + ምግብ = የምግብ

## ክፍለጊዜ ስምንት

### መልመጃ አምስት

### መድረሻ ቅጥያ መነጠል

መምህር ተማሪዎቹ መድረሻ ቅጥያዎችን ከቃላት ለይተው ማሳየትን እንዲለማመዱ በቂ ምሳሌ በመስጠት ያለማምዷቸው። በመማሪያ መጽሐፍ ላይ ከቀረቡት ቃላት መድሻ ቅጥያዎችን ከቃል በመጀመሪያ በግል እንዲነጥሉ ያድርጉ። በግል የሰሩትን በጥንድ ያስተያዩ። የጋራ ግንዘቤ ለመፍጠር ከተወሰኑ ተማሪዎች መልስ ተቀብለው ሰሌዳ ላይ በመጻፍ ተማሪዎች ሀሳብ እንዲሰጡበት ያድርጉ።

ምሳሌ ፡ ልጆች = ልጅ ኦች

## ለ.ቃላትን ከመድረሻ ቅጥያዎች ጋር አጣምሩ።

መምህር ተማሪዎቹ መድረሻ ቅጥያዎችን ከቃላት ጋር አጣምረው ማሳየትን እንዲለማመዱ በቂ ምሳሌ በመስጠት ያለማምዷቸው። በመማሪያ መጽሐፍ ላይ ተነጣጥለው የቀረቡትን መድረሻ ቅጥያና ቃል በመጀመሪያ በግል እንዲያጣምሩ ያድርጉ። በግል የሰሩትን በጥንድ ያስተያዩ። የጋራ ግንዘቤ ለመፍጠር ከተወሰኑ ተማሪዎች መልስ ተቀብለው ሰሌዳ ላይ በመጻፍ ተማሪዎች ሀሳብ እንዲሰጡበት ያድርጉ።

ምሳሌ፡ ስንዴ + ው = ስንዴው

## ክፍለጊዜ ዘጠኝ

## ትምህርት አራት፡ የቃላት ጥናት

### መልመጃ ስድስት

ሀ. መምህር ተማሪዎቹ በመማሪያ መጽሐፍ ላይ የቀረቡት ቃላት ውስጥ ያሉ ፊደላትን ቦታ በመቀያየርና በመቀነስ የተለያዩ ቃላትን መመስረት እንደሚቻል እንዲረዱ በቂ ምሳሌ ሰርተው ያሳዩ። በመቀጠል ከተማሪዎችዎጋር በጋራ ይስሩ። በመጨረሻ መማሪያ መጽሀፉ ላይ የቀረቡትን በግል ይስሩ በግል በሰሩት ላይ በጥንድ እንዲነጋገሩ ያድርጉ።

**ለምሳሌ፡** ሰለጠነ፣ ሰጠ፣ ነጠለ

## ክፍለጊዜ አስር

ለ. መምህር በ“ሀ” ስር ያሉትን ቃላት አብሯቸው ሊሄዱ ከሚችሉ ”ለ” ስር ካሉት ቅጥያዎች ጋር እንዲያዛምዱ ምሳሌ በመስጠት ያሳይዋቸው። አንድ ቅጥያ ከአንድ ቃል በላይ ሊዛመድ እንደሚችል ይጠቁሟቸው። ስለዚህ ከሰንጠረዡ ውጪ ደብተራቸው ላይ በመጻፍ አንድ ቅጥያ ከተለያዩ ቃላት ጋር መዛመድ እንደሚችል ጽፈው ያሳዩዋቸው። መጀመሪያ በግል እንዲሞክሩ ያድርጉ። በግል የሞከሩትን በጥንድ ያስተያዩ።

## ክፍለጊዜ አስራ አንድ

መምህር እርስዎ በሚሰጧቸው ምሳሌ መሰረት ተመሳሳይ ዜማ የሚፈጥሩ ቃላትን ጽፈው እንዲናገሩ ያድርጉ። በተሰጡት ሁለቱ ምሳሌዎች በእያንዳንዳቸው ላይ ሶስት ሶስት በግል እንዲጨምሩ ይምሯቸው።

**ምሳሌ፡**1. ቁርጠት 2. ግንባታ

ብልጠት እርባታ

## ክፍለጊዜ አስራ ሁለት

## ትምህርት አምስት ፡ ማንበብ

### የዶሮ ወጥ አሰራር

*መምህር ተማሪዎች መፅሐፋቸውን ክፍለጊዜ አስራ ሁለትን ገልጠው ርዕሱን (የዶሮ ወጥ አሰራር) እንዲያነቡ ያድርጉና ጥቁር ሰሌዳ ላይ ይፃፉት። በመቀጠል መማሪያ መጽሐፍ ላይ ያለውን ቅድመንባብ ጥያቄ እጅ በማውጣት በየተራ እንዲመልሱ በመጠየቅ ከተወሰኑ ተማሪዎች መልስ ይቀበሉ። ከዚያም ተማሪዎቹ ማንበብ ከመጀመራቸው በፊት የንባብ ጊዜ መልመጃውን እንዲያነቡ ያድርጉ። የባዶ ቦታ ማሟያዎቹን እያነበቡ እንደሚያገኙም ያሳውቋቸው። ንባቡንም በግላቸው ድምጽ ሳያሰሙ እንዲያነቡ ያድርጉ። አነባበባቸውን ይከታተሉ። በአነባበብ ሂደት ውስጥ የሚታዩትን ግድፈቶችንም በማረም ድጋፍ ያድርጉላቸው።*

**ድህረንባብ፡ አንብቦ መረዳት**

**መልመጃ ሰባት**

*መምህር በመማሪያ መጽሐፍ ላይ የቀረቡትን ጥያቄዎች ሁለት ሁለት ሆነው እየተወያዩ እንዲሰሩ ያድርጉ። የውይይቱን ሂደት በመከታተል አስፈላጊውን ድጋፍ ያድርጉላቸው። መልሳቸውንም በቃል ይቀበሏቸው።*

## ክፍለጊዜ አስራ ሶስት

## ተግባር ሶስት

## ድምጽን ከፍ አድርጎ ማንበብ

*መምህር ባህላዊ ምግቦች የሚለውን ምንባብ ተማሪዎችዎን በየተራ ድምጻቸውን ከፍ አድርገው እንዲያነቡ በማድረግ አነባበባቸውን ይከታተሉ። ለክፍል ደረጃው በሚመጥን ፍጥነት፣ ትክክለኝነትና ቅላጼ እንዲሁም ሀረጋትን አዋህደው ማንበባቸውን መረጃ በመያዝ ይከታተሉ። እንደ ተማሪዎቹ ችግር መለያየት ትኩረትዎን እየለያዩ የተማሪዎችዎ የማንበብ ብቃት ላይ ይስሩ።*

## ክፍለጊዜ አስራ አራት

## ትምህርት ስድስት፡ መጻፍ

**መልመጃ ስምንት**

*መምህር "የዶሮ ወጥ አሰራር" በሚለው ምንባብ ውስጥ ያለውን የድርጊት ቅደም ተከተል አስተካክለው እንዲጽፉ ይንገሯቸው። ቅደም ተከተሉን ከምንባቡ መረዳት እንደሚችሉ ይጠቁሟቸው። የመጀመሪያዎቹ ሁለቱ እንደተሰሩላቸው ያሳውቋቸው። የተቀሩትን*

በምሳሌው መሰረት እንዲሰሩ ያድርጉ።

ምሳሌ 1.ሸንኩርት መክተፍ

2.ማቁላላት

## ክፍለጊዜ አስራ አምስት

### መልመጃ ዘጠኝ

ሰንጠረዡ ውስጥ ባሉት ቃላት አረፍተ ነገሮች ጻፉ።

| | | |
|---|---|---|
| ገመቹ | ዶሮ ወጥ | ሰራች |
| ጫልቱ | | በላች |
| መሀመድ | | በላ |
| | | ሰራ |

## ክፍለጊዜ አስራ ስድስት

### መልመጃ አስር

መምህር ተማሪዎችዎ የሚወዱትን ባህላዊ ምግብ እንዲመርጡ ይጠይቋቸው። የመረጡትን ባህላዊ ምግብ ለምን እንደሚወዱት ባጭሩ እንዲጽፉ ያበረታቷቸው። የጻፉትንም ለክፍል ጓደኞቻቸው እንዲያነቡ ይጋብዟቸው

ምሳሌ ፡ እኔ ጩኮ እወዳለሁ። ጩኮ ክፍተኛ የምግብነት ጠቀሜታ አለው። ጣእሙ ይመቸኛል። ሳይበላሽ ብዙ ጊዜ ይቆያል። በዚህ ምክንያት ከሌሎች ባህልዊ ምግቦች ጩኮ እመርጣለሁ። የሚል መነሻ ሊሰጧቸው ይችላሉ

## ክፍለጊዜ አስራ ሰባት

### መልመጃ አስራ አንድ

መምህር በመማሪያ መጽሐፍ ላይ በ "ሀ" ስር የቀረቡትን ቃላት አንብበው በ"ለ"ስር ከቀረቡት ምስሎች ጋር እንዲያዛምዱ ያድርጉ። ቢቻልና በተለያየ ካርድ ላይ ቀርበው ብጤ በመፈለግ ስልት ቢቀርብ ሳቢ ይሆናል። ሌላም ለሚያስተምሩበት ቦታ ምቹ የሆነ አማራጭ ካለ ተፈትሾ ስራ ላይ ይዋል።

## ክፍለጊዜ አስራ ስምንት

### መልመጃ አስራ ሁለት

መምህር ተማሪዎችዎ ቅጥያዎችን ከቃል ጋር አጣምረው ጽፈው እንዲያነቡ ያድርጉ።

ምሳሌ፡- አል-መጣም፡- አልመጣም

### መልመጃ አስራ ሶስት

መምህር ተማሪዎችዎ የሚወዱትን የምግብ አይነት በመጥቀስ ስለአዘገጃጀቱ እንዲጽፉ ይምሯቸው።

# ምዕራፍ ዘጠኝ

# ዲጂታል መሳሪያዎች

(18 ክፍለ ጊዜ)

## 1. ከትምህርቱ የሚጠበቁ ውጤቶች

ከዚህ ምዕራፍ ትምህርት በኋላ ተማሪዎች፤

- ከሚደመጠው ምንባብ ዋና ዋና መረጃዎች በተለየ መልክ ያደራጃሉ፤
- ከምንባቡ ተቃራኒ ቃላትን ያዛምዳሉ፤
- ለቃላት አገባባዊ ትርጉም ይሰጣሉ፤
- ከቀረቡ ቃላት ቅድመ ግንድ ቅጥያዎችን ለይተው ይናገራሉ፤
- አጭር ታሪክ በትክክል ያነባሉ፤
- አራት አረፍተ ነገሮችን በትክክል ይጽፋሉ።

## 2. ዝርዝር ይዘቶች

- ማዳመጥና መናገር
- ድምጻዊ ግንዛቤ (የትዕምርተ ድምጽ ግንዛቤ)
- የቃላት ጥናት፡ ተዘውታሪ(የትምህርት)ቃላት -ጽንሰሃሳቦችን መሰየም
- ማንበብና መጻፍ
    - ማንበብ፡ትክክለኛነት፣ፍጥነት፣ጥሩ አገላለጽ፣አንብቦ መረዳት
    - ድምጸታዊ ግንዛቤ

## 3. የማስተማሪያ ብልሀቶችና መሳሪያዎች

መምህር የተማሪዎችን የቀደመ እውቀት ተጠቅመው በማነሳሳት እንዲያዳምጡ ማዘጋጀት፤ በቡድን እንዲቀመጡ አድርገው በአንድ በተወሰነ ርእሰ ጉዳይ ላይ እንዲያተኩሩ ማድረግ፤ ቻርቱን ከምንባቡ በወጡ መረጃዎች ማሟላት፤ በመጨረሻም እያንዳንዱ ቡድን የጨበጠውን መረጃ ለሌሎች ቡድኖች ማጋራት።

**ተቃራኒ ቃላት፣** መምህር በግድግዳ ላይ ቃላት ጽፈው ይለጥፋሉ። ተማሪዎች ግድግዳ ላይ ለተለጠፉት ቃላት ተቃራኒ ፍቺ ካላቸው ቃላት ማዛመድ። የቃላትን አገባባዊ ፍቺ፤ በምንባቡ ውስጥ ተደጋጋሚ ቃላት፣ ቅድመግንድ ቅጥያ ያላቸው ቃላት ይለያሉ።

**ቀስበቀስ ማብቃት ፡** በገደል ማሚቶ፣ በህብረት ማንበብ፣ ከጓደኛ ጋር ማንበብ፣ በቀስታ

ማንበብ

**በጊዜ የተገደበ ንባብ፡** ተማሪዎች አጭር ምንባብን ብዙ ጊዜ ማንበብ። እያንዳንዱን ንባብም ሰዓት መመዝገብ፤ለውጡንም ለመመልከት በቻርት ማስቀመጥ።

**መከፋፈል፡** ተማሪዎች ጽሁፍን በተገቢ ሀረጋት ከፋፍሎ ማንበብ መቻል።

**መጠየቅ፡** ተማሪዎች ጥያቄዎችን እንዲያነሱበት ጊዜ መስጠት።

**ለምልክቶች ትኩረት መስጠት፡**

አገላለጽን ለማሻሻል መምህር በግልጽ የምልክቶችን አላማ በመግለጽ እንዴት እነዚህ ምልክቶች በአገላለጽና በድምጸት ላይ ተጽእኖ እንደሚያደርጉ ማብራራት።

## 4. ምዘና

- በጽሁፍ/በቃል ጥያቄዎችን መጠየቅ፤ አካላዊ ምላሽ (ተማሪዎች በግል ለጥያቄዎች አካላዊ ምላሽ ይሰጣሉ) ኢመደበኛ ቁጥጥር (ምልከታ፣ በስዕል መወከል፣ ተራ በተራ ማቅረብ፣ ስልታዊ ልምምድ፣ የመውጫ ካርድ)

## ክፍለ ጊዜ አንድ

## ትምህርት አንድ፡ ማዳመጥ

*መምህር ወደ ማንበብ ተግባር ከመግባትዎ በፊት የተማሪዎቹን የቀደመ እውቀት መቀስቀስ እንደሚያስፈልግ አይዘንጉ።ለዚህም በመማሪያ መጽሐፍ ላይ የቀረቡትን የቅድመማዳመጥ ጥያቄዎች ይጠይቁ። ለጥያቄዎቹ ተማሪዎች እጅ እያወጡ መልስ እንዲሰጡ ያድርጉ። የተማሪዎችን የቅድመማዳመጥ ጥያቄዎች መልስ ከተቀበሉ በኋላ የምንባቡን መልዕክት ለመረዳት በጥሞና ማዳመጥ እንዳለባቸው ያሳስቧቸው። ከሚያዳምጡት ውስጥ ዋና ዋና የሚሏቸውን ነጥቦች በማስታወሻ መያዝ እንደሚጠበቅባቸው ያሳውቋቸው። እርስዎም ተማሪዎችዎ መልእክቱን መረዳት እንዲችሉ ለደረጃው በሚመጥን ፍጥነት ሶስት ጊዜ ደጋግመው ያንብቡላቸው። በምንባቡ ውስጥ *** ምልክት ባለበት ንባቡን ቆም አድርገው የቀደመ ሃሳብ ማጤንና ቀጣዩን ሀሳብ መገመት እንዲችሉ ጥያቄዎችን ይጠይቁ፤ ከተወሰኑ ተማሪዎችም መልስ ይቀበሉ። ማስደመጡ ካበቃ በኋላ በማዳመጥ ሂደት ውስጥ እንግዳ የሆኑባቸው ቃላት ካሉ እንዲጠይቁ ያበረታቷቸው። ቃላቱን ወረቀት ላይ በመጻፍ በክፍሉ ግድግዳ ላይ ይለጥፉ። በመጨረሻም ማዳመጣቸውን ለመፈተሽ መማሪያ መጽሐፍ ላይ የቀረቡትን የአዳምጦ መረዳት መልመጃ ያሰሯቸው።*

*መምህር ከዳመጡት ባገኙት ሀሳብ መሰረት ለባዶ ቦታዎች የሚስማማ መልስ ሊያገኙ*

ስለሚችሉ ምንባቡ ሳይቀርብላቸው በፊት ባዶቦታዎች ያሉባቸውን ጥያቄዎች ከመጽሐፋቸው ላይ እንዲያነቡት ይደረግ። ሶስቴ ከተነበበላቸው በኋላ የባዶቦታዎቹን ማሟያ መልሶች እጅ እያወጡ እንዲሰጡ ያድርጉ።

## ዲጂታል መሳሪያዎች

ዘመን ያፈራቸው ድጂታል መሳሪያዎች ተግባቦትን ቀላል አድርገውታል። ተራርቀው የሚኖሩ ዘመዳሞች ወይም ጓደኛሞች በተንቀሳቃሽ ስልክ እየተያዩ ማውራት አስችሏል። በአንድ ሀገር ስለሆነው ጥሩም ሆነ መጥፎ ነገር ቤታችን ሆነን በቴሌቭዥን መስኮት መከታተል የተቻለውም ዘመኑ ባፈራው መሳሪያ ነው። ታሪካዊና አይረሴ ጉዳዮችን ለመቅረጽና ለትውልድ ለማቆየት የሚያስችለው ካሜራም ዘመኑ የሰጠን ሌላው የተግባቦት መሳሪያ ነው።

1. የተግባቦት መሳሪያዎች ተብለው የተቀሱት ምን ምን ናቸው?
2. ከተጠቀሱት ሌላ ዘመን ያፈራቸው የተግባቦት መሳሪያዎች ምን ሊሆኑ ይችላሉ?

የዘመን ስጦታ የተጠቀሱት መሳሪያዎች ብቻ አይደሉም። በፍጥነት የጽሁፍ፣ የምስልና የድምጽ መልእክት መለዋወጥ ያስቻሉት እንደ ቴሌግራም መተግበሪያ ያሉት የዚሁ ዘመን ገጸበረከቶች ናቸው። ወረቀት ላይ ተጽፎና ብዙ ጊዜ ፈጅቶ የሚደርሰውን ደብዳቤ የመጻፍ ስርአትንም በአጭር መልዕክት ልውውጥ የተካውና ያቀለጠፈው ዘመኑ ያፈራው ድጅታል መሳሪያ ነው።

ሌላው ዘመኑ ያፈራው በእንተርኔት አማካኝነት ለመገናኘት የሚያስችለው ማኅበራዊ ድረገጽ ነው። ከማህበራዊ ድረገጾች ውስጥ እንደ ፌስቡክ፣ ትዊተር፣ ኢንስታግራም ወዘተ. ያሉት ለበጎ ከዋሉ ብዙ ጥቅም ይሰጣሉ። ለምሳሌ ፌስቡክ **በበጎ ገጽታው** ለበርካታ ቁምነገሮች መጠቀም ተችሏል። በቀላሉ የግል ሀሳብን ለብዙሃን ማስተላለፍ አስችሏል። ሌሎችም ማህበራዊ ድረገጾች በተመሳሳይ መንገድ የአለምን ህዝብ የማገናኘት አገልድሎት እየሰጡ ነው። በአግባቡ ስራ ላይ ካልዋሉም የሚያስከትሉት ጉዳት ከፍተኛ ነው። ምክንያቱም በቀላልና በፍጥነት አለምን የማዳረስ ብቃት ያላቸው ስለሆኑ ነው። በፍጥነትና በቀላሉ አለምን የማዳረስ ብቃት ስላላቸው አለምን አንድ መንደር አድርገዋታል። የተጠቀሱትንና ሌሎች የሰው ልጅን ድካም እንዲቀል ማድረግ ያስቻሉት ዘመኑ ያፈራቸው ድጂታል መሳሪያዎች ናቸው።

## ክፍለጊዜ ሁለት

## አዳምጦ መረዳት ጥያቄዎች

### መልመጃ አንድ

*መምህር ከዳመጡት ባገኙት ሀሳብ መሰረት መልመጃ አንድ ላይ ጥንድ ጥንድ ሆነው መልሱን እንዲፈልጉ ያቀናጁቸው። በጥንድ ሲወያዩ በትክክለኛ ሂደት ላይ መሆናቸውን ይከታተሉ። በሚያስፈልግበት የማስተካከያ ድጋፍ ያድርጉላቸው።*

## ክፍለጊዜ ሶስት

## ትምህርት ሁለት፡ መናገር

### ተግባር አንድ

*መምህር ተማሪዎቹ በመማሪያ መጽሀፋቸው ላይ በቀረቡት ነጥቦች መነሻ ሀሳብነት በቡድን እንዲወያዩ ያድርጓቸው። በቡድን ውይይት ወቅት ሁሉም ተሳትፎ እንዲኖራቸው እርስ በርስ እንዲቆጣጠሩ የቡድን አደረጃጀቱን ያመቻቹ። ክንውናቸውንም ይከታተሉ፤ አስፈላጊ በሆነበት የማስተካከያ ድጋፍ ያድርጉላቸው።*

## ክፍለጊዜ አራት

### ተግባር ሁለት

*መምህር ተማሪዎቹ በመማሪያ መጽሀፋቸው ተግባር ሁለት ስር በቀረቡት ነጥቦች መነሻነት በቡድን እንዲወያዩ ያድርጓቸው። በቡድን ውይይት ወቅት ሁሉም ተሳትፎ እንዲኖራቸው ያበረታቷቸው። በውይይታቸውም ውስጥ የሚነሱ ዋና ዋና ነጥቦችን በማስታወሻ ይዘው የተገነዘቡትን ልክ የሆነና ልክ ያልሆነ አጠቃቀም እርስዎ በሚሰጧቸው ቅደም ተከተል ለክፍል ጓደኞቻቸው እንዲነግሩ ያበረታቷቸው።*

## ክፍለጊዜ አምስት

### ተግባር ሶስት

*መምህር ተማሪዎችዎ ስራን በኮምፒዩተር የመስራት ጥቅም ምን እንደሆነ ከሚያውቅ ሰው ጠይቀው ያገኙትን ሃሳብ አባል ለሆኑበት ቡድን እንዲያቀርቡና እንዲወያዩበት መመሪያ ይስጧቸው። የተወያዩበትን ዋና ዋና ነጥብ በተወካያቸው አማካኝነት ለክፍል ጓደኞቻቸው አቅርበው ልምድ እንዲለዋወጡበት ያድርጉ።*

## ክፍለጊዜ ስድስት

## ትምህርት ሶስት፡ መነጠልና ማጣመር

### መነጠል

### መልመጃ ሁለት

ሀ. መምህር ቅጥያን መነጠልና ማጣመር በምዕራፍ ስምንት ውስጥ እንዲሰሩ ተማሪዎችዎን ያስታውሱ። በዚህም ምዕራፍ ተመሳሳይ መልመጃ በሌሎች ቃላት እንደሚሰራ ያሳውቋቸው። ምሳሌ በመስጠት በመማሪያ መጽሐፍ ክፍለጊዜ ስድስት፣ መልመጃ ሁለት ስር ከቀረቡት ቃላት ላይ **መነሻ** ቅጥያ ነጥለው መጻፍ እንደሚጠበቅባቸው ያሳውቋቸው። በመልመጃው ስር የቀረቡትን ቃላት መጀመሪያ በግላቸው ይስሩ። ቀጥለው በጥንድ በመልሶቻቸው ላይ ይወያዩ። በመጨረሻ ከተወሰኑ ተማሪዎች በናሙናነት መልስ ይቀበሉ። በመልስ አሰጣጣቸው ላይ በመመሥረት አስፈላጊውን ማስተካከያ በመስጠት ትምህርቱን ያጠናክሩ።

ምሳሌ ፡ትመጣለች ት - መጣለች

## ክፍለጊዜ ሰባት

ለ. መምህር ምሳሌ በመስጠት ተማሪዎችዎ በመማሪያ መጽሐፍ ክፍለጊዜ ሰባት፣ መልመጃ ሁለት “ለ” ስር ከቀረቡት ቃላት ላይ **መድረሻ** ቅጥያ ነጥለው መጻፍ እንደሚጠበቅባቸው ያሳውቃቸው። በመልመጃው ስር የቀረቡትን ቃላት መጀመሪያ በግላቸው ይስሩ። ቀጥለው በጥንድ በመልሶቻቸው ላይ ይወያዩ። በመጨረሻ ከተወሰኑ ተማሪዎች በናሙናነት መልስ ይቀበሉ። በመልስ አሰጣጣቸው ላይ በመመሥረት አስፈላጊውን ማስተካከያ በመስጠት ትምህርቱን ያጠናክሩ።

ምሳሌ፡-መጣች መጣ-ች

## ክፍለጊዜ ስምንት

ሐ. መምህር ለተማሪዎች እንዴት እንደሚሰሩ ተጨማሪ ምሳሌ ይስጧቸው። በመማሪያ መጽሐፍ ላይ በቀረበው ሰንጠረዥ ውስጥ በተጀመረው መሰረት የቀረውን መነሻና መድረሻ ቅጥያ ነጥለው እንዲያሳዩ ያበረታቷቸው።

## ክፍለጊዜ ዘጠኝ

## ትምህርት አራት፡ የቃላት ጥናት

### መልመጃ ሶስት

ሀ. መምህር መማሪያ መጽሐፍ ክፍለጊዜ ዘጠኝ “ሀ” ስር ለቀረቡት ቃላት በፍቺ ተቃራኒ የሚሆኑ ቃላትን ከ“ለ” ረድፍ ፈልገው እንዲያዛምዱ ይምሯቸው። መጀመሪያ በግል እንዲሰሩት አድርገው በመቀጠል መልሶቻቸውን በጥንድ በማስተያየት እንዲነጋገሩበት መመሪያ ይስጧቸው። ለማረጋገጥ ከተወሰኑ ተማሪዎች መልስ ተቀብለው ሰሌዳ ላይ በመጻፍ በተማሪዎች ሀሳብ እንዲሰጥበት በማድረግ ሀሳቡ እንዲንሸራሸር ያድርጉ።

ለ. መምህር መማሪያ መጽሐፍ ክፍለጊዜ ዘጠኝ “ለ” ስር ለቀረቡት ቃላት በፍቺ ተቃራኒ የሚሆኑ ቃላትን እንዲፈልጉ ይምሯቸው። መጀመሪያ በግል እንዲሰሩት አድርገው በመቀጠል መልሶቻቸውን በጥንድ በማስተያየት እንዲነጋገሩበት መመሪያ ይስጧቸው። ለማረጋገጥ ከተወሰኑ ተማሪዎች መልስ ተቀብለው ሰሌዳ ላይ በመጻፍ ተማሪዎች ሀሳብ እንዲሰጡበት በማድረግ ስለቃላቱ በቂ ግንዛቤ እንዲያገኙ ያድርጉ።

## ክፍለጊዜ አስር

### መልመጃ አራት

መምህር ተማሪዎችዎ በአረፍተነገር ውስጥ ለተሰመረባቸው ቃላት አገባባዊ ፍቺ እንዲሰጡ ምሳሌዎችን በማቅረብ ያለማምዷቸው። ለቃላቱ መጀመሪያ በአገባባቸው መሰረት በየግላቸው ፍቺ ለመስጠት እንዲሞክሩ ያድርጉ። በግላቸው የሰጡትን ፍቺ ሌሎች ተማሪዎች ከሰጡት ፍቺ ጋር እንዲያስተያዩ ያመቻቹላቸው። በጥንድ ወይም በቡድን በመልሶቻቸው ላይ በመማሪያ መጽሐፉ ላይ ለተሰመረባቸው ቃላት አገባባዊ ፍቺ እንዲሰጡ ይርዷቸው።

## ክፍለጊዜ አስራ አንድ

## ትምህርት አምስት፡ ማንበብ

# ኮምፒውተር

መምህር ተማሪዎችዎ መፅሐፋቸውን ክፍለጊዜ አስራ አንድን እንዲያወጡና ርዕሱን (ኮምፒዩተር) እንዲያነቡ ያድርጉና ጥቁር ሰሌዳ ላይ ይፃፉት። በመቀጠልም መማሪያ መጽሐፍ ላይ ያለውን ቅድመንባብ ጥያቄ እጅ በማውጣት በየተራ እንዲመልሱ በመጠየቅ ከተወሰኑ ተማሪዎች መልስ ይቀበሉ። ተማሪዎችዎ ንባብ ከመጀመራቸው በፊት የንባብ ጊዜ

መልመጃውን እንዲያነቡ ያድርጉ። የባዶ ቦታ ማሚያዎቹን እያነበቡ እንደሚያገኙም ያሳውቋቸው። ማንበቡንም ድምጽ ሳያሰሙ በግል እንዲያካሂዱት ያድርጉ። አነባበባቸውን ይከታተሉ።

## ክፍለጊዜ አስራ ሁለት

### መልመጃ አምስት

መምህር በመማሪያ መጽሐፍ ላይ የቀረቡትን ሀሳቦች በምንባቡ መሰረት በመጀመሪያ በግላቸው ትክክል ከሆኑ "እውነት"፣ ትክክል ካልሆኑ ደግሞ "ሀሰት" ብለው እንዲመልሱ ያድርጓቸው። በመቀጠል በጥንድ ሆነው መልሶቻቸውን እንዲያስተያዩ ያቀናጁቸው። በመልስ አሰጣጣቸው ላይ ልዩነት ባለበት እንዲነጋገሩና ወደአንድ ሃሳብ ለመምጣት እንዲሞክሩ ይርዷቸው። ካልተቻለ በጋራ ውይይት ጊዜ መልስ እንደሚያገኙ በማሳወቅ መልመጃውን እንዲሰሩ ይምሯቸው።

## ክፍለጊዜ አስራ ሶስት

### መልመጃ ስድስት

መምህር ተማሪዎችዎ ባነበቡት ምንባብ ውስጥ በተደጋጋሚ የቀረቡ ቃላትን ቆጥረው ከመማሪያ መጽሀፍ ላይ ወደደብተራቸው በገለበጡት ሰንጠረዥ ውስጥ እንዲሞሉ ግልጽ መመሪያ ይስጧቸው። ባገኙት ብዛት ላይ ይነጋገሩ። ልዩነት ባለበት ደግመው ምንባቡን በመፈተሽ ትክክለኛውን ቁጥር ማረጋገጥ እንደሚችሉ ይጠቁሟቸው።

## ክፍለጊዜ አስራ አራት

### ተግባር አራት

መምህር በመማሪያ መጽሀፍ ክፍለጊዜ አስራ አራት ስር የቀረቡትን አረፍተነገሮች ተማሪዎች ድምጻቸውን ከፍ አድርገው እንዲያቡ በማድረግ ስለአነባበብ ቅላጼያቸው፣ ፍጥነታቸውና ትክክለኝነታቸው መረጃ በመያዝ በተማሪዎችዎ የንባብ ብቃት መሻሻል ላይ ይስሩ።

## ክፍለጊዜ አስራ አምስት

### ተግባር አምስት

መምህር በመማሪያ መጽሀፍ ላይ **የእያንቱ ሞባይል** በሚል ርእስ ስር የቀረበውን ምንባብ ተማሪዎች እርስዎ ገድበው በሚሰጧቸው ጊዜ ውስጥ በፍጥነት የሚያነቡትና የተማሪዎች ፍጥነትና ትክክለኝነት ለመስፈር የሚውል ነው። ስለዚህ ምንባቡን እርስዎም ይዘው ተረኛ

ተማሪ ለአንድ ደቂቃ እንዲያነብ ያድርጉ። በሚነብብበት ጊዜ በስህተት በተነበቡ ቃላት ላይ የመለያ ምልክት ያድርጉ። ደቂቃው ሲያልቅ በተደረሰበት ቦታ ምልክት ያድርጉ። ምልክት እስከተደረገበት ስንት ቃላት እንደተነበቡ ይቁጠሩ። ከተነበቡት ውስጥ በስህተት የተነበቡትን ይቀንሱ። የተመዛኝ ተማሪ የአንድ ደቂቃ ፍጥነት ያለ ስህተት የተነበበው ይሆናል። በዚህ መንገድ በተማሪዎችዎ መካከል ያለውን የንባብ ፍጥነት መለየትና ማን በጥሩ ደረጃ ላይ እንዳለ/ች ማወቅ ይችላሉ። በዚሁ መንገድ የተማሪዎችዎን የንባብ ፍጥነት መረጃ መሰብሰብና መርዳት ይችላሉ።

## ክፍለጊዜ አስራ ስድስት

## ትምህርት ስድስት፡ መጻፍ

### መልመጃ ሰባት

መምህር በመልመጃ ሰባት “ሀ” ስር የቀረቡትን ምስሎች በማየት ምንነታቸውን በትክክለኛ ፊደላት በመጻፍ ጽህፈትን ወይም ስእል በጽሁፍ መግለጽን መለማማድ እንደሚችሉ ይጠቁሟቸውና ስራቸውን ይከታተሉ። ድጋፍም ያድርጉላቸው።

መምህር በመልመጃ ሰባት “ለ” ስር የቀረበውን ለማስተግበር የሚከተሉትን አረፍተ ነገሮች በቃል እያነበቡላቸው ተማሪዎቹ እንዲጽፉ ያድርጉ። በትክክል መጻፋቸውንም ለማረጋገጥ ደብተራቸውን ሰብስበው በማረም ወይም ትክክለኛውን አጻጻፍ ጥቁር ሰሌዳ ላይ ጽፈው ተማሪዎች እንዲተራረሙ በማድረግ ያሉበትን ደረጃ እንዲያውቁ ስለሚረዳ ተከታትለው ያሰሯቸው።

1. ሀዊ የዘጠነኛ ክፍል ተማሪ ናት።
2. ሀዊ ተንቀሳቃሽ ስልክ አላት።.
3. ሀዊ ትምህርቷን በርትታ ታጠናለች።
4. ሀዊ ስልኳን ትምህርት ቤት ይዛ አትሄድም።

## ክፍለጊዜ አስራ ሰባት

### መልመጃ ስምንት

#### ሀ. ግርግዳ ላይ ለተለጠፉት ቃላት ተቃራኒያቸውን ማስጻፍ

መምህር በተለያየ ጊዜ ለተማሪዎች አዲስ በመሆናቸው በወረቀት ላይ ተጽፈው ግድግዳ ላይ የለጠፏቸውን ቃላት ተማሪዎቹ ክፍል ውስጥ እየተዘዋወሩ እንዲመለከቱና ተቃራኒያቸውን ደብተራቸው ላይ እንዲጽፉ በማድረግ ስለቃላቱ በቂ ግንዛቤ መጨበጣቸውን ያረጋግጡ።

## ለ. የተዘበራረቁ ቃላትን አስተካክለው እንዲጽፉ መርዳት

መምህር ቅደምተከተላቸው ተዛብተው የቀረቡ ቃላትን አስተካክለው የቋንቋውን ስርአት የጠበቀ አረፍተነገር እንዲጽፉ ምሳሌ በመስጠት ይምሯቸው። በአግባቡ አስተካክለው መጻፋቸውንም ያረጋግጡ።

## ክፍለጊዜ አስራ ስምንት

## መልመጃ ዘጠኝ

መማሪያ መጽሐፍ ላይ በቀረቡት ቃላት አረፍተነገር እንዲያዋቅሩ ያድርጉ። በአዋቀሩት አረፍተነገር ውስጥ አራት ነጥብና ጥያቄ ምልክት ባግባቡ መጠቀማቸውን በትኩረት ይመልከቱ፤ ተገቢውን ምጋቤ ምላሽ በወቅቱ ይስጧቸው።

# ምዕራፍ አስር

# የዱር እንስሳት

(18 ክፍለ ጊዜ)

## 1. ከዚህ ምዕራፍ በኋላ ተማሪዎች

- ከሚደመጠው ምንባብ ዋና ዋና መረጃዎችን በጽሁፍ ያቀርባሉ።
- የምንባቡን ሀሳብ ከነባራዊ ህይወት ጋር ያዋህዳሉ
- ቃለ አጋኖ እና የጥያቄ ምልክቶችን ይጠቀማሉ።
- ምንባቡን በተገቢ ሁኔታ ያነባሉ።
- ከክፍሉ ደረጃ ጋር ተመጣጣኝ የሆኑ አረፍተ ነገሮችን ይጽፋሉ።

## 2. ዝርዝር ይዘቶች

- ማዳመጥና መናገር
- ድምጻዊ ግንዛቤ
- የትዕምርተ ድምጽ ግንዛቤ
- የቃላት ጥናት፡ ተዘውታሪ(የትምህርት ቃላት) -ጽንሰሃሳቦችን መሰየም
- ማንበብና መጻፍ
  - ማንበብ፡ትክክለኛነት፣ፍጥነት፣ጥሩ አገላለጽ፣አንብቦ መረዳት
- መጻፍ፡ትክክለኛነት
  - ድምጸታዊ ግንዛቤ

## 3. የማስተማሪያ ብልሀቶችና መሳሪያዎች

መምህር የተማሪዎችን የቀደመ እውቀት ተጠቅሞ በማነሳሳት እንዲያዳምጡ ማዘጋጀት፡ በቡድን እንዲቀመጡ አድርጎ ተማሪው ከምንባብ ስለእንስሳት የሚገልጽ አረፍተ ነገር ጽፎ በቃል ማቅረብ።

**ማተካካት** መምህር ለተማሪዎች ቀለማትን/ድምጾችን በመግደፍ፣በመተካትና በመጨመር ጨዋታ እንዲጫወቱ ማዘጋጀት።

ሀ. መግደፍ ተማሪዎች አንድን ቃል በማዳመጥ በመነሻ ላይ የሚገኘውን ቀለም/ድምጽ በመግደፍ መጥራት።

ለ. መጨመር ተማሪዎች ቃልን በማድመጥ በቃሉ ላይ ቀለም/ድምጽ በመጨመር መጥራት።

ሐ. መተካት ተማሪዎች ባዳመጡት ቃል ውስጥ ያሉትን ቀለማት/ድምጾች በመተካት መጥራት።

**መናገር** መምህር ቃልን በማሳየት እያንዳንዳቸውን ድምጾች ጠርቶ በማጣመር መናገር። (በታወቁ የፊደል ድምጽ መጠቀም) ተማሪዎች ሁሉንም ድምጽ በመጥራት አጣምረው መጥራት። (በታወቁ የፊደል ድምጽ መጠቀም) (የድምጾችን/የፊደላትን ቅርጽ፣የባለቀለም ወረቀት ፣የካርቱን ስዕሎች ፣የቃላት ካርድ፣ ሰሌዳ መጠቀም)

**አውድን ማዛመድ፡**ተማሪዎች መናገርን መለማመድ።

**ተደጋጋሚ ቃላዊ ንባብ፡** ለተማሪዎች ቃላዊ ንባብ በማካሄድ ከመምህራን፣ከንደኛ ምላሽ ማግኘት።

**በጊዜ የተገደበ ንባብ፡** ተማሪዎች አጭር ምንባብን ብዙ ጊዜ ማንበብ።እያንዳንዱን ንባብም ሰዓት መመዝገብ ፤ለውጡንም ለመመልከት በቻርት ማስቀመጥ።

**የአረፍተ ነገር ቅኝት፡** አንድ አረፍተ ነገር ማንበብ።ብዙ ጊዜ በእያንዳንዱ የንባብ ጊዜ የተለየ ቃል ትኩረት ይሰጥበታል።

የፊደል ድምጽ ግንኙነት፣ ቃላት፣ አረፍተነገሮች

**ለምልክቶች ትኩረት መስጠት፡**

አገላለጽን ለማሻሻል መምህር በግልጽ የምልክቶችን አላማ በመግለጽ እንዴት እነዚህ ምልክቶች በአገላለጽና በድምጸት ላይ ተጽእኖ እንደሚያደርጉ ማብራራት።

## 4. ምዘና

- በጽሁፍ/በቃል ጥያቄዎችን መጠየቅ
- አካላዊ ምላሽ ተማሪዎች በግል ለጥያቄዎች የሚመልሱት አካላዊ ምላሽ
- ኢ-መደበኛ ቁጥጥር (ምልከታ፣ በስዕል መወከል፣ ተራ በተራ ማቅረብ፣ ስልታዊ ልምምድ፣ የመውጫ ካርድ፣

## ክፍለ ጊዜ አንድ

## ትምህርት አንድ፡ ማዳመጥ

መምህር የማዳመጥ ግብአት ማቅረብ ከመጀመርዎ በፊት የተማሪዎችዎን የቀደመ እውቀት ለመቀስቀስ በመጀመሪያ የእለቱን ርእስ (የአይጥ ንጉስ ልጅ) እንዲያነቡና ለቅድመማዳመጥ በመማሪያ መጽሐፉ ላይ የቀረቡትን ጥያቄዎች እያነበቡ እጅ በማውጣት የመሰላቸውን መልስ እንዲሰጡ ይጋብዙ። የተማሪዎችዎን መልስ ከተቀበሉ በኋላ የግብአቱን መልዕክት ለመረዳት በጥሞና ማዳመጥ እንዳለባቸው ያስገንዝቧቸው። የማዳመጥ ግብአቱንም

ያቅርቡላቸው። በግብአቱ መሀል*** ምልክት ባለበት ግብአቱን ማቅረቡን ቆም አድርገው ቀጣዩን ሀሳብ መገመት እንዲችሉ ግብአቱ ውስጥ ያሉትን ጥያቄዎች በመጠየቅ ተማሪዎቹ መልስ እንዲሰጡበት ያድርጉ።

*ማሳሰቢያ (*** ምልክት ባለበት ጥያቄዎቹ መቅረብ ያለባቸው በመጀመሪያው ዙር የማቅረብ ጊዜ ብቻ መሆን አለበት***)*

## የአይጥ ንጉስ ልጅ

በአንድ ወቅት ራሳቸውን በምድር ላይ ካሉ እንስሳት ሁሉ በላይ አድርገው የሚቆጥሩ የአይጥ መንጋ አባላት ነበሩ። አይጦቹም በጣም ትምክህተኞችና ህልመኞች የነበሩ ሲሆን ራሱን ከእነርሱ በላይ አድርጎ የሚመለከት አንድ ከሁሉም መጥፎ ንጉስ ነበራቸው።

ከጊዜ በኋላ ንጉሱ አይጥ ልጅ ወልዶ “ተመልከቱ! ልጄ በምድር ላይ ካሉ ፍጡራን ሁሉ የላቀ ፍጡር ስለሆነ በተመሳሳይ ደረጃ ላይ የምትገኝ ሚስት እንዲኖረው እፈልጋለሁ።” አለ። “ነገር ግን እዚህ ምድር ላይ ካሉት የማይረቡ እንስሳት አንዷም ለሚስትነት ልጄን ስለማትመጥነው የጭጋግን ልጅ ነው ማግባት ያለበት” አለ።

ስለዚህ የአገር ሽማግሌዎችን ሰብስቦ “ሂዱችሁ ጭጋግን ልጁን እንዲድርልን ጠይቁት።” አላቸው።

እነርሱም ወደ ጭጋግ ሂደው “እጅግ በጣም ግሩም ልጅ አለን፤ ቆንጆ ጎበዝና የተለየ ነው። እናም ሴት ልጅህ ለልጃችን ሚስት ትሆነው ዘንድ እንድትሰጠን እንፈልጋለን” አሉት።

**** ጭጋግ ልጁን የሚድርለት ይመስላችኃል?****

የጋብቻ ጥያቄ የቀረበለት ጭጋግ “ከምትናገሩት ነገር በመነሳት ልጃችሁ ምን ያህል ልዩ እንደሆነ ማወቅ ችያለሁ። እንዲያውም ልጁ እጅግ በጣም ልዩ ስለሆነ ከእኔ ልጅ የተሻለች ማግባት ያለበት ይመስለኛል።” አላቸው።

የአገር ሽማግሌዎቹ ግን “ተመልከት፣ አንተ ከፍጥረታት ሁሉ የላቅህ እንደሆንክ እናውቃለን።” አሉት።

ጭጋግም እንዲህ አላቸው “አይሆንም፣ እኔ ሰማይ ላይ የምኖር ነኝ፤ንፋስ መቶ ሲያባርረኝ የምጠፋ ነኝ። ስለዚህ ሂዳችሁ የንፋስን ልጅ ጠይቁ፣ በጣም ቆንጆ ናት።” አላቸው

ሽማግሌዎቹም ወደ ንጉሱ ሂደው “ተመልከት፣ ጭጋግ ንፋስ ከኔ ይበልጣል ካለ ትክክል መሆን አለበት” አሉት።

***ቀጥሎስ ምን የሚሆን ይመስላችኋል?***

ንጉሱም ሽማግሌዎቹ ወደ ንፋስ ሄደው ልጁን ለጋብቻ እንዲጠይቁ ላካቸው። እናም ሽማግሌዎቹ ወደ ንፋሱ ቤተ መንግስት ሄደው "ተመልከት እኛ ከሁሉ የላቀ ሃያለኛ ልጅ አለን። አንተም ቆንጆ ሴት ልጅ እንዳለህ ሰምተናልና ልናጋባቸው እንችላለን?" ብለው ጠየቁት። "ንፋሱም እስኪ ስለ ልጁ አጫውቱኝ" አላቸው።

ሽማግሌዎቹም "ልጃችን ቆንጆ፣ ጎበዝና ታላቅ ነው" አሉት። "ንፋስም እንደዚያማ ከሆነ ልጃችን ከእርሱ ስለምታንስ ከእርሷ የበለጠችዋን ነው ማግባት ያለበት" አላቸው። በዚሁ ተሰነባበቱ።

## አዳምጦ የመረዳት ጥያቄዎች

### መልመጃ አንድ

**ሀ. ባዳመጡት መሰረት በቃል እንዲመልሱ ያድርጉ**

### ክፍለ ጊዜ ሁለት

ለ. መምህር ተማሪዎቹ ለጥያቄዎቹ መልስ ባዳመጡት መሰረት ሲሰጡ መጀመሪያ ለሶስት እንዲወያዩ በማድረግ ይሁን። ለሶስት ተነጋግረው የተስማሙበትን ሃሳብ የሚያቀርቡት እርስዎ በሚሰጧቸው ቅደም ተከተል በቡድን ተወካይ በኩል ይሁን።

### ክፍለ ጊዜ ሶስት

## ትምህርት ሁለት፡ መናገር

### ተግባር አንድ

**መምህር** ተማሪዎች ስለሚያውቁት አንድ የዱር አውሬ እና ስለሚያደንቁት የዱር እንስሳ ለምን እንደሚያደንቁት ጭምር እንዲናገሩ በማድረግ ንግግርን እንዲለማመዱ ያድርጉ። የንግግር ሂደታቸውን በመከታተል አስፈላጊውን እርማትና ድጋፍ ያድርጉላቸው።

### ክፍለ ጊዜ አራት

### መልመጃ ሁለት

**መምህር** ተማሪዎች ስለኒያላ፣ አንበሳ፣ ወይም ነብር ወይም በአካባቢያቸው ስለሚታወቅ የዱር እንስሳ ታሪክ ቤተሰቦቻችሁን ጠይቀው ያገኙትን ሀሳብ ተዘጋጅተውበት ለክፍል ጓደኞቻቸው ንግግር እንዲያደርጉ ያድርጉ። ስራውን እንዲዘጋጁበት ከክፍለጊዜው በፊት

በየቤት ሰራነት ይስጧቸው።

**ክፍለጊዜ አምስት**

## ተግባር ሶስት

**መምህር** ተማሪዎች አይጥ በሰው ላይ ስለምታደርሳቸው ጉዳቶች ጠይቀው ለክፍል ጓደኞቻቸው በንግግር እንዲያቀርቡ መልመጃውን ቀድመው ያሳውቋቸው።

**ክፍለጊዜ ስድስት**

## ትምህርት ሶስት፡ መነጠልና ማጣመር

### መልመጃ ሁለት

### ሀ. መነጠል

**መምህር** ተማሪዎች ቃላትን ወደ ቀለም ወይም ድምጽ መነጠልን ብዙ ጊዜ መለማመዳቸውን ያስታውሷቸው። በመማሪያ መጽሐፍ ላይ የቀረቡትን የዱር እንስሳት ስም ቀለማት እየነጣጠሉ በጭብጨባ አጅበው በምሳሌው መሰረት ነጥለው እንዲጠሩ ያድርጉ።

**ክፍለጊዜ ሰባት**

### ለ. ማጣመር

**መምህር** ተማሪዎች ቀለምን ወይም ድምጽን በማጣመር ቃላት መፍጠራትን ብዙ ጊዜ መለማመዳቸውን ያስታውሷቸው። በመማሪያ መጽሐፍ ላይ የቀረቡትን የዱር እንስሳት ስሞችን በመጀመሪያ የተነጠሉ ቀለማትን በጭብጨባ አጅበው እንዲጠሩ እና በምሳሌው መሰረት አጣምረው እንዲናገሩ ግልጽ መመሪያ ይስጧቸው።

**ክፍለጊዜ ስምንት**

## ትምህርት አራት፡ የቃላት ጥናት

### መልመጃ ሶስት

**መምህር** ተማሪዎች በመማሪያ መጽሐፍ ላይ በሰንጠረዥ ከቀረቡት ፊደላት እየመረጡ በክፍት ቦታዎች ላይ እያስገቡ ቃላትን እንዲመሰርቱ ያድርጓቸው። ተግባሩን በመጀመሪያ በየግላቸው ይስሩት። በመቀጠል ለሁለት በየስራዎቻቸው ላይ ይነጋገሩ። በመጨረሻ ከተወሰኑ ተማሪዎች የሰሩትን ይቀበሉ። የተማሪዎቹን መልስ ሰሌዳ ላይ እየጻፉ ስለትክክለኝነቱ ሌሎች ተማሪዎች እንዲናገሩ ያድርጉ።

## ክፍለጊዜ ዘጠኝ

## መልመጃ አራት

### ሀ. የመጀመሪያ ሆሄ (ቅጥያ) በመግደፍ አዲስ ቃል መመስረት

መምህር ተማሪዎች በመማሪያ መጽሐፍ ላይ ከቀረቡ ቃላት የመጀመሪያውን ፊደል በመግደፍ አዲስ ቃል እንዲመሰርቱ መመሪያ ይስጧቸው። የመሰረቱትን ቃል በማስታወሻ ደብተራቸው ላይ ይጻፉትና ሲጠየቁ ያንብቡ።

### ለ. የመጨረሻ ሆሄ (ቅጥያ) በመግደፍ አዲስ ቃል መመስረት

መምህር ተማሪዎች በመማሪያ መጽሐፍ ላይ ከቀረቡ ቃላት የመጨረሻውን ፊደል በመግደፍ አዲስ ቃል እንዲመሰርቱ መመሪያ ይስጧቸው። የመሰረቱትን ቃል በማስታወሻ ደብተራቸው ላይ ይጻፉትና ሲጠየቁ ያንብቡት።

## ክፍለጊዜ አስር

## መልመጃ አምስት

መምህር ተማሪዎች በመማሪያ መጽሐፍ ላይ ከቀረቡ ቃላት የመጀመሪያውን ፊደል በመተካት አዲስ ቃል እንዲመሰርቱ መመሪያ ይስጧቸው። የመሰረቱትን ቃል ማስታወሻ ደብተራቸው ላይ ይጻፉና ሲጠየቁ ያንብቡ። በዚህ መልመጃ የሚመሰረቱት ቃላት ከአንድ በላይ ሊሆኑ ስለሚችሉ ተማሪዎች በቀረቡት ቃላት በየንዳንዳቸው የቻሉትን ያህል ቃላት እንዲመሰርቱ በቂ ጊዜ ይስጧቸው። ተማሪዎች ስራውን ሲሰሩ ክፍል ውስጥ እየተዘዋወሩ ሂደቱን ይከታተሉ። አስፈላጊ በሆነበት የማስተካከያ ምጋቤ ምላሽ የስጧቸው።

## ክፍለጊዜ አስራ አንድ

## መልመጃ ስድስት

መምህር ተማሪዎች በመማሪያ መጽሐፍ ላይ ከቀረቡ ቃላት የመጨረሻውን ፊደል በመተካት አዲስ ቃል እንዲመሰርቱ መመሪያ ይስጧቸው። የመሰረቱትን ቃል ማስታወሻ ደብተራቸው ላይ ይጻፉትና ሲጠየቁ ያንብቡ። በዚህ መልመጃ የሚመሰረቱት ቃላት ከአንድ በላይ ሊሆኑ ስለሚችሉ ተማሪዎች በቀረቡት ቃላት በየንዳንዳቸው የቻሉትን ያህል ቃላት እንዲመሰርቱ በቂ ጊዜ ይስጧቸው። ተማሪዎች ስራውን ሲሰሩ ክፍል ውስጥ እየተዘዋወሩ ሂደቱን ይከታተሉ። አስፈላጊ በሆነበት የማስተካከያ ምጋቤ ምላሽ የስጧቸው።

## ክፍለጊዜ አስራ ሁለት

## ትምህርት አምስት፡ ማንበብ

## ዝሆንና ሌሎች እንሰሳት

*መምህር፣ ተማሪዎች መፅሐፋቸውን ክፍለጊዜ አስራ ሁለትን እንዲያወጡ ያድርጉ። ርዕሱን "ዝሆንና ሌሎች እንሰሳት" እንዲያነቡ ያድርጉና የተነበበውን ርዕስ ጥቁር ሰሌዳ ላይ ይፃፉ። በመቀጠልም መማሪያ መጽሐፍ ላይ ያለውን የቅድመንባብ ጥያቄ እጅ በማውጣት በየተራ እያነበቡ እንዲመልሱ በመጠየቅ ከተወሰኑ ተማሪዎች መልስ ይቀበሉ። ተማሪዎቹ ማንበብ ከመጀመራቸው በፊት የንባብ ጊዜ ጥያቄዎቹን እንዲያነቡ ያድርጉ። ምክንያቱም ለጥያቄዎቹ መልስ የሚያገኙት በቀጥታ ከምንባቡ ውስጥ እያነበቡ እንደሆነና ለዚህም ጥያቄዎቹን በአእምሮአቸው ይዘው ማንበብ እንዳለባቸውም ያሳውቋቸው። ካነበቡም በኋላ የአንብቦ መረዳት ጥያቄዎችን መስራት እንደሚጠበቅባቸው ያስታውሷቸው። በመልመጃውም አንብበው መረዳታቸውን ይፈትሹ።*

### አንብቦ መረዳት

### መልመጃ ሰባት

*መምህር እባኮ ተማሪዎቹ የምንበቡን ዋና ዋና ነጥቦችን ዘርዝረው በጽሁፍ እንዲያዘጋጁ ይንገሯቸው።*

## ክፍለጊዜ አስራ ሶስት

### ተግባር አራት

*መምህር ለፍጥነት ንባብ የቀረበውን ጽሁፍ ተማሪዎች በየተራ በትክክለኛ ቅላጼና ፍጥነት እንዲያነቡ ያድርጉ። የማያነቡት ተማሪዎች ደግሞ መጽሐፋቸውን ይዘው አንባቢን እንዲከታተሉ ያድርጉ። በሂደቱ ውስጥ የሚታዩ ጠንካራ ጎኖችን በማድነቅ ሊሻሻሉ በሚገባቸውም ላይ ሀሳብ ይስጧው።*

## ክፍለጊዜ አስራ አራት

### ተግባር አምስት

*መምህር ተማሪዎች መማሪያ መጽሐፍ ላይ ለዚሁ አላማ የቀረበውን ጽሁፍ ተጠቅመው እርስ በርስ የሚገማገሙበትን ዘዴና ምን እንደሚያስፈልጋቸው በግልጽ ያስረዷቸው።*

የሚነበበውን መጽሐፋቸው ውስጥ ያለውን እንዲጠቀሙ ያድርጉ። ለጊዜ መቆጣጠሪያ ሰዓት ወይም ተንቀሳቃሽ ስልክ መጠቀም እንደሚችሉ ይግለጹላቸው።

የሚነበበው ለአንድ ደቂቃ ብቻ ነው። አንድ ደቂቃ ባለቀበት ምልክት ተደርጎ ንባቡ መቆም እንዳለበት ይንገሯቸው። ንባቡ ከቆመ በኋላ መጨረሻ ንባቡ የቆመበት ድረስ በጠቅላላው ስንት ቃላት እንደሆኑ መቁጠርና ከተቆጠሩት ቃላት ውስጥ በትክክል ያልተነበቡትን እንዲቀንሱ ይንገሯቸው። ተቀናንሶ የሚገኘው ውጤት የተማሪው/ የተማሪዋ የአንድ ደቂቃ የንባብ ፍጥነት እንደሚሆን ያሳውቋቸው።

የአንዳቸው ሲያልቅ የሌላቸውም ሚና በመቀያየር በተመሳሳይ መንገድ መፈጸም እንደሚጠበቅባቸው ያስረዷቸው።

መምህር ተማሪዎችዎ እርስ በርስ ሲገማገሙ ሂደቱን በመከታተል አስፈላጊውን ድጋፍ ያድርጉላቸው።

## ክፍለጊዜ አስራ አምስት

## ትምህርት ስድስት፡ መጻፍ

### መልመጃ ስምንት

**ቃለአጋኖ ወይም የጥያቄ ምልክት መጠቀም**

**መምህር** ተማሪዎችዎ የስርዓተ ነጥብ አጠቃቀም ተረድተው ይተገብሩ ዘንድ ምልክቶችን በጥቁር ሰሌዳው ላይ በመጻፍ አጠቃቀማችውን ምሳሌ እየሰጡ ያስገንዝቧቸው። ከዚያም በመማሪያ መጽሀፍ ላይ ባሉት አረፍተነገሮች ውስጥ ከተጠቀሱት ስርዓተ ነጥቦች ውስጥ በመምረጥ በተገቢው ቦታ እንዲያስገቡ ትእዛዝ ይስጧቸው። በአግባቡ ማስገባታቸውንም ያረጋግጡ።

## ክፍለጊዜ አስራ ስድስት

### መልመጃ ዘጠኝ

**መምህር** ተማሪዎች የሚከተሉትን እንዲሰሩ ይዘዟቸው።

1. በመኖሪያ አከባቢያቸው ያሉትን የዱር እንሰሳት በዝርዝር ይጻፉ።
2. ስለዱር እንስሳት የሚያወሱ ሁለት ሁለት አረፍተነገሮችን ይጻፉ።

## ክፍለጊዜ አስራ ሰባት

### መልመጃ አስር

መምህር በመማሪያ መጽሐፍ ላይ ቅደም ተከተላቸው ተዛንፈው የቀረቡትን ቃላት ቅደም ተከተላቸውን አስተካክለውና አስፈላጊውን ስርአተነጥብ አስገብተው እንዲጽፉ ይዘዟቸው። አስተካከለው የጻፉትን እጅ በማውጣት እንዲያነቡ ያድርጉ። ሌሎች ተማሪዎች ስለትክክለኝነቱ አስተያየት እንዲሰጡ ያድርጉ።

## ክፍለጊዜ አስራ ስምንት

## መልመጃ አስራ አንድ

መምህር በተማሪዎችዎ መማሪያ መጽሀፍ ክፍለጊዜ፡ አስራ ስምንት ስር የቀረቡትን ቃላት በመጠቀም አረፍተነገር እንዲያዋቅሩ ያድርጉ። ያዋቀሯቸውን አረፍተነገሮች በጥንድ አንዳቸው ለሌላቸው እንዲያነቡና እርማት እንዲሰጣጡ ያድርጉ።

በመጨረሻ ፈቃደኛ የሆነ/ች ተማሪ ለክፍል ያዋቀረውን/ችውን እንዲያነቡ ያድርጉ። ለክፍል የተነበበውን አረፍተነገር እርስዎ በጥቁር ሰሌዳ ላይ ይጻፉት። ከክፍል ተማሪዎች ውስጥ በአረፍተነገሩ ላይ ሀሳብ ለመስጠት ፈቃደኛ የሆነ/ች ተማሪ አስተያየት እንዲሰጡ ይጋብዙ። በተሰጠ አስተያየትና ለክፍል በተነበቡ አረፍተነገሮች ላይ የማጠቃለያ ሀሳብ በመስጠት ትምህርቱን ይቋጩ።

# መልሶች

## ምዕራፍ አንድ

### ክፍለጊዜ አንድ

1. ቡሉኮ፣ ቀሚስ፣ ጋቢ
2. ኮት፣ ሱሪ፣ ሸሚዝ፣ ሹራብ

### ክፍለጊዜ ሁለት

1. አገልግሎት/ቀለም
2. ቀለም

### ክፍለጊዜ አስራ ሁለት

1. ባህላዊ፣ 2. መቀነት፣ 3. ነጭ፣ 4. ጥጥ 5. ቆሪ

# ምዕራፍ ሁለት

## ክፊፍለጊዜ አስራ ሶስት

1. ድልድይ 2. ውይይት 3. ችግር

## ክፊፍለጊዜ አስራ አራት

1. ወንዝ 2. የገቢሳና የድባቤ ቤተሰቦች (የሁለቱ ቤተሰቦች) ሊሉ ይችላሉ
3. የውይይት አስፈላጊነት መተሳሰብ የመሳሰሉትን ሊሉ ይችላሉ።

## ክፍለጊዜ አስራ ስምንት

2. ተማሪዎቹ በጋራ በማጥናታቸው ጎበዙ/ጥሩ ውጤት አገኙ :: ወላጆቻቸውም ባመጡት ውጤት ደስተኛ ሆኑ:: በዚህም በጋራ ማጥናት/መስራት ለውጤት እንደሚያበቃ_ ተገነዘቡ::

# ምዕራፍ ሶስት

## ክፍለጊዜ አስራ አንድ

1. አሰለፈ= አለፈ፣
2. አወለቀ = አወቀ፣ አለቀ
3. አፈሰሰ = አሰሰ፣ አፈሰ
4. አበጠረ = አበረ፣ አጠረ
5. ምርቃት = ምርት
6. አነበቡ = አነቡ፣ አበቡ

## ክፍለጊዜ አስራ ሶስት

1. ሐሰት 2.እውነት 3. እውነት 4. ሐሰት 5. እውነት

## ክፍለጊዜ አስራ አራት

1. ቀርፋፋ 2.በሩጫ 3. ሩጫውን 4. ጋደም 5.ከእንቅልፏ

## ክፍለጊዜ አስራ ሰባት

### መልመጃ ስድስት

1. ጎሽ! እንኳን መጣህ!
2. መቼ ትመጪያለሽ?
3. ቤቱ ትልቅ ነው።
4. የመፅሐፉ ዋጋ ስንት ነው?
5. እሰይ! ምኞቴ ተሳካ።

# ምዕራፍ አራት

## ክፍለጊዜ ሰባት

1. ፈተና  2.. ሜዳ  3. ቤተመጻህፍት  4 ሰልፍ  5. ባንዲራ  6.ኳስ

## ክፍለጊዜ አስራ አምስት

1. ምቹ  2. ማዳበሪያ  3. ማዕድኖችን  4. ለምነት  5. ማስዋብ
6. ኖረው  7. ለም  8. ተመራጭ  9. ተብላልቶ  10. ይበላሻል

## ክፍለጊዜ አስራ ስድስት

1. ለም
2. ተመራጭ
3. ማመቻቸት
4. የሚመረት
5. ሰው ሰራሽ

ሀ. ተፈላጊ
ለ. የዳበረ
ሐ. በፋብሪካ የሚመረት
መ. ማስተካከል
ሠ. የሚሰራ

## ክፍለጊዜ አስራ ስምንት

1. በለጠ ኳስ ተጫወተ።
2. ኡፈይ! አረፍኩ!
3. ክፍሉን ያጸዳው ማነው?
4. ልጁ ጠንክሮ ስለሰራ ተሸለመ።
5. በሬው በስንት ብር ተሸጠ?
6. በሪቴ የት ሄደች?

# ምዕራፍ አምስት

## ክፍለጊዜ ሁለት

**መልመጃ አንድ፡ ሀ.**

1. የግቢያቸው መቆሸሽ  2. የቢንቢ

**መልመጃ አንድ፡ ለ.**

1. እውነት  2. እውነት  3. ሐሰት  4. ሐሰት  5. እውነት

## ክፍለጊዜ አስር

1. __ ተና  <u>ፈ</u>ተና/<u>ጉ</u>ተና/<u>ብ</u>ተና  2. __ ልስ  <u>መ</u>ልስ

3. __ ያቄ ጥያቄ

4. __ ብተር ደብተር

5. __ ጽሐፍ መጽሐፍ

6. __ ፍል ክፍል

## ክፍለጊዜ አስራ አንድ፡ “ለ”

1. ጥያ__ ጥያቄ
2. ወንበ__ ወንበር
3. ክፍ __ ክፍል
4. እርሳ__ እርሳስ
5. መቀ__ መቀስ
6. መልመ_ መልመጃ

## ክፍለጊዜ አስራ አንድ፡ “ሐ”

1. ቦርሳ
2. መልስ
3. ወንበር
4. እርሳስ
5. ደብተር
6. መልመጃ

## ክፍለጊዜ አስራ አምስት፡ ሠ

ከሰንጠረዥ ሊወጡ የሚችሉ ቃላት

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| አበረ | አበጠ | አጠበ | አበራ | አበሰ | አበሰረ |
| አበጠረ | በጠሰ | በረረ | ሰረበ | ሰበራ | ሰመረ |
| ሰመጠ | ሰስ | ሰራ | ረጠበ | ጠራ | ጠበሰ |
| መራ | መኖ | መሰጠ | መረጠ | መስኖ | ስስ |
| ስራ | ኖረ | ኖራ | ራራ | ራሰ | ራበ |
| ራስ | | | | | |

# ምዕራፍ ስድስት

## ክፍለጊዜ ስምንት

### መልመጃ አራት

መልስሊሆኑ የሚችሉ

1. ክራር በክራር፣ ለክራር፣ ከክራር
2. ጎሰመ ጎሰመች፣ በጎሰመ፣ ለጎሰመ፣ መጎሰም
3. ደወለ መደወል፣ ደዋይ፣ ደወለች
4. መታ በመታ፣ ከመታ፣ ለመታ
5. ጽናፅል በጽናጽል፣ ለጽናጽል
6. ቃጭል በቃጭል፣ለቃጭል፣ ከቃጭል

## ክፍለጊዜ አስራ አንድ

### ሀ. የመጀመሪያ ቅጥያ ተገድፎ

| | | |
|---|---|---|
| 1. | ስለጎሰመ | ስለጎሰመ |
| 2. | ስለነፋ | ስለነፋ |
| 3. | በነጋሪት | ነጋሪት |
| 4. | እንደዋሽንት | ዋሽንት |

### ለ. የመጨረሻ ቅጥያ ተገድፎ

| | | |
|---|---|---|
| 1. | ጎሳሚዎች | ጎሳሚ |
| 2. | ደርዳሪዎች | ደርዳሪ |
| 3. | መቺዎች | መቺ |
| 4. | ገዝጋዦች | ገዝጋዥ |

## ምዕራፍ ስምንት

### ክፍለጊዜ ሰባት ሀ

| | | | |
|---|---|---|---|
| 1. | በማዕድ | በ | መዕድ |
| 2. | ለማዘጋጀት | ለ | ማዘጋጀት |
| 3. | የሚያገለግሉ | የሚ | ያገለግሉ |
| 4. | የተለያዩ | የ | ተለያዩ |
| 5. | የምግብ | የ | ምግብ |

### ክፍለጊዜ ሰባት ለ.መነሻ ቅጥያ ማጣመር

1. የግድ =
2. በጽዳት=
3. የሽንኩርት=
4. ከድስት=
5. በማንኪያ=

## መልመጃ አምስት

## ክፍለጊዜ ስምንት

ቃልና ቅጥያ ተነጥሎ

1. ትልቅ ም
2. ቁሳቁስ ኦች
3. እቃ ዎች
4. ቢላ ዎች
5. ሳህን ኦች
6. ሹካ ዎች

**ለ.ቃላትን ከመድረሻ ቅጥያዎች ጋር አጣምሩ።**

1. ቀረሁ
2. በላን
3. ወሰደች
4. ሀገራችን
5. ቤታቸው

## ክፍለጊዜ ዘጠኝ

**መልመጃ ስድስት**

ለምሳሌ፡ ሰለጠነ፣ ሰጠ፣ ነጠለ

| 1.አበሰለ | 2.ቀላቀለች | 3.አቀረበ | 4. ዘይት |
|---|---|---|---|
| በሰለ | ቀላ | ቀረበ | ይዘት |
| ለበሰ | ላቀች | ቀበረ | ትይ |
| አበሰ | ቀላች | አቀበ | |
| ሰለበ | ቀላቀለ | አበረ | |
| አሰበ | ላቀ | | |

**ምዕራፍ ዘጠኝ**

## ክፍለጊዜ ስድስት

**መልመጃ አራት**

| | | |
|---|---|---|
| 1.ትሰፋለች | ት | ሰፋለች |
| 2.ይሄዳሉ | ይ | ሄዳሉ |
| 3.ተከመረ | ተ | ከመረ |
| 4. ከታብሌት | ከ | ታብሌት |
| 5. ለሲም | ለ | ሲም |
| 6. ከድረገጽ | ከ | ድረገጽ |
| 7. በድረገጽ | በ | ድረገጽ |
| 8. የደወለ | የ | ደወለ |
| 9. በፌስቡክ | በ | ፌስቡክ |

## ክፍለጊዜ ሰባት ለ

| | | | |
|---|---|---|---|
| 1.መጣ | -ሽ | 6. ኮምፒዩተር | -ኦች |
| 2.ሰራ | -ህ | 7.ታብሌት | -ሽ |
| 3.ሄድ | -አችሁ | 8.ስልክ | -ህ |
| 4.በላ | -ን | 9. ላፕቶፕ | -ኦች |
| 5.ወሰደ | -ች | 10.ድረገጽ | -ኦች |

## ክፍለጊዜ ስምንት ሐ

| ቃል | መነሻቅጥያ | መጨረሻቅጥያ |
|---|---|---|
| ከስልካችን | ከ- | -አችን |
| በላፕቶፖች | በ- | -ኦች |
| የታብሌትሽ | የ- | -ሽ |
| በፌስቡካችሁ | በ- | -አችሁ |
| በድረገጻቸው | በ- | -አቸው |
| ከቴሌቭዥናችን | ከ- | -አችን |
| በድረገጹ | በ- | -ኡ |

## ክፍለጊዜ ዘጠኝ

<u>መ</u> 1. የግል ሀ. በከባድ

<u>ሐ</u> 2. በአግባቡ ለ. ለማዳከም

<u>ሀ</u> 3. በቀላል ሐ. ያለአግባብ

<u>ለ</u> 4.ለማጠናከር መ. የቡድን

| | |
|---|---|
| 1. ጠቃሚ | ጎጂ |
| 2. በርትታ | ደክማ |
| 3. ለማጠናከር | ለማዳከም |
| 4. ዘወትር | አንዳንድ ጊዜ/አልፎ አልፎ |
| 5. ጥንታዊ | ዘመናዊ |

# መርሃ ትምህርት

## የሁለተኛ ክፍል የአንደኛ ወሰነ ትምህርት መርሃ ትምህርት

**ምእራፍ አንድ፡ አልባሳት(18 ክፍለ ጊዜ)**

**ከዚህ ምእራፍ ትምህርት በኋላ ተማሪዎች**

- ምንባብን አዳምጠው አጠቃላይ መልእክት ይለያሉ፤
- ምንባብን አንብቦ ዋና መልእክትን ይለያሉ፤
- ለተዘውታሪ ቃላት ፍች ይሰጣሉ፤
- ባለ ሶስት ቀለም ቃላትን ይነጣጥላሉ፤ያጣምራሉ፤
- የፊደል ድምጸ ግንኙነትን ይጽፋሉ።

| ብቃት | ይዘት | የመማር ብልሃቶችና መሳሪያዎች | ምዘና |
|---|---|---|---|
| • ከሚደመጥ ምንባብ አጠቃላይ ሀሳብን መለየት<br>• ምንባብን አንብቦ ዋና መልእክትን መለየት<br>• ለተለመዱ ቃላት ፍች መስጠት<br>• ባለሶስት ቀለም ቃላትን መነጠልና ማጣመር<br>• የፊደል ድምጽ ተዛምዶን መጻፍ | **ማዳመጥን መናገር**<br>**ድምጻዊ ግንዛቤ**<br>**ትዕምርተ ድምጸ ግንዛቤ**<br><br>**የቃላት ጥናት**ተዘውታሪ ቃላት(የትምህርት ቃላት)<br><br>**ማንበብና መጻፍ**<br>**ማንበብ፡ትክክለኛነት፣ በፍጥነት፣በመግለጽ፣በመረዳት**<br><br>**መጻፍ፡ ድምጸትን** | መምህር ስለሚደመጠው ጉዳይ ቁንጽል መረጃዎችን መናገር። ጥቂት ጥያቄዎችን በሰሌዳ ላይ መጻፍ። ከዚያም ተማሪዎች እያዳመጡ መመለስ። መምህር ስለርእሰ ጉዳዩ መረጃዎችን መናገር። በተለመዱ ቃላት ላይ መወያየት፤መምህር ምንባቡን ድምጻቸውን ከፍ አድርጎ ማንበብ። በተማሪው መማሪያ መጽሀፍ ላይ ያሉትን አንብቦ የመረዳት ጥቄዎች መስራት።<br>**መነጠልና ማጣመር፡-** ተማሪዎች ቃላትን በፍጥነት መጥራት። (በዚህ ጊዜመምህር መነጠልን ለማሳየት ድምጾችን ያዋህዳል) እና መነጠልን ለማሳየት ቀለሞችን ወይም ድምጾችን በተከታታይ መነጠል።ተማሪዎች ቃላትን ወደ ሁለት ቀለሞችና ድምጾች ነጥለው ማጣመር።<br>**ማተካካት፡**<br>ሀ. መግደፍ-ተማሪዎች ቃላትን አዳምጠው በመነሻ ላይ ያለውን ቀለም/ድምጽ በመግደፍ ማንበብ።<br>ለ. መጨመር-ተማሪዎች ቃላት | በቃልና በጽሁፍ ጥያቄዎችን መጠየቅ ከካላዊ ምላሽ የተማሪዎች በግል ለጥያቄዎች የሚመልሱት አካላዊ ምላሽ ኢ.መደበኛ ቁጥጥር ምልከታ በስዕል መወከል ተራ በተራ ማቅረብ ስልታዊ ልምምድ የመውጫ ካርድ |

| | | | |
|---|---|---|---|
| | **በትክክል መረዳት** | ሲጠሩ አዳምጠው በቃላቱ ላይ ቀለሞችን ፣ድምጾችን መጨመር። <br>ሐ. ተማሪዎች ቃላት ሲነገሩ አዳምጠው በቃላት ውስጥ ያሉትን ቀለሞች ወይም ድምጾች በሌሎች መተካት። (/የድምጾችን/የፊደላትን ቅርጽ፣የባለቀለም ወረቀት ፣የካርቱን ስዕሎች ፣የቃላት ካርድ፣ ሰሌዳ መጠቀም)<br><br>**ተዘውታሪ ቃላት፡**የተማሪዎች ልምድ በከፍተና ደረጃ የሚደጋገሙ ቃላትን በምንባብ ውስጥ እንዲለዩ ያደርጋቸዋል።በምንባብ ውስጥም ውጪም ወዲያውኑ መለየት።<br>**በቃል መጻፍ፡**መምህርቃላትን ሲያነብ ተማሪዎች በትክክል ይጽፋሉ ።ተማሪ ቃሉን ያዳምጣል ከዚያም ለመጻፍ መሞከር።<br>**የግድግዳ ላይ ቃል፡**መምህርመነሻ እንዲሆነው ቃላትን ጽፎ በግድግዳ ላይ መለጠፍ።<br>ተማሪ በግድግዳ ላይ የተለጣጠፉትን ቃላት የፍቻቸውን ውህደት ይመለከታል።<br>**ተደጋጋሚ ቃላዊ ንባብ፡** ይህ ተደጋጋሚ ቃላዊ ንባብ በማቅረብ ከጓደኛ፣ከመምህራንና ከቤተሰብ ምላሽ ማግኘት።<br>**በጊዜ የተገደበ ተደጋጋሚ ንባብ፡**ተማሪዎች አጭር ምንባብን ብዙ ጊዜ ያነባሉ።እያንዳንዱን ንባብም በጊዜ ይገድባል።የንባብ ፍጥነትንም ለውጡን በቻርት ማስቀመጥ።<br>**አረፍተ ነገርን ደጋግሞ ማንበብ -** አንድ አረፍተ ነገር ብዙ ጊዜ | |

| | | | |
|---|---|---|---|
| | | ማንበብ።በእያንዳንዱ ጊዜ የተለየው ቃል ትኩረት መስጠት።<br>የፊደል -ድምጽ ግንኙነት፣ቃላት፣አረፍተ ነገሮች<br>**ለምልክቶች ትኩረት መስጠት፡** አገላለጽን ለማሻሻል መምህር በግልጽ ስርዐተ ነጥብ አላማ በመግለጽ እንዴት እነዚህ ምልክቶች በአገላለጽና በድምጸት ላይ ተጸእኖ እንደሚደርጉ ማብራራት።<br>መምህር ተማሪዎችን በቡድን ማስቀመጥ።ስርዓተ ነጥቦችን(አራት ነጥብ፣የጥያቄ ምልክት፣) ያልያዘ አጭር ምንባብ ለተማሪዎች መስጠት፤ ተማሪዎች ተራ በተራ ድምጻቸውን ከፍ አድርገው ማንበብ። ከዚያም መምህርተማሪዎች ያለ ስርዓተ ነጥበ ማንበብ ቀላል ወይም ከባድ መሆኑን ይጠይቃል።ይሄ ለምን ሆነ፤ምን ማለት እንችላለን የስርዓተ ነጥብ አገልግሎት ነው ማለት እንችላለን እንዴት ይረዳናል ከዚያም ተማሪዎች አራት ነጥብ በሚገባበት ቦታ ከጓደኞቻቸው ጋር መጠቀም።<br>**በቡድን መጻፍ**፡ መምህር አርዐያ በመሆን ተማሪዎች አንድ የጋራ ንባብ እንዲጽፉ ማበረታታት። | |

**ምእራፍ ሁለት፡ ወቅቶች (18 ክፍለጊዜ)**
**ከትምህርቱ የሚጠበቁ ውጤቶች**
ከዚህ ምዕራፍ ትምህርት በኋላ ተማሪዎች

- ምንባቡን በማድመጥ ዝርዝር ሀሳቦችን ይለያሉ፤
- በቃል የምንባቡን መልእክት ይናገራሉ፤
- ወቅቶች ከሚለው ቃል ጋር የሚቀራረቡ የቃላት ትርጎሞችን ይሰጣሉ፤
- ድምጾችን ከቃላት የመነጠልና የማጣመር (ድምጾችን/ፊደላትን ለይተው መዘርዘር) ተግባር ይፈጽማሉ፤
- የሚታወቁ ባለ አራት ቀለም ቃላትን ይጽፋሉ፤
- አራት ነጥብንና ጥያቄ ምልክቶችን ይለያሉ።

| ብቃት | ይዘት | የመማር ብልሃትና መሳሪያዎች | ምዘና |
|---|---|---|---|
| • ካዳመጡት ምንባብ ዋና ሀሳብ መለየት<br>• የምንባቡን ዋና ሀሳብ መናገር<br>• ለቃላት ትርጉም መስጠት<br>• ከምንባቡ ለወጡ ጥያቄዎች መልስ መስጠት<br>• ድምጾችን መነጠልና ማጣመር<br>• ቀለል ያሉ የማህበረሰቡን ተረቶች መናገር | **መናገርና ማዳመጥ**<br><br>**ስነድምጻዊ ግንዛቤ**<br>**ትዕምርተ ድምጻዊ ግንዛቤ**<br><br>**የቃላት ጥናት**<br>ተዘውታሪ ቃላት(የትምህርት ቃላት)<br>-የቃላት ዕውቀት ማሳደግ<br><br>**ማንበብና መጻፍ**<br>**ማንበብ፡ትክክለኛነት፣ በፍጥነት፣በመግለጽ፣በመረዳ ት** | መመህሩ ስለርዕሱ የቀደመዕውቀታቸውን ለማነሳሳት ለተማሪዎች የተወሰኑ ቅድመንባብ ጥያቄዎችን ማቅረብ። በከፊል የተሞሉ የቢ.ጋር ሰንጠረዥችን በማቅረብ ቀሪውን ተማሪዎች እንዲሞሉ ማድረግ። መምህርድምጹን ከፍ አድርጎ ሲያነብ የቀረውን ተማሪዎች በቃል ባዶ ቦታውን መሙላት። ተማሪዎች ከወቅቶች ጋር የሚቀራረቡ ቃላትን እንዲለዩ ማድረግ። (ለምሳሌ፡- በሳምንት ውስጥ ያሉ ቀናት፣በአመት ውስጥ ያሉትን ወራት፣የበጋ ወቅት፣ክረምት፣መከር) የአከባቢውን ወቅታዊ ሁኔታ ማሰብ **መነጠልና ማጣመር ፡** ተማሪዎች በቃሉ ውስጥ ያሉትን ድምጾች በመነጠል መናገር። (በፍጥነት ማስባል)በመቀጠል | ቃላዊ/ጽሁፋዊ ጥያቄዎችን መጠየቅ አካላዊ ምላሽ ተማሪዎች በግላቸው ለጥያቄዎች የሚሰጡት ምላሽ በአካል ኢ.መደበኛ ቁጥጥር ምልከታ በሚታይ መወከል ተራ በተራ ማቅረብ የመውጫ ካርዶች ጽብረቃ ስልታዊ ልምምድ |

| | | | |
|---|---|---|---|
| | **መጻፍ፡ ድምጸትን በትክክል መረዳት** | (መምህር መነጠልን ለማሳየት ፊደላትን ማጣመር)። ተማሪዎች ቃሉን ጠርተው በቃሉ ውስጥ ያሉትን ቀለሞችና ድምጾች በመጥራት ማጣመር።<br><br>**ማተካካት፡** መምህር ተማሪዎች የገደፉትን ቃላት መልሶ መተካት።<br>ሀ.መግደፍ ፡- ተማሪዎች ቃላትን ካዳመጡ በኋላ ድምጾችን/ቀለማትን እንደመጀመሪያው ሳይጠሩ መቀየር<br>ለ.መጨመር ፡- ተማሪዎች ባዳመጡት ቃል ላይ ድምጽን/ምዕላድን መጨመር<br>ሐ.መተካት ተማሪዎች ካዳመጡት ቃል ሌላ ድምጽ/ምእላድ መተካት (የድምጾችን/የፊደላትን ቅርጽ፣ የባለቀለም ወረቀት፣ የካርቱን ስዕሎች፣ የቃላት ካርድ፣ ሰሌዳ ወዘተ መጠቀም)<br><br>**ከምንባቡ ጋር ማዛመድ** ተማሪዎች ምንባቡን በማንበብ መጻፍ መለማመድ፣የሚጻፈውም ምንባቡ ነው።<br>**ተዘውታሪ ቃል፡** ተማሪዎች ከምንባቡ ውስጥና ከምንባቡ ውጭ ከፍተኛ | |

| | | | |
|---|---|---|---|
| | | ድግግሞሽ ያላቸውን ቃላት ፈጥነው የመለየት ልምድ ማዳበር። **በቃል መጻፍ** ተማሪዎች ቃላትን አዳምጠው በትክክል ለመጻፍ መሞከር። **የግድግዳ ላይ ቃላት** መምህር ቃላትን ጽፈው ግድግዳ ላይ በመለጠፍ እንደማጣቀሻ መጠቀም። ተማሪዎች በተራ ተዘውታሪ ቃላትን ፍች መግልገል። **ተደጋጋሚ ቃላዊ ንባብ፡** ይህ ተደጋጋሚ ቃላዊ ንባብ በማቅረብ ከጓደኛ፣ከመምህራንና ከቤተሰብ ምላሽ ማግኘትን ይመለከታል። **በጊዜ የተገደበ ተደጋጋሚ ንባብ፡** ተማሪዎች አጭር ምንባብን ብዙ ጊዜ ያነባሉ። እያንዳንዱን ንባብም በጊዜ መገደብ። የንባብ ፍጥነትንም ለውጡን በቻርት ማስቀመጥ። **አረፍተ ነገሮችን ማድመቅ፡** አንድ አረፍተ ነገር ብዙ ጊዜ ማንበብ። በእያንዳንዱ ጊዜ የተለየው ቃል ትኩረት መስጠት። **የፊደል -ድምጽ ግንኙነት፣ቃላት፣አረፍተ ነገሮች ለምልክቶች ትኩረት መስጠት፡** አገላለጽን | |

| | | | |
|---|---|---|---|
| | | ለማሻሻል<br>መምህርበግልጽ<br>የምልክቶችን አላማ<br>በመግለጽ እንዴት<br>እነዚህ ምልክቶች<br>በአገላለጽና በድምጸት<br>ላይ ተጸእኖ<br>እንደሚደርጉ<br>ያብራራል።<br>መምህርተማሪዎችን<br>በቡድን ማስቀመጥ።<br>ስርዓት ነጥቦችን<br>(አራት ነጥብ፣የጥያቄ<br>ምልክት፣) ያልያዘ<br>አጭር ምንባብ<br>ለተማሪዎች ይሰጣል፤<br>ተማሪዎች ተራ በተራ<br>ድምጻቸውን ከፍ<br>አድርገው ማንበብ።<br>ከዚያም መምህር<br>ተማሪዎች ያለ ስርዓት<br>ነጥበ ማንበብ ቀላል<br>ወይም ከባድ መሆኑን<br>ይጠይቃል።ይሄ ለምን<br>ሆነ፤ምን ማለት<br>እንችላለን የስርዓት<br>ነጥብ አገልግሎት ነው<br>ማለት እንችላለን<br>እንዴት ይረዳናል<br>ከዚያም ተማሪዎች<br>አራት ነጥብ<br>በሚገባበት ቦታ<br>ከጓደኞቻቸው ጋር<br>ያስገባሉ።<br>በቡድን<br>መጻፍ፡መምህርአርዐያ<br>በመሆን ተማሪዎች<br>አንድ የጋራ ንባብ<br>እንዲጽፉ<br>ማበረታታት። | |

**ምእራፍ ሶስት ተረቶች (18 ክፍለ ጊዜ)**

**ከትምህርቱ የሚጠበቁ ውጤቶች**

ከዚህ ምዕራፍ ትምህርት በኋላ ተማሪዎች

- ምንባቡን አዳምጠው ዋና ሀሳቡን በመለየት በቃል ይዘግባሉ፤
- ያነበቡትን ምንባብ አጠቃላይ ሀሳብ ይጽፋሉ፤
- በአረፍተ ነገር ውስጥ አራት ነጥብን ይጠቀማሉ፤
- ባለአራት ቀለም ቃላትን ይጽፋሉ፤
- ቃለአጋኖንና የጥያቄ ምልክትን ይጠቀማሉ።

| ብቃት | ይዘት | የመማር ብልሃቶችና መሳሪያዎች | ምዘና |
|---|---|---|---|
| • ካዳመጡት ምንባብ ዋናሀሳቡን ለይተው የተወሰኑትን ዝርዝሮች በቃል ይዘግባሉ።<br>• ካነበቡት አጠቃላይ ሀሳብን ይጽፋሉ።<br>• ቃለአጋኖንና የጥያቄ ምልክትን በአረፍተ ነገር ውስጥ ይጠቀማሉ።<br>• ባለአራት ቀለም ቃላትን ይጽፋሉ። | **መናገርና ማዳመጥ**<br><br><br><br><br><br>**ስነድምጻዊ ግንዛቤ ትዕምርተ ድምጻዊ ግንዛቤ**<br><br>**የቃላት ጥናት**<br>ተዘውታሪ ቃላት(የትምህርት ቃላት)<br>-የቃላት ዕውቀት ማሳደግ<br>-የጽንሰ ሀሳብ ስያሜ<br><br><br>**ማንበብና መጻፍ**<br>**ማንበብ፡ትክክለኛነት፣ በፍጥነት፣በመግለጽ፣በመረዳት**<br><br>**መጻፍ፡ ድምጸትን በትክክል መረዳት** | መምህር ቅድመ ማዳመጥ ጥያቄዎችን አቅርበው የተማሪዎችን የቀደመ እውቀታቸውን መጠቀም። ጮክ ብሎ ማንበብ። ተማሪዎች ቃላዊ ዘገባ ያቀርባሉ። መምህርቅድመ ንባብ ጥያቄዎችን አቅርቦ ተማሪዎችን የቀደመ እውቀታቸውን ይጠይቃል። ጮክ ብሎ ያነባል። ተማሪው አሳጥሮ በጽሁፍ ማቅረብ። **ማተካካት፡**መምህርተማሪ ዎች ከቃላት ላይ የሚያጠፉትን፣ የሚጨምሩትንና የሚተኩትን ቀለሞች/ድምጾች መናገር።<br>ሀ.መግደፍ፡ተማሪዎች ቃላትን ካዳመጡ በኋላ ድምጾችን/ ቀለማትን በቃል መነሻ ላይ ያሉትን ቀለሞች/ ድምጾች በመተው መጥራት።<br>ለ.መጨመር ተማሪዎች ባዳመጡት ቃል ላይ ድምጽን/ ምዕላድን ይጨምራሉ። | ቃላዊ/ጽሁፋዊ ጥያቄዎችን መጠየቅ አካላዊ ምላሽ ተማሪዎች በግላቸው ለጥያቄዎች የሚሰጡት ምላሽ በአካል ኢመደበኛ ቁጥጥር ምልከታ በሚታይ መወከ ተራ በተራ ማቅረብ የመውጫ ካርዶች ጽብረቃ ስልታዊ ልምምድ |

| | | | |
|---|---|---|---|
| | | ሐ.መተካት ተማሪዎች ካዳመጡት ቃል ሌላ ድምጽ/ ምእላድ መተካት።<br><br>**መናገር፡** መምህር ቃሉን ካሳየ በኋላ በቃሉ ውስጥ ያሉትን ድምጾች ይጠሩና ድምጾቹን መነጠል (የታወቁ ትዕምርተ ድምጽ ግንዛቤን ተጠቀም) ተማሪዎች ቃልን ወስደው ድምጾችን መነጠልን ይለማመዳሉ (የታወቁ ትዕምርተ ድምጽ ግንዛቤን ተጠቅመው) (የድምጾችን/የፊደላትን ቅርጽ፣የባለቀለም ወረቀት ፣የካርቱን ስዕሎች ፣የቃላት ካርድ፣ ሰሌዳ መጠቀም)<br>የሚገናኙ ምንባቦች፡ ተማሪዎች ማንበብን መለማመድ።<br>**ከምንባቡ ጋር ማዛመድ** መምህር በተደጋጋሚ ምንባቡን ያነባል ተማሪዎችም መምህሩን ተከትለው ያነባሉ።ተማሪዎች መጻፍ መለማመድ።<br>**ተደጋጋሚ ቃላዊ ንባብ፡**ይህ ተደጋጋሚ ቃላዊ ንባብ በማቅረብ ከጓደኛ፣ ከመምህራንና ከቤተሰብ ምላሽ ያገኛል።<br>*በጊዜ የተገደበ ተደጋጋሚ* ንባብ፡ተማሪዎች አጭር ምንባብን ብዙ ጊዜ ማንበብ። እያንዳንዱን ንባብም በጊዜ ይገድባል። የንባብ ፍጥነትንም ለውጡን በቻርት | |

| | | | |
|---|---|---|---|
| | | ማስቀመጥ።<br>**የአረፍተ ነገር ቅኝት፡**አንድ አ/ነገር ብዙ ጊዜ ማንበብ። በእንዳንዱ ንባብ ጊዜ እንዳንዱ ቃል ላይ ትኩረት መስጠት።<br>የፊደል -ድምጽ ግንኙነት፣ቃላት፣አረፍተ ነገሮች<br>**ለምልክቶች ትኩረት መስጠት፡** አገላለጽን ለማሻሻል መምህርበግልጽ የምልክቶችን አላማ በመግለጽ እንዴት እነዚህ ምልክቶች በአገላለጽና በድምጸት ላይ ተጽእኖ እንደሚደርጉ ማብራራት።<br>***በቡድን መጻፍ***፡ መምህርአርአያ በመሆን ተማሪዎች አንድ የጋራ ንባብ እንዲጽፉ ማበረታታት። | |

**ምዕራፍ አራት፡- የአትክልት ቦታ(18 ክፍለ ጊዜ)**

**ከትምህርቱ የሚጠበቁ ውጤቶች**

ከዚህ ምዕራፍ ትምህርት በኋላ ተማሪዎች

- ከሚያዳምጡት ነገር ዝርዝር መረጃዎችን ይለያሉ፤
- ከሚያነቡት ጽሁፍ ዋና ሀሳቦችን ይጽፋሉ፤
- ቃለአጋኖንና የጥያቄ ምልክትን ይለያሉ።

| ብቃት | ይዘት | የመማር ብልሃቶችና መሳሪያዎች | ምዘና |
|---|---|---|---|
| • ከሚያዳምጡት ነገር ዝርዝር መረጃዎችን መለየት<br>• ከሚያዳምጡት ነገር ዝርዝር መረጃዎችን መጻፍ<br>• ቃለአጋኖንና የጥያቄ ምልክትን መለየት<br>• ድምጾችን ከቃላት መነጠልና ማጣመር | **ማዳመጥና መናገር**<br><br>**ድምጻዊ ግንዛቤ**<br>**የትዕምርተ ድምጽ ግንዛቤ**<br><br>**የቃላት ጥናት፡** ተዘውታሪ (የትምህርት) ቃላት -ጽንሰሃሳቦችን መሰየም<br><br>**ማንበብና መጻፍ**<br><br>**ማንበብ፡ትክክለኛነት፣ፍጥነት፣ጥሩ አገላለጽ፣አንብቦ መረዳት**<br><br>**መጻፍ፡ትክክለኛነት**<br>**ድምጸታዊ ግንዛቤ** | መምህር የተማሪዎችን ቀደመ እውቀት መቀስቀስ። በተማሪው የሚሞላ ቻርት ማዘጋጀት። መምህርተማሪዎች ከሚያዳምጡት ነገር ቻርቱን እንዲሞሉ ማድረግ። **መነጠልን ማጣመር፡** መምህርሞዴል ሆኖ ቃላትን ከድምጾች ጋር ድምጾችን ደግሞ ከቃላት ጋር መነጠልንና ማጣመርን ማሳየት። ተማሪዎች በቃላት ውስጥ ድምጾችን ከዚያም ቃላትን በፍጠነት መጥራት (ፊደላትን አገናኝቶ ማጣመርን ያሳያል) ከዚያም እያንዳንዱን ቀለም ወይም ድምጽ መጥራት። **ማተካካት፡** መምህር ተማሪዎች ጨዋታ እንዲወዳደሩ በቡድን ማስቀመጥ። ተራ በተራ ከቃላት ላይ ድምጾችን/ቀለማትን የመግደፍ ፣የመጨመርና የማተካካት ጨዋታ እንዲጫወቱ መንገር። ጨዋታው ለማጠናቀቅ የሚፈጀው ጊዜ ላይ ይመሰረታል። ጨዋታውን ቀድሞ ያጠናቀቀ ነጥብ ያገኛል። ይህም ጨዋታውን | በጽሁፍ ጥያቄዎችን መጠየቅ ከካላዊ ምላሽ የተማሪዎች በግል ለጥያቄዎች የሚመልሱት አካላዊ ምላሽ ኢመደበኛ ቁጥበቃልና ጥር ምልከታ በስዕል መወከል ተራ በተራ ማቅረብ ስልታዊ ልምምድ የመውጫ ካርድ |

| | | | |
|---|---|---|---|
| | | ይጫወታል። ሰዓት አስከባሪ፣ውጤት መዝጋቢና መሪ መሆን።<br>ሀ.ተማሪዎች ቃላቱን ካነበቡ በኋላ በቃሉ መነሻ ላይ ያለውን ቀለም/ድምጽ በመተው መጥራት።<br>ለ. ተማሪዎች ቃላቱን ካዳመጡ በኋላ ቀለሞችን /ድምጾችን መጨመር።<br>ሐ.ማተካካት፡ተማሪዎች ካዳመጡ በኋላ በቃሉ ላይ ያሉትን ቀለማትን/ድምጾችን ይቀይራሉ<br>መናገር፡መምህርቃሉን ካሳየ በኋላ በቃሉ ውስጥ ያሉትን ድምጾች ይጠራና ድምጾቹን ይነጥላል(የታወቁ ትዕምርተ ድምጽ ግንዛቤን ተጠቀም)ተማሪዎች ቃልን ወስደው ድምጾችን መነጠልን ይለማመዳሉ(የታወቁ ትዕምርተ ድምጽ ግንዛቤን ተጠቅመው)(የድምጾችን/የፊደላትን ቅርጽ፣የባለቀለም ወረቀት ፣የካርቱን ስዕሎች ፣የቃላት ካርድ፣ ሰሌዳ ተጠቀም)<br>የሚገናኙ ምንባቦች፡ ተማሪዎች ማንበብን መለማመድ።<br>**ተደጋጋሚ ቃላዊ ንባብ፡**ይህ ተደጋጋሚ ቃላዊ ንባብ በማቅረብ ከጓደኛ፣ከመምህራንና ከቤተሰብ ምላሽ ማግኘት።<br>**በጊዜ የተገደበ ተደጋጋሚ ንባብ፡** ተማሪዎች አጭር ምንባብን ብዙ ጊዜ ያነባሉ። እያንዳንዱን ንባብም በጊዜ መገደብ። የንባብ ፍጥነትንም ለውጡን | |

| | | | |
|---|---|---|---|
| | | በቻርት ማስቀመጥ። **የአረፍተ ነገር ቅኝት** ፡አንድ አረፍተ ነገር ብዙ ጊዜ ማንበብ። በእንዳንዱ ንባብ ጊዜ እንዳንዱ ቃል ላይ ትኩረት መስጠት።የፊደል -ድምጽ ግንኙነት፣ቃላት፣አ/ነገሮች **ለምልክቶች ትኩረት መስጠት፡** አገላለጽን ለማሻሻል መምህርበግልጽ የምልክቶችን አላማ በመግለጽ እንዴት እነዚህ ምልክቶች በአገላለጽና በድምጸት ላይ ተጽእኖ እንደሚደርጉ ማብራራት። **በቡድን መጻፍ፡**መምህርአርዐያ በመሆን ተማሪዎች አንድ የጋራ ንባብ እንዲጽፉ ማበረታታት። | |

**ምዕራፍ አምስት ፡የአከባቢ ጽዳት(18 ክፍለ ጊዜ)**

**ከትምህርቱ የሚጠበቁ ውጤቶች**

ከዚህ ምዕራፍ ትምህርት በኋላ ተማሪዎች

- ከሚያዳምጡት ነገር አዳዲስ ቃላትን ይሰጣሉ፤
- ከሚያነቡት ጽሁፍ ዝርዝር ሀሳቦችን ይለያሉ፤
- ቃለአጋኖንና የጥያቄ ምልክትን ይለያሉ።

| ብቃቶች | ይዘቶች | የመማር ብልሃቶችና መሳሪያዎች | ምዘና |
|---|---|---|---|
| • ከሚያዳምጡት ነገር አዳዲስ ቃላትን ይሰጣሉ።<br>• ከሚያነቡት ጽሁፍ ዝርዝር ሀሳቦችን ይለያሉ።<br>• ቃለአጋኖንና የጥያቄ ምልክትን ይለያሉ።<br>• አራት ነጥብን በአረፍተነገር ውስጥ ይጠቀማሉ። | **ማዳመጥና መናገር**<br>**ድምጻዊ ግንዛቤ**<br>**የትዕምርተ ድምጽ ግንዛቤ**<br>**የቃላት ጥናት**፡ተዘውታሪ(የትምህርት)ቃላት<br>-ጽንሰሃሳቦችን መሰየም<br>**ማንበብና መጻፍ**<br>**ማንበብ፡ትክክለኛነት፣ፍጥነት፣ጥሩ አገላለጽ፣አንብቦ መረዳት**<br>**መጻፍ፡ትክክለኛነት ድምጸታዊ ግንዛቤ** | መምህርየተማሪዎችን የቀደመ እውቀት ያነሳሳል።በተማሪው የሚሞላ ቻርት ያዘጋጃል።መምህርተማሪዎች ከሚያዳምጡት ነገር ቻርቱን እንዲሞሉ ማድረግ።<br>**መነጠልና ማጣመር**፡ተማሪዎች በቃል ውስጥ ያለውን ድምጽ በፍጥነት ይጠራሉ።(መምህርማጣመርን ለማሳየት ፊደላትን ያሳያል።ከዚያም መነጠልን ለማሳየት ቀለሞችን/ድምጾችን መጥራት።<br>**ማተካካት**፡ መምህር ተማሪዎች ጨዋታ እንዲወዳደሩ በቡድን ያስቀምጣቸዋል።ተራ በተራ ከቃላት ላይ ድምጾችን/ቀለማትን የማጥፋት ፣የመጨመርና የማተካካት ጨዋታ እንዲጫወቱ መንገር። ጨዋታውን ለማጠናቀቅ የሚፈጀው ጊዜ ላይ ይመሰረታል። ጨዋታውን ቀድሞ ያጠናቀቀ ነጥብ ያገኛል። ይህም ጨዋታውን ይጫወታል። ሰዓት አስከባሪ፣ውጤት መዝጋቢና መሪ ይሆናል። | በጽሁፍ/በቃል ጥያቄዎችን መጠየቅ<br>አካላዊ ምላሽ<br>ተማሪዎች በግል ለጥያቄዎች የሚመልሱት አካላዊ ምላሽ<br>ኢ.መደበኛ ቁጥጥር<br>ምልከታ<br>በስዕል መወከል<br>ተራ በተራ ማቅረብ<br>ስልታዊ ልምምድ<br>የመውጫ ካርድ |

| | | | |
|---|---|---|---|
| | | ሀ.መግደፍ -ተማሪዎች ቃላቱን ካነበቡ በኋላ በቃሉ መነሻ ላይ ያለውን ቀለም/ድምጽ በመተው መጥራት። ለ. መጨመር-ተማሪዎች ቃላቱን ካዳመጡ በኋላ ቀለሞችን /ድምጾችን መጨመር። ሐ.መተካት-ተማሪዎች ካዳመጡ በኋላ በቃሉ ላይ ያሉትን ቀለማትን/ድምጾችን መቀየር **መናገር**፡ መምህርቃሉን ካሳየ በኋላ በቃሉ ውስጥ ያሉትን ድምጾች ይጠራና ድምጾቹን ይነጥላል(የታወቁ ትዕምርተ ድምጽ ግንዛቤን ተጠቀም)ተማሪዎች ቃልን ወስደው ድምጾችን መነጠልን ይለማመዳሉ(የታወቁ ትዕምርተ ድምጽ ግንዛቤን ተጠቅመው) **በቃል መጻፍ፡** መምህርበግድግዳ ላይ ያሉትን ቃላት ያነባል።ተማሪው አዳምጦ በትክክል ይጽፋል። (የድምጾችን/የፊደላትን ቅርጽ፣የባለቀለም ወረቀት ፣የካርቱን ስዕሎች ፣የቃላት ካርድ፣ ሰሌዳ መጠቀም) **ከምንባቡ ጋር ማገናኘት፡** ተማሪዎች ማንበብን ይለማመዳሉ።<br><br>**ተደጋጋሚ ቃላዊ ንባብ፡** ይህ ተደጋጋሚ ቃላዊ ንባብ በማቅረብ ከጓደኛ፣ከመምህራንና ከቤተሰብ ምላሽ ማግኘት። **በጊዜ የተገደበ ተደጋጋሚ** | |

| | | | |
|---|---|---|---|
| | | **ንባብ፡** ተማሪዎች አጭር ምንባብን ብዙ ጊዜ ያነባሉ።እያንዳንዱን ንባብም በጊዜ ይገድባል።የንባብ ፍጥነትንም ለውጡን በቻርት ማስቀመጥ። **የአረፍተ ነገር ቅኝት ፡** አንድ አረፍተ ነገር ብዙ ጊዜ ይነበባል።በእንዳንዱ ንባብ ጊዜ እንዳንዱ ቃል ላይ ትኩረት መስጠት።የፊደል -ድምጽ ግንኙነት፣ቃላት፣አ/ነገሮች **ለምልክቶች ትኩረት መስጠት፡** አገላለጽን ለማሻሻል መምህርበግልጽ የምልክቶችን አላማ በመግለጽ እንዴት እነዚህ ምልክቶች በአገላለጽና በድምጸት ላይ ተጽእኖ እንደሚያደርጉ ማብራራት። **በቡድን መጻፍ፡** መምህርአርአያ በመሆን ተማሪዎች አንድ የጋራ ንባብ እንዲጽፉ ማብራራት። | |

# የሁለተኛ ክፍል ሁለተኛ ወሰነ ትምህርት መርሃ ትምህርት

**ምዕራፍ ስድስት ፡ባህላዊ ሙዚቃ (18 ክፍለ ጊዜ)**

**ከትምህርቱ የሚጠበቁ ውጤቶች**

ከዚህ ምዕራፍ ትምህርት በኋላ ተማሪዎች

- ምንባቡን በማዳመጥ በተዘውታሪ ቃላት ቀላል አረፍተ ነገሮችን ይገነባሉ፣
- የተዘውታሪ ቃላትን ትርጉም በምንባቡ መሰረት ይለያሉ፣
- ቃለአጋኖና ይጥያቄ ምልክትን ይጠቀማሉ፣
- ቅጥያዎችን ቃላት ላይ በመጨመር ይናገራሉ።

| ብቃቶች | ይዘቶች | የመማር ብልሃቶችና መሳሪያዎች | ምዘና |
|---|---|---|---|
| • ምንባብን አዳምጠው አጭር ታሪክ ይጽፋሉ።<br>• በምንባቡ መሰረት የተዘውታሪ ቃላትን ትርጉም መስጠት<br>• ቃለአጋኖንና የጥያቄ ምልክት መጠቀም<br>• ቅጥያዎችን ቃላት ላይ ጨምሮ መናገር | **ማዳመጥና መናገር**<br>**ድምጻዊ ግንዛቤ**<br>**የትዕምርተ ድምጽ ግንዛቤ**<br>**የቃላት ጥናት፡** ተዘውታሪ(የትምህርት )ቃላት -ጽንሰሃሳቦችን መሰየም<br>**ማንበብና መጻፍ**<br>**ማንበብ፡ትክክለኛነት፣ ፍጥነት፣ጥሩ አገላለጽ፣አንብቦ መረዳት**<br>**መጻፍ፡ትክክለኛነት ድምጸታዊ ግንዛቤ** | መምህርየተማሪዎችን የቀደመ እውቀት ተጠቅሞ ያነሳሳቸዋል።የተወሰኑ ቅድመ ማዳመጥ ጥያቄዎችን መጠየቅ። ምንባቡን ድምጹን ከፍ አድርጎ ያነባል።ተማሪዎችን በቡድን ያስቀምጣል። በደብተራቸውም ላይ ካዳመጡት ምንባብ አንድ ሀሳብ መጻፍ።<br>**ማጣመርና መነጠል፡** ተማሪዎች በአንድ ቃል ውስጥ ያሉ ድምጾችን ጠርተው ቃሉን በፍጥነት ይላሉ። (መምህር ማጣመርን ለማሳየት ፊደላትን ያሳያል።ከዚያም መነጠልን ለማሳየት ቀለሞችን/ ድምጾችን መጥራት) (የድምጾችን/የፊደላትን ቅርጽ፣የባለቀለም ወረቀት ፣የካርቱን ስዕሎች ፣የቃላት ካርድ፣ ሰሌዳ መጠቀም)<br>**መለየት፡**ተማሪዎች ቃላት በተመሳሳይ ድምጽ የሚጀምሩና የሚጨርሱ መሆናቸውን ይወስናሉ።<br>**ተመሳሳይ ዜማ፡** ተማሪዎች ተመሳሳይ ዜማ ያላቸውን ቤተሰባዊ ቃላትን መጥራት።<br>**ቃላትን መመስረት፡** ተማሪዎች መጻፍን መለማመድ።<br>**ተዘውታሪ ቃላት፡**መምህር ከምንባቡ ውስጥ ከፍተኛ ድግግሞሽ ያላቸውን ቃላት | በጽሁፍ/በቃል ጥያቄዎችን መጠየቅ<br>አካላዊ ምላሽ<br>ተማሪዎች በግል ለጥያቄዎች የሚመልሱት አካላዊ ምላሽ<br>ኢ-መደበኛ ቁጥጥር<br>ምልከታ<br>በስዕል መወከል<br>ተራ በተራ ማቅረብ<br>ስልታዊ ልምምድ<br>የመውጫ ካርድ |

| | | | |
|---|---|---|---|
| | | ይለያሉ።ተማሪዎች ከፍተኛ ድግግሞሽ ያላቸውን ቃላት ከምንባቡ ውስጥም ሆነ ውጭ ፈጥኖ የመለየት ልምድ ማዳበር።<br>**በቃል መጻፍ፡** መምህር ተማሪዎች በቃል የሚጽፏቸውን ሁለት አረፍተ ነገሮች ማዘጋጀት። ተማሪዎችም መምህር የሚያነባቸውን አረፍተነገሮች በማዳመጥ በትክክል መጻፍ።<br>**ግድግዳ ላይ የተለጠፉ ቃላት፡**ተማሪዎች አዳዲስ ቃላትን ባወቁ ጊዜ መምህር በወረቀት ላይ በመጻፍ በግድግዳ ላይ ለጥፎ እንደማጣቀሻ መጠቀም።<br>**ስዕላዊ መግለጫ** የቃላት ካርታ፣ቻርትን መረዳት፣ቃላትን መፈለግ<br>**ጆርናሎችን መረዳት**:ተማሪዎች ጆርናል አንብበው የቀደመ እውቀታቸውን ይገነባሉ፤የቀደመ እውቀታቸውን አውጥተው ማንጸባረቅ።<br>**አውድን ማዛመድ፡**ተማሪዎች የሚዛመዱ አውዶችን አንብበው መልዕክቱን ማግኘት።<br>**ቀስበቀስ ማብቃት** ፡በገደል ማሚቶ፣በህብረት ማንበብ፣ከጓደኛ ጋር ማንበብ፣በሹክሹክታ ማንበብ<br>**በጊዜ የተገደበ ንባበብ፡** ተማሪዎች አጭር ምንባብን ብዙ ጊዜ ማንበብ።እያንዳንዱን ንባብም ሰዓት ይመዘግቡለታል፤ለውጡንም ለመመልከት በቻርት ማስቀመጥ።<br>**መከፋፈል፡** ተማሪዎች ሀረጋትን ከፋፍለው ማንበብ።<br>**መገመት፡** መምህር ለተማሪዎች በሚሰጣቸው ፍንጭ ላይ መሰረት አድርገው ስለምን ሊያነቡ እንደሚችሉ እንዲገምቱ መጠየቅ።<br>**መጠየቅ፡** ተማሪዎች ጥያቄ መጠየቅ እንዲችሉ እድል መስጠት።<br>**ተቀናጅቶ ድምጽን ከፍ በማድረግ** | |

| | | | |
|---|---|---|---|
| | | **ማንበብ፡** መምህር አንድ አጭር ታሪክ ያዘጋጃል። ተማሪዎች አጭር ታሪክ በማንበብ ይሳተፋሉ። ታሪኩን በቡድን ይከፋፈላሉ። አንዱ ቡድን ጮክ ብሎ ሲያነብ ሌላኛው የተነበበውን የታሪክ ክፍል ዋና ሀሳብ መናገር። **ተደጋጋሚ ቃላዊ ንባብ** ለተማሪዎች ቃላዊ ንባብ በማካሄድ ከመምህራን፣ከጓደኛ ምላሽ ያገኛሉ። **በጊዜ የተገደበ ንባብ** ተማሪዎች አጭር ምንባብን ብዙ ጊዜ ያነባሉ። እያንዳንዱን ንባብም ሰዓት ይመዘግቡለታል፤ለውጡንም ለመመልከት በቻርት ማስቀመጥ። **የአረፍተ ነገር ቅኝት፡** አንድ አረፍተ ነገር ብዙ ጊዜ ማንበብ። በእያንዳንዱ ንባብ ጊዜ እንዳንዱ ቃል ላይ ትኩረት ይሰጣል።የፊደል-ድምጽ ግንኙነት፣ቃላት፣ በአ/ነገሮች **ማጠቃለያ** መረጃዎችን በተደራጀና በተጠቃለለ መልክ ማቅረብን ማለማመድ። የፊደል ድምጽ ግንኙነት፣ቃላት፣አረፍተ ነገር **ለምልክቶች ትኩረት መስጠት፡** አገላለጽን ለማሻሻል መምህርበግልጽ የምልክቶችን አላማ በመግለጽ እንዴት እነዚህ ምልክቶች በአገላለጽና በድምጸት ላይ ተጽእኖ እንደሚያደርጉ ማብራራት፡ **በቡድን መጻፍ፡** መምህር አርዐያ በመሆን ተማሪዎች አንድ የጋራ ንባብ እንዲጽፉ ማበረታታት። | |

**ምዕራፍ ሰባት ፡መልካም ጠባይ (18 ክፍለ ጊዜ)**

**ከትምህርቱ የሚጠበቁ ውጤቶች**

ከዚህ ምዕራፍ ትምህርት በኋላ ተማሪዎች

- ከምንባቡ የወጡ አዳዲስ ቃላትን ተጠቅሞ ቀላል አረፍተነገሮችን ይመሰርታሉ፤
- ከምንባቡ ለወጡ ቃላት አገባባዊ ፍች ይሰጣሉ፤
- ተመሳሳይ ቅጥያ ያላቸውን ቃላት ይዘረዝራሉ፤
- ተቀባይነት ባለው የፍጥነት ደረጃ አጭር ታሪክ ያነባሉ፤
- ቃላትን በትክክል ይጽፋሉ።

| ብቃት | ይዘቶች | የመማር ብልሃቶችና መሳሪያዎች | ምዘና |
|---|---|---|---|
| • ምንባቡን በማዳመጥ በአዳዲስ ቃላት ቀላል ታሪኮችን ይገነባሉ።<br>• ለቃላት አገባባዊ ፍች ይሰጣሉ።<br>• ተመሳሳይ ቅጥያ ያላቸውን ቃላት ይዘረዝራሉ።<br>• በተገቢው ፍጥነት አጭር ታሪክ ያነባሉ።<br>• ቃላትን አስተካክለው ይጽፋሉ። | **ማዳመጥና መናገር**<br><br>**ድምጻዊ ግንዛቤ**<br>**የትዕምርተ ድምጽ ግንዛቤ**<br><br>**የቃላት ጥናት፡**<br>ተዘውታሪ(የትምህርት) ቃላት<br>-ጽንሰሃሳቦችን መሰየም<br><br>**ማንበብና መጻፍ**<br><br>**ማንበብ፡ትክክለኛነት፣ፍጥነት፣ጥሩ አገላለጽ፣አንብቦ መረዳት**<br><br>**መጻፍ፡ትክክለኛነት ድምጸታዊ ግንዛቤ** | መምህርየተማሪዎችን የቀደመ እውቀት ተጠቅሞ ያነሳሳቸዋል።የተወሰኑ ቅድመ ማዳመጥ ጥያቄዎችን መመለስ። ምንባቡን ድምጹን ከፍ አድርጎ ያነባል። ተማሪዎችን በቡድን ያስቀምጣል። በደብተራቸውም ላይ ካዳመጡት ምንባብ አንድ ሀሳብ በመጻፍ አጭር ታሪክ መጻፍ።<br>**ተመሳሳይ ዜማ፡** ተማሪዎች ተመሳሳይ ዜማ ያላቸውን ቤተሰባዊ ቃላትን መፍጠር።<br>**ቃላትን መመስረት፡**ተማሪዎች መጻፍን መለማመድ።<br>**አውድን ማዛመድ** ተማሪዎች የሚዛመዱ አውዶችን ማንበብ።(የድምጾችን/የፊደላትን ቅርጽ፣የባለቀለም ወረቀት ፣የካርቱን ስዕሎች ፣የቃላት ካርድ፣ ሰሌዳ መጠቀም)<br>**ግድግዳ ላይ የተለጠፉ ቃላት፡** ተማሪዎች አዳዲስ ቃላትን ባወቁ ጊዜ መምህር በወረቀት ላይ በመጻፍ በግድግዳ ላይ ለጥፎ እንደማጣቀሻ መጠቀም።<br>**ስዕላዊ መግለጫ** የቃላት ካርታ፣ቻርትን መረዳት፣ቃላትን መፈለግ<br>**ተዘውታሪ ቃላት፡**መምህር ከምንባቡ ውስጥ ከፍተኛ ድግግሞሽ ያላቸውን ቃላት መለየት።ተማሪዎች ከፍተኛ | በጽሁፍ/በቃል<br>ጥያቄዎችን መጠየቅ<br>አካላዊ ምላሽ<br>ተማሪዎች በግል ለጥያቄዎች የሚመልሱት አካላዊ ምላሽ<br>ኢ-መደበኛ ቁጥጥር<br>ምልከታ<br>በስዕል መወከል<br>ተራ በተራ ማቅረብ<br>ስልታዊ ልምምድ<br>የመውጫ ካርድ |

| | | | |
|---|---|---|---|
| | | ድግግሞሽ ያላቸውን ቃላት ከምንባቡ ውስጥም ሆነ ውጭ ፈጥኖ የመለየት ልምድ ያዳብራሉ። **ቀስበቀስ ማብቃት** ፡በገደል ማሚቶ፣በህብረት ማንበብ፣ከጓደኛ ጋር ማንበብ፣በቀስታ ማንበብ **በጊዜ የተገደበ ንባበብ፡** ተማሪዎች አጭር ምንባብን ብዙ ጊዜ ማንበብ። እያንዳንዱን ንባብም ሰዓት መመዝገብ፤ለውጡንም ለመመልከት በቻርት ማስቀመጥ። **መከፋፈል** ፡ ተማሪዎች ሀረጋትን ከፋፍለው ማንበብ። **በርካታ እድሎችን መፍጠር፡**ዳራዊ እውቀት መገንባት፡የቀደመ እውቀት ማንጸባረቅ **መገመት፡** መምህርለተማሪዎች በሚሰጣቸው ፍንጭ ላይ መሰረት አድርገው ስለምን ሊያነቡ እንደሚችሉ እንዲገምቱ መጠየቅ። **መጠየቅ፡** ተማሪዎች ጥያቄ መጠየቅ እንዲችሉ እድል መስጠት። **ተቀናጅቶ ድምጽን ከፍ በማድረግ ማንበብ፡** ተማሪዎች በታሪኩ ውስጥ መሳተፍ (የድምጾችን/የፊደላትን ቅርጽ፣የባለቀለም ወረቀት ፣የካርቱን ስዕሎች ፣የቃላት ካርድ፣ ሰሌዳ መጠቀም) **በቃል መጻፍ፡**መምህር ሶስት ተራ አረፍተ ነገሮችን በቃል ለማጻፍ ማዘጋጀት። መምህርተማሪዎች በቃል የሚጽፏቸውን ሶስት ተራ አረፍተ ነገሮች ያዘጋጃል። ተማሪዎችም መምህር የሚያነባቸውን አረፍተነገሮች በማዳመጥ በትክክል መጻፍ። | |

| | | | |
|---|---|---|---|
| | | **ተደጋጋሚ ቃላዊ ንባብ** ለተማሪዎች ቃላዊ ንባብ በማካሄድ ከመምህራን፣ከጓደኛ ምላሽ ማግኘት። **በጊዜ የተገደበ ንባብ** ተማሪዎች አጭር ምንባብን ብዙ ጊዜ ማንበብ። እያንዳንዱን ንባብም ሰዓት ይመዘግቡለታል፤ለውጡንም ለመመልከት በቻርት ማስቀመጥ። **የአረፍተ ነገር ቅኝት፡** አንድ አረፍተ ነገር ብዙ ጊዜ ይነበባል። በእያንዳንዱ ንባብ ጊዜ እንዳንዱ ቃል ላይ ትኩረት መስጠት።የፊደል-ድምጽ ግንኙነት፣ቃላት፣ በአ/ነገሮች **ማጠቃለያ** መረጃዎችን በተደራጀና በተጠቃለለ መልክ ማቅረብን ያለማምዳል። የፊደል ድምጽ ግንኙነት፣ቃላት፣አረፍተ ነገር **ለምልክቶች ትኩረት መስጠት፡** አገላለጽን ለማሻሻል መምህርበግልጽ የምልክቶችን አላማ በመግለጽ እንዴት እነዚህ ምልክቶች በአገላለጽና በድምጸት ላይ ተጽእኖ እንደሚያደርጉ ማብራራት። **ብዙ ጊዜ** በእያንዳንዱ የንባብ ጊዜ የተለየ ቃል ትኩረት መስጠት፡ **በቡድን መጻፍ፡** መምህርአርዐያ በመሆን ተማሪዎች አንድ የጋራ ንባብ እንዲጽፉ ማበረታታት። | |

**ምዕራፍ ስምንት ፡የምግብ ዝግጅት (18 ክፍለ ጊዜ)**

**ከትምህርቱ የሚጠበቁ ውጤቶች**

ከዚህ ምዕራፍ ትምህርት በኋላ ተማሪዎች

- ከሚደመጠው ምንባብ ዋና ዋና መረጃዎች በተለየ መልክ ያደራጃሉ፤
- ከሚደመጠው ምንባብ ተመሳሳይ ቃላትን ያዛምዳሉ፤
- ተመሳሳይ ቅጥያ ያላቸውን ቃላት ይዘረዝራሉ፤
- ተራ አረፍ ተነገሮችን ከምንባብ ይለያሉ፤
- አጭር ታሪክ በተገቢ ሁኔታ ያነባሉ።

| ብቃት | ይዘቶች | የመማር ብልሃቶችና መሳሪያዎች | ምዘና |
|---|---|---|---|
| • ከሚደመጠው ምንባብ በተለየ መልክ ዋና ዋና መረጃዎች ያደራጃሉ።<br>• ከሚደመጠው ምንባብ ተመሳሳይ ቃላትን ያዛምዳሉ።<br>• ተመሳሳይ ቅጥያ ያላቸውን ቃላት ይዘረዝራሉ።<br>• ተራ አረፍ ተነገሮችን ከምንባብ ይለያሉ።<br>• አጭር ታሪክ በተገቢ ሁኔታ ያነባሉ። | **ማዳመጥና መናገር**<br><br>**ድምጻዊ ግንዛቤ የትዕምርተ ድምጽ ግንዛቤ**<br><br>**የቃላት ጥናት፡** ተዘውታሪ(የትምህርት)ቃላት<br>-ጽንሰሃሳቦችን መሰየም<br><br>**ማንበብና መጻፍ**<br><br>**ማንበብ፡ትክክለኛነት፣ፍ** | መምህሩ ስዕላዊ መግለጫዎችን በማጓደል አቅርቦ ተማሪዎች የተጓደለውን መረጃ መሙላት። መምህር በቃል ሲያነብ ተማሪዎች ሂደቱን የሚያሳይ ስዕላዊ መግለጫዉን መሙላት።<br>**ማጣመርና መነጠል፡** መምህር ከሚደመጠው ምንባብ የተወሰኑ ድህረግንድ ቅጥያ ያላቸውን ቃላት በመለየት፣ጥቂት ቃላትን ድህረ ግንድ ቅጥያዎቻቸውን በማጣመርና በመነጠል ያሳያል።ተማሪው የጠቀሩትን በምሳሌው መሰረት ድህረ ግንድ ቅጥያዎችን ከቃላቱ መለየት።<br>**መለየት** ተማሪዎች ቃላቱ በተመሳሳይ ድህረግንድ ቅጥያዎች የሚጀምሩ ወይም የሚጨርሱ መሆናቸውን መለየት።<br>**ተመሳሳይ ዜማ** ተማሪዎች ተመሳሳይ ዜማ ያላቸውን ቤተሰባዊ ቃላት መፍጠር።<br>**ቃላትን መመስረት** ተማሪዎች ማንበብን መለማመድ።<br>**ግድግዳላይ የተለጠፉ ቃላት፡**ተማሪዎች አዳዲስ ቃላትን ባወቁ ጊዜ መምህርበወረቀት ላይ በመጻፍ በግድግዳ ላይ ለጥፎ እንደማጣቀሻ መጠቀም። | በጽሁፍ/በቃል ጥያቄዎችን መጠየቅ<br>አካላዊ ምላሽ<br>ተማሪዎች በግል ለጥያቄዎች የሚመልሱት አካላዊ ምላሽ<br>ኢ-መደበኛ ቁጥጥር<br>ምልከታ<br>በስዕል መወከል<br>ተራ በተራ ማቅረብ<br>ስልታዊ ልምምድ<br>የመውጫ ካርድ |

| | | | |
|---|---|---|---|
| | **ጥንት፣ጥሩ አገላለጽ፣አንብቦ መረዳት**<br><br><br><br><br><br><br>**መጻፍ፡ትክክለኛነት ድምጸታዊ ግንዛቤ** | **አውድን ማዛመድ ተማሪዎች** የሚዛመዱ አውዶችን ማንበብ። (የድምጾችን/የፊደላትን ቅርጽ፣የባለቀለም ወረቀት ፣የካርቱን ስዕሎች ፣የቃላት ካርድ፣ ሰሌዳ መጠቀም)<br><br>**ቀስበቀስ ማብቃት** ፡በገደል ማሚቶ፣በህብረት ማንበብ፣ከጓደኛ ጋር ማንበብ፣በቀስታ ማንበብ<br>**በጊዜ የተገደበ ንባብ፡** ተማሪዎች አጭር ምንባብን ብዙ ጊዜ ማንበብ። እያንዳንዱን ንባብም ሰዓት መመዝገብ፤ለውጡንም ለመመልከት በቻርት ማስቀመጥ።<br>**መከፋፈል** ፡ ተማሪዎች ሀረጋትን ከፋፍለው ማንበብ።<br>**በርካታ እድሎችን መፍጠር፡**ዳራዊ እውቀት መገንባት፡የቀደመ እውቀት ማንጸባረቅ<br>**መገመት፡** መምህር ለተማሪዎች በሚሰጣቸው ፍንጭ ላይ መሰረት አድርገው ስለምን ሊያነቡ እንደሚችሉ እንዲገምቱ መጠቀም።<br>**መጠየቅ፡** ተማሪዎች ጥያቄ መጠየቅ እንዲችሉ እድል መሥጠት።<br>**ተቀናጅቶ ድምጽን ከፍ በማድረግ ማንበብ፡** ተማሪዎች በታሪኩ ውስጥ ይሳተፋሉ (የድምጾችን/የፊደላትን ቅርጽ፣የባለቀለም ወረቀት ፣የካርቱን ስዕሎች ፣የቃላት ካርድ፣ ሰሌዳ መጠቀም)<br>**ተዘውታሪ ቃላት፡** መምህር ከምንባቡ ውስጥ ከፍተኛ ድግግሞሽ ያላቸውን ቃላት ይለያሉ።ተማሪዎች ከፍተኛ ድግግሞሽ ያላቸውን ቃላት | |

| | | | |
|---|---|---|---|
| | | ከምንባቡ ውስጥም ሆነ ውጭ ፈጥኖ የመለየት ልምድ ያዳብራሉ። **ተደጋጋሚ ቃላዊ ንባብ** ለተማሪዎች ቃላዊ ንባብ በማካሄድ ከመምህራን፣ከጓደኛ ምላሽ ያገኛሉ። **በጊዜ የተገደበ ንባብ** ተማሪዎች አጭር ምንባብን ብዙ ጊዜ ያነባሉ።እያንዳንዱን ንባብም ሰዓት ይመዘግቡለታል፤ለውጡንም ለመመልከት በቻርት ያስቀምጣሉ። **የአረፍተ ነገር ቅኝት፡** አንድ አረፍተ ነገር ማንበብ **ብዙ ጊዜ** በእያንዳንዱ የንባብ ጊዜ የተለየ ቃል ትኩረት ይሰጥበታል። **ስዕላዊ መግለጫ**/graphic organization/፡ የቃላት ካርታ፣ቻርትን መረዳት፣ቃላትን መፈለግ **ጆርናሎችን መረዳት**/response journal/:ተማሪዎች ጆርናል አንብበው የቀደመ እውቀታቸውን ይገነባሉ፤የቀደመ እውቀታቸውን አውጥተው ያንጸባርቃሉ። **በቃል መጻፍ፡**መምህርሶስት ተራ አረፍተ ነገሮችን በቃል ለማጻፍ ያዘጋጃል።መምህርተማሪዎች በቃል የሚጽፏቸውን ሶስት ተራ አረፍተ ነገሮች ያዘጋጃል።ተማሪዎችም መምህርየሚያነባቸውን አረፍተነገሮች በማዳመጥ በትክክል ይጽፋሉ። **ማጠቃለያ** መረጃዎችን በተደራጀና በተጠቃለለ መልክ ማቅረብን ያለማምዳል። የፊደል ድምጽ | |

| | | | |
|---|---|---|---|
| | | ግንኙነት፣ቃላት፣አረፍተ ነገር<br>**ለምልክቶች ትኩረት መስጠት፡** አገላለጽን ለማሻሻል መምህር በግልጽ የምልክቶችን አላማ በመግለጽ እንዴት እነዚህ ምልክቶች በአገላለጽና በድምጸት ላይ ተጽእኖ እንደሚያደርጉ ማብራራት።<br>**በቡድን መጻፍ፡** መምህርአርዐያ በመሆን ተማሪዎች አንድ የጋራ ንባብ እንዲጽፉ ማበረታታት።<br>**ተዘውታሪ ቃላት፡** መምህር ከምንባቡ ውስጥ ከፍተኛ ድግግሞሽ ያላቸውን ቃላት ይለያሉ። ተማሪዎች ከፍተኛ ድግግሞሽ ያላቸውን ቃላት ከምንባቡ ውስጥም ሆነ ውጭ ፈጥኖ የመለየት ልምድ ማዳበር።<br>**ተደጋጋሚ ቃላዊ ንባብ** ለተማሪዎች ቃላዊ ንባብ በማካሄድ ከመምህራን፣ከጓደኛ ምላሽ ማግኘት።<br>**በጊዜ የተገደበ ንባብ** ተማሪዎች አጭር ምንባብን ብዙ ጊዜ ያነባሉ።እያንዳንዱን ንባብም ሰዓት ይመዘግቡለታል፤ለውጡንም ለመመልከት በቻርት ማስቀመጥ። | |

**ምዕራፍ ዘጠኝ ፡ዲጂታል መሳሪያዎች (18 ክፍለ ጊዜ)**

**ከትምህርቱ የሚጠበቁ ውጤቶች**

ከዚህ ምዕራፍ ትምህርት በኋላ ተማሪዎች

- ከሚደመጠው ምንባብ ዋና ዋና መረጃዎች በተለየ መልክ ያደራጃሉ፣
- ከምንባቡ ተቃራኒ ቃላትን ያዛምዳሉ፣
- ለቃላት አገባባዊ ትርጉም ይሰጣሉ፣
- ከቃለት ቅድመ ግንድ ቅጥያዎችን ይናገራሉ፣
- አጭር ታሪክን በትክክል ያነባሉ፣
- አራት አረፍተ ነገሮችን በትክክል ይጽፋሉ።

| ብቃት | ይዘቶች | የመማር ብልሃቶችና መሳሪያዎች | ምዘና |
|---|---|---|---|
| • ከሚደመጠው ምንባብ ዋና ዋና መረጃዎች በተለየ መልክ ያደራጃሉ።<br>• ከምንባቡ ተቃራኒ ቃላትን ያዛምዳሉ።<br>• ለቃላት አገባባዊ ትርጉም ይሰጣሉ።<br>• ከቃለት ቅድመ ግንድ ቅጥያዎችን ይናገራሉ።<br>• አጭር ታሪክን በትክክል ያነባሉ።<br>• አራት አረፍተ ነገሮችን በትክክል ይጽፋሉ። | **ማዳመጥና መናገር**<br><br>**ድምጻዊ ግንዛቤ**<br>**የትዕምርተ ድምጽ ግንዛቤ**<br><br>**የቃላት ጥናት፡**<br>ተዘውታሪ(የትምህርት )ቃላት<br>-ጽንሰሃሳቦችን መሰየም<br><br>**ማንበብና መጻፍ**<br><br>**ማንበብ፡ትክክለኛነት፣ ፍጥነት፣ጥሩ አገላለጽ፣አንብቦ መረዳት**<br><br>**መጻፍ፡ትክክለኛነት ድምጸታዊ ግንዛቤ** | መምህር የተማሪዎችን የቀደመ እውቀት ተጠቅሞ በማነሳሳት እንዲያዳምጡ ማዘጋጀት። በቡድን እንዲቀመጡ አድርጎ በአንድ በተወሰነ ርእሰጉዳይ ላይ እንዲያተኩሩ ማድረግ። ቻርቱን ከምንባቡ በወጡ መረጃዎች ማሟላት። በመጨረሻም እያንዳንዱ ቡድን የጨበጠውን መረጃ ለሌሎች ቡድኖች ማጋራት።<br>**ተቃራኒ ቃላት** መምህርተቃራኒ ቃላትን ለይቶ ማውጣት። በግድግዳ ላይ ቃላትን ጽፎ ያንጠለጥላል። ተማሪዎች ተቃራኒ ቃላት ያላቸውን ማዛመድ።<br>አገባባዊ ትርጉሞችን፡በምንባቡ ውስጥ ተደጋጋሚ ቃላት፣ቅድመግንድ ቅጥያ ያላቸው ቃላት<br>**ቃላትን መመስረት** መምህር የሚነበቡ ቃላትን አዘጋጅቶ በጥቁር ሰሌዳላይ መጻፍ።<br>**ተዘውታሪ ቃላት፡** መምህር ከምንባቡ ውስጥ ከፍተኛ ድግግሞሽ ያላቸውን ቃላት መለየት።ተማሪዎች ከፍተኛ | በጽሁፍ/በቃል ጥያቄዎችን መጠየቅ<br>አካላዊ ምላሽ ተማሪዎች በግል ለጥያቄዎች የሚመልሱት አካላዊ ምላሽ<br>ኢ.መደበኛ ቁጥጥር<br>ምልከታ<br>በስዕል መወከል<br>ተራ በተራ ማቅረብ<br>ስልታዊ ልምምድ<br>የመውጫ ካርድ |

| | | | |
|---|---|---|---|
| | | ድግግሞሽ ያላቸውን ቃላት ከምንባቡ ውስጥም ሆነ ውጭ ፈጥኖ የመለየት ልምድ ማዳበር።<br><br>**ግድግዳ ላይ የተለጠፉ ቃላት፡**ተማሪዎች አዳዲስ ቃላትን ባወቁ ጊዜ መምህር በወረቀት ላይ በመጻፍ በግድግዳ ላይ ለጥፎ እንደማጣቀሻ መጠቀም።<br>**አውድን ማዛመድ**<br>ተማሪዎች የሚዛመዱ አውዶችን ያነባሉ።(የድምጾችን/የፊደላትን ቅርጽ፣የባለቀለም ወረቀት ፣የካርቱን ስዕሎች ፣የቃላት ካርድ፣ ሰሌዳ መጠቀም)<br><br>**ቀስበቀስ ማብቃት** ፡ በገደል ማሚቶ፣በህብረት ማንበብ፣ከጓደኛ ጋር ማንበብ፣በቀስታ ማንበብ<br>**በጊዜ የተገደበ ንባብ፡**<br>ተማሪዎች አጭር ምንባብን ብዙ ጊዜ ማንበብ።እያንዳንዱን ንባብም ሰዓት መመዝገብ፤ለውጡንም ለመመልከት በቻርት ማስቀመጥ።<br>**መከፋፈል፡** ተማሪዎች ሀረጋትን ከፋፍለው ያነባሉ።<br>**ጆርናሎችን መረዳት**<br>፡ተማሪዎች ጆርናሎችን አንብበው መልዕክቱን መረዳት።<br>በርካታ እድሎችን ማቅረብ<br>**ስዕላዊ መግለጫ፡-** የቃላት ካርታ፣ቻርትን መረዳት፣ቃላትን መፈለግ<br>**መገመት፡** መምህር ለተማሪዎች በሚሰጣቸው | |

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| | | ፍንጭ ላይ መሰረት<br>አድርገው ስለምን ሊያነቡ<br>እንደሚችሉ እንዲገምቱ<br>መጠየቅ።<br>**መጠየቅ፡** ተማሪዎች<br>ጥያቄዎችን እንዲያጎለብቱ<br>ጊዜ መስጠት።<br>**ተቀናጅቶ ድምጽን ከፍ<br>በማድረግ ማንበብ፡**<br>ተማሪዎች አጭር ታሪክ<br>ማንበብ ላይ ማሳተፍ።<br>**ተደጋጋሚ ቃላዊ ንባብ፡**<br>ለተማሪዎች ቃላዊ ንባብ<br>በማካሄድ<br>ከመምህራን፣ከጓደኛ ምላሽ<br>ማግኘት።<br>**ለምልክቶች ትኩረት<br>መስጠት፡**<br>አገላለጽን ለማሻሻል<br>መምህር በግልጽ<br>የምልክቶችን አላማ<br>በመግለጽ እንዴት እነዚህ<br>ምልክቶች በአገላለጽና<br>በድምጸት ላይ ተጽእኖ<br>እንደሚያደርጉ ማብራራት።<br>**በጊዜ የተገደበ ንባበብ፡**<br>ተማሪዎች አጭር ምንባብን<br>ብዙ ጊዜ ማንበብ።<br>እያንዳንዱን ንባብም ሰዓት<br>መመዝገብ፤ ለውጡንም<br>ለመመልከት በቻርት<br>ማስቀመጥ።<br>**የአረፍተ ነገር ቅኝት፡** አንድ<br>አረፍተ ነገር ማንበብ።<br>**ብዙ ጊዜ** በእያንዳንዱ<br>የንባብ ጊዜ የተለየ ቃል<br>ትኩረት መስጠት።<br>ስእላዊ መግለጫ<br>ማጠቃለያ<br>**በቃል መጻፍ፡**መምህር ሶስት<br>ተራ አረፍተ ነገሮችን በቃል<br>ለማጻፍ ማዘጋጀት።<br>መምህር ተማሪዎች በቃል<br>የሚጽፏቸውን ሶስት ተራ | |

| | | | |
|---|---|---|---|
| | | አረፍተ ነገሮች ማዘጋጀት። ተማሪዎችም መምህር የሚያነባቸውን አረፍተ ነገሮች በማዳመጥ በትክክል መጻፍ።<br>**ማጠቃለያ** መረጃዎችን በተደራጀና በተጠቃለለ መልክ ማቅረብን ማለማመድ።<br>የፊደል ድምጽ ግንኙነት፣ ቃላት፣አረፍተ ነገር<br>**ጆርናሎችን መረዳት** :- መምህርተማሪዎች በክፍላቸው ውስጥ በየእለቱ የሚያከናውኑትን ተግባራት እንዲ ጽፉ ነግሮ ለሚቀጥለው ክፍለ ጊዜ ዘገባ ለማቅረብ ማዘጋጀት። ተማሪዎች በክፍሉ ካሉ ተማሪዎች ጋር የጻፉትን ታሪክ መለዋወጥ።<br>**አውድን ማዛመድ፡** ተማሪዎች የሚዛመዱ አውዶችን አንብበው መልዕክቱን ማግኘት።<br>**ቀስበቀስ ማብቃት** ፡ በገደል ማሚቶ፣በህብረት ማንበብ፣ከጓደኛ ጋር ማንበብ፣በቀስታ ማንበብ<br>**መከፋፈል፡** ተማሪዎች ሀረጋትን ከፋፍለው ማንበብ።<br>**በጊዜ የተገደበ ንባብ** ተማሪዎች አጭር ምንባብን ብዙ ጊዜ ማንበብ። እያንዳንዱን ንባብም ሰዓት መመዝገብ፤ለውጡንም ለመመልከት በቻርት ማስቀመጥ ። (በጆርናሉ ውስጥ ያሉ መልእክቶችን መገዘብ።) | |

**ምዕራፍ አስር ፡ የዱር እንስሳት (18 ክፍለ ጊዜ)**

**ከትምህርቱ የሚጠበቁ ውጤቶች**

ከዚህ ምዕራፍ ትምህርት በኋላ ተማሪዎች

- ከሚደመጠው ምንባብ ዋና ዋና መረጃዎችን በጽሁፍ ያቀርባሉ፤
- የምንባቡን ሀሳብ ከነባራዊው ህይወት ጋር ያዋህዳሉ፤
- ቃላአጋዋና የጥያቄ ምልክትን ይጠቀማሉ፤
- ምንባቡን በተገቢ ሁኔታ ያነባሉ፤
- ከክፍሉ ደረጃ ጋር ተመጣጣኝ የሆነ አረፍተ ነገር ይጽፋሉ።

| ብቃት | ይዘት | የመማር ብልሃቶችና መሳሪያዎች | ምዘና |
|---|---|---|---|
| • ከሚደመጠው ምንባብ ዋና ዋና መረጃዎችን በጽሁፍያ ቀርባሉ።<br>• የምንባቡን ሀሳብ ከነባራዊው ህይወት ጋር ያዋህዳሉ።<br>• ቃላአጋዋና የጥያቄ ምልክትን ይጠቀማሉ።<br>• ቃላትን ማጣመርና መነጠል<br>• ምንባቡን በተገቢ ሁኔታ ያነባሉ።<br>• ከክፍሉ ደረጃ ጋር ተመጣጣኝ የሆነ አረፍተ ነገር ይጽፋሉ። | **ማዳመጥና መናገር**<br><br>**ድምጻዊ ግንዛቤ**<br>**የትዕምርተ ድምጽ ግንዛቤ**<br><br>**የቃላት ጥናት፡**<br>ተዘውታሪ(የትምህርት)ቃላት<br>-ጽንሰሃሳቦችን መሰየም<br><br>**ማንበብና መጻፍ**<br><br>**ማንበብ፡ትክክለኛነት፣ፍጥነት፣ ጥሩ አገላለጽ፣አንብቦ መረዳት**<br><br>**መጻፍ፡ትክክለኛነት**<br>**ድምጸታዊ ግንዛቤ** | መምህርየተማሪዎችን የቀደመ እውቀት ተጠቅሞ በማነሳሳት እንዲያዳምጡ ማዘጋጀት፡ በቡድን እንዲቀመጡ አድርጎ ተማሪው ከምንባ ስለእንስሳት የሚገልጽ አረፍተ ነገር ጽፎ በቃል ማቅረብ።<br>**ማተካካት**<br>መምህርለተማሪዎች ቀለማትን/ድምጾችን በመግደፍ፣በመተካትና በመጨመር ጫወታ እንዲጫወቱ ማዘጋጀት።<br>ሀ.መግደፍ<br>ተማሪዎች አንድን ቃል በማዳመጥ በመነሻ ላይ የሚገኘውን ቀለም/ድምጽ በመግደፍ መጥራት።<br>ለ.መጨመር<br>ተማሪዎች ቃልን በማድመጥ በቃሉ ላይ ቀለም/ድምጽ በመጨመር መጥራት። | በጽሁፍ/በቃል ጥያቄዎችን መጠየቅ<br>አካላዊ ምላሽ<br>ተማሪዎች በግል ለጥያቄዎች የሚመልሱት አካላዊ ምላሽ<br>ኢ-መደበኛ ቁጥጥር<br>ምልከታ<br>በስዕል መወከል<br>ተራ በተራ ማቅረብ<br>ስልታዊ ልምምድ<br>የመውጫ ካርድ |

| | | | |
|---|---|---|---|
| | | ሐ.መተካት ተማሪዎች ባዳመጡት ቃል ውስጥ ያሉትን ቀለማት/ድምጾች በመተካት መጥራት። **መናገር** መምህር ቃልን በማሳየት እያንዳንዳቸውን ድምጾች ጠርቶ በማጣመር መናገር። (በታወቁ የፊደል ድምጽ መጠቀም) ተማሪዎች ሁሉንም ድምጽ በመጥራት አጣምረው መጥራት። (በታወቁ የፊደል ድምጽ መጠቀም) (የድምጾችን/የፊደላትን ቅርጽ፣የባለቀለም ወረቀት ፣የካርቱን ስዕሎች ፣የቃላት ካርድ፣ ሰሌዳ መጠቀም)<br><br>**አውድን ማዛመድ፡**ተማሪዎች መናገርን መለማመድ። **ተደጋጋሚ ቃላዊ ንባብ፡** ለተማሪዎች ቃላዊ ንባብ በማካሄድ ከመምህራን፣ከጓደኛ ምላሽ ማግኘት። **በጊዜ የተገደበ ንባብ፡** ተማሪዎች አጭር ምንባብን ብዙ ጊዜ ማንበብ።እያንዳንዱን ንባብም ሰዓት | |

| | | | |
|---|---|---|---|
| | | መመዝገብ ፤ለውጡንም ለመመልከት በቻርት ማስቀመጥ። **የአረፍተ ነገር ቅኝት፡** አንድ አረፍተ ነገር ማንበብ።ብዙ ጊዜ በእያንዳንዱ የንባብ ጊዜ የተለየ ቃል ትኩረት ይሰጥበታል። የፊደል ድምጽ ግንኙነት፣ ቃላት፣ አረፍተነገሮች **ለምልክቶች ትኩረት መስጠት፡** አገላለጽን ለማሻሻል መምህር በግልጽ የምልክቶችን አላማ በመግለጽ እንዴት እነዚህ ምልክቶች በአገላለጽና በድምጸት ላይ ተጽእኖ እንደሚያደርጉ ማብራራት።<br><br>**ጆርናሎችን መረዳት** መምህር ተማሪዎችን የእለት ሁለት ተግባራትን ጽፎ ለቀጣይ ጊዜ ማቅረብ። ተማሪዎች የጻፉትን የየእለት ተግባራት እርስ በርሳቸው መለዋወጥ። (ጆርናሎችን በማንበብ ተግባቦት መፍጠር) | |